# ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ

ከግራሃም ሐንኩክ

በጌታቸው ተሰፋዬ ጉጂ

የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

አሳታሚ ጌታቸው ተስፋዬ ጎጂ

ፖ.ሣ.ቁ. 2470
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ኢ.ሜል፡ gtesfayeg@yahoo.com

አምስተኛ እትም፡ 2001 ዓ.ም
አራተኛ እትም፡ 2000 ዓ.ም
ሦስተኛ እትም፡ 1999 ዓ.ም
ሁለተኛ እትም፡ 1995 ዓ.ም
የመጀመሪያ እትም፡ 1993 ዓ.ም

# መግቢያ

ግራሃም ሐንኩክ የታል ኪዳኑን ታቦት በተመለከተ አስር ዓመት የፈጀ ምርምርና ጥናት አካሂደዋል፡፡ "The Sign and the Seal" የተባለው መጽሐፍም የዚሁ ጥረት ውጤት ነው፡፡ መጽሐፉ ታትሞ በወጣበት ወቅት በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳጅነትን አትርፏል፡፡

ይህን መጽሐፍ ልዩ የሚያደርገው እስከአሁን ኢትዮጵያን በተመለከተ በአገር ውስጥና በውጪ ተመራማሪዎችና አርኪዎሎጂስቶች የተደረጉትን ጥናቶች ከጥላ ጎደል ያካተተ መሆኑ ነው፡፡ ደራሲው በእስራኤል፣ በግብጽ፣ በፈረንሣይ፣ በእንግሊዝና በኢትዮጵያ በመዘዋወር በርካታ መረጃዎችን አሰባስበዋል፡፡

ይሁንና ባንዳንድ ቦታዎች ራሳቸውም እንደሚሉት "wild speculations" (ተጨባጭነት የሌላቸውን አስተያየቶች) ይሰነዝራሉ፡፡ እነዚህን ክፍሎች ተርጓሚው በዚህ መፅሐፍ አላካተተም፡፡ ጠቀሜታም የላቸውም፡፡

ከዚህ በተረፈ መጽሐፉ ምሉዕነቱን እንደጠበቀ ቀርቧል፡፡

የውጪ አገር ምሁራንን ተለምዶአዊ እምነት (አመለካከት) በመጋፈጥ የተለዩ ሃሳቦቻቸውንና ግኝቶቻቸውን የሚሠነዝሩት የኚህ ተመራማሪ መጽሐፍ የልብወለድ ታሪክን ያክል ልብ እንደሰቀለ የሚነበብ ነው፡፡ በመፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት ዘመናት አቆጣጠርም የአውሮፓውያኑ ነው፡፡

- ተርጓሚው

# ማውጫ

ገጽ


የጥረት ጅማሬ (1983) ........ 1

ባዶ ተስፋ ........ 15

የቅዱስ ዕፀው ምሥጢራዊ ፅሁፍ ........ 26

የምሥጢሩ ቁልፍ ........ 45

ነጭ ነፍጠኞችና ጨለማው አህጉር ........ 53

ጥርጣሬን ማስወገድ ........ 72

ምሥጢርና ግብቷ የሌለው ፍለጋ ........ 90

ጉዞ ወደኢትዮጵያ ........ 108

ቅዱስ ሐይቅ ........ 111

የሕልም ሩጫ ........ 118

ዳዊትም በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ዘፈነ ........ 125

ምትሐት ... ወይስ ብልሃት ........ 138

የጨለማው ዘመን ቅርስ ........ 155

ክብርና ሞገሱ ከእስራኤል ርቋል ........ 158

የተደበቀ ታሪክ ........ 173

የደቡብ አገሮች በር ........ 191

ከዲያብሎሶች ጋር መቋደስ ........ 213

የማይደረስበት ቅርስ ........ 219

# ምዕራፍ አንድ

## የጥረት ጅማሬ (1983)

[የዘመን አቆጣጠሩ በሙሉ የአውሮፓውያኑ ነው።]

ለዓይን ያዝ አድርጓል። ከኢትዮጵያ ተራራማ በታዎች የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየር አጥንት ድረስ ዘልቆ በመግባት ሰውነትን ያንቀጠቅጣል። ኅበጥ ብለው መቋሚያቸውን እየተሞረኮዙ ዝግ ብለው የሚሄዱ መነኩሴ ከቤተመቅደሱ በራፍ ወደኔ መጡ። አስተርጓሚዬ እኔን ማስተዋወቅ ጀመረ። መነኩሴው በጥሞና ያዳምጡታል።

አመጣጤን፣የሥራ ፀባዬን፣ፍላጐቴን፣የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ መሆን አለመሆኔንና የመሳሰሉትን ጠየቁኝ። እኔም በደብዛዛው ብርሃን የጠያቂዬን ገጽታ እያስተዋልኩ ላቀረቡልኝ ጥያቄዎች በሙሉ ዝርዝር ምላሽ ሰጠሁ። መነኩሴው ጥቁር ሲሆኑ፣ ቆዳቸው በእርጅና ተሸብሽቧል። ሞራ የጋረዳቸው ትናንሽ ዓይኖቻቸው ይቁለጨለጫሉ። በረዥም ሪዛቸው ከተከበበው አፋቸው የሚወጣው ድምፅ ጉላ ያለ ቢሆንም የሚሉት በግልጽ ስለማይለይ ምናልባት ጥርሶቻቸው አልቀው ይሆናል ብዬ አሰብኩ። በርግጠኝነት መናገር የምችለው መነኩሴው የእድሜ ባለፀጋ እንደሆኑና እድሜያቸውም እስከ መቶ ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ነው። አነጋገራቸው አስተዋይነትን የተላበሰና ስለኔም ያቀረቡት ጥያቄ ማንነቴን በትክክል ለማወቅ ከመፈለግ መሆኑን ተገነዘብኩ።

ስለኔ የፈለጉትን ካወቁ በኋላ በዕርጅና በኮሰመነ እጃቸው በእርካታ ጨበጡኝ። የደረቡት ወፍራም ካባ መጠነኛ የዕጣን ሽታ ነበረው።

ትውውቁ እንዳበቃ ቀጥታ ወደፍሬ ነገሩ ገባሁ። ጀርባችን ላይ ተንጠላው ቤተክርስቲያን እያመለከትኩ፣ "የቃል ኪዳኑ ታቦት በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ ስለመገኘቱ ኢትዮጵያዊ አፈታሪክ መኖሩን አውቃለሁ። እርስዎም የታቦቱ ጠባቂ እንደሆኑ ሰምቻለሁ። እነዚህ ነገሮች እውነት ይሆኑ?" ስል ጠየቅኳቸው።

"እውነት ናቸው።"

"ግን በሌሎች ሀገሮችኩ ማንም ይህን ታሪክ አምኖ አይቀበልም። ስለናንተ ወግና ባሕል የሚያውቁ ጥቂት ሰዎች ቢኖሩም ይህን ታሪክ ግን አይቀበሉትም።"

"ሰዎች ያሻቸውን ማመን ይችላሉ። እውነታው ግን ታቦተ ሕጉ፣ ማለትም የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚገኘው በኛ እጅ መሆኑ ነው። ጠባቂውም እኔ ነኝ።"

"ግልፅ እንዲሆንልኝ እፈልጋለሁ" አልኳቸው ጣልቃ በመግባት። "ከእንጨት ተሠርቶ በወርቅ የተለበጠውና አሠርቱ ቃላት የተጻፉበትን ኦሪጂናሌ የጽላተ ሙሴ ማስቀመጫ ማለትዎ ነው?"

"አዎን፣ እግዚአብሔር ራሱ ነበር አሠርቱ ትእዛዛትን ሁለቱ ጽላቶች ላይ የጻፋቸው። ሙሴ እነዚህን ጽላቶች ያስቀመጠበት ታቦት፣እስራኤላውያን ወደተስፋይቱ ምድር በበረሀ በተጓዙበት ሁሉ

በድል እንዲወጡ አስችሉአቸዋል፡፡ ታላቅ ሕዝብም አድርጓቸዋል፡፡ በመጨረሻም ተልዕኮውን እንዳጠናቀቀ ንጉሥ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠርቶ በዚያ አኖረው፡፡ ብዙም ሳይቆይ ግን ታቦተ ሕጉ ወደ ኢትዮጵያ መጣ. . ."

"ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? እኔ የማውቀው አፈታሪክ በወቅቱ ኢትዮጵያን ትገዛ የነበረችው ንግሥተ ሳባ ወደኢየሩሳሌም ታሪካዊ ጉዞ ባደረገችበት ወቅት ከንጉሥ ሰሎሞን መጸነስዋንና ወንድ ልጅ መውለድዋን ነው፡፡ከጊዜ በኋላም ከንጉሥ ሰሎሞን የተወለደው ልዑል ይህን የቃል ኪዳን ታቦት ሠርቆ ወደኢትዮጵያ ማምጣቱን. . ."

መነኩሴው በረዥሙ ከተነፈሱ በኋላ "ያነሳሽው ልዑል ምኒልክ ይባላል፡፡ በኛ ቋንቋ ትርጉሙ 'የብልህ ሰው ልጅ' ማለት ነው፡፡ ኢየሩሳሌም ውስጥ ቢጸነስም ንግሥተ ሳባ ማርገዝዋን እንዳወቀች ወደሀገርዋ ተመልሳ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የተወለደው፡፡ ሃያ ዓመት ሲሞላው ምኒልክ ከኢትዮጵያ ወደ እስራኤል ተጓዘ፡፡ ከአባቱ ቤተ መንግሥት እንደደረሰም የክብር አቀባበል ተደረገለት፡፡ ይሁንና ለአንድ ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ የእስራኤል ታላላቅ ሰዎች ንጉሥ ሰሎሞን፣ ምኒልክን ከኛ የበለጠ ያቀርበዋል፣ ይወደዋል በሚል በምቀኝነት ተነሳሱበት፡፡ ወደሀገሩ ይመለስ ዘንድም አጥብቀው ጠየቁ፡፡ ንጉሡም የቀረበለትን አቤቱታ ካዳመጠ በኋላ ምኒልክ ወደሀገሩ የሚመለሰው የእስራኤል ታላላቅ ሰዎች የበኩር ልጆች ሁሉ በአጃቢነት አብረውት ወደ ኢትዮጵያ የሚሄዱ ከሆነ ብቻ መሆኑን ገለፀላቸው፡፡

በዚህም ተስማሙ፡፡ ከነዚህም መካከል ከምኒልክ ጋር ወደኢትዮጵያ ከመጡት መካከል የሊቀ ካህናት ሳዶቅ የበኩር ልጅ አዛርያስ ይገኝበታል፡፡ የቃል ኪዳኑን ታቦት ከቤተ መቅደስ ቅድስተ ቅዱሳን ደብቆ ያወጣውም እርሱ ነበር፡፡ ምኒልክ ታቦቱ በድብቅ ወጥቶ ከርሱ ጋር መምጣቱን ያወቀው ከኢየሩሳሌም ብዙ ርቆ ከተጓዘ በኋላ ነበር፡፡ ስለሁኔታው እንደነገሩት ድርጊቱ የተፈጸመው በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ተገንዝቦ ታቦተ ሕጉ ከርሱ ጋር መሆን እንዳለበት አምኖ ተቀበለ፡፡ በዚህ ሁኔታ ነበር ታቦተ ሕጉ ወደኢትዮጵያ የመጣውና ከዚህች ከተቀደሰች ከተማ የተቀመጠው" አሉ፡፡

"ይህ አፈታሪክ እውነት ነው እያሉኝ ነው?"

"አፈታሪክ አይደለም፤ ታሪክ ነው፡፡"

"እንዴት እርግጠኛ ሊሆኑ ቻሉ?"

"ምክንያቱም ጠባቂው እኔ ነኝ፡፡ ስለዚህም የታቦተ ሕጉን ምሥጢር ጠንቅቄ አውቃለሁ፡፡"

በመካከላችን ፀጥታ ሰፈነ፡፡ እኔም መነኩሴው በረጋ መንፈስ የነገሩኝን ሊሆን የማይችልና የማይታመን ነገር በውስጡ ማሰላሰል ያዝኩኝ፡፡ በመቀጠልም ለምንና እንዴት ለዚህ ኃላፊነት ሊመረጡ እንደቻሉ ጠየቅኳቸው፡፡ ርሳቸው ለዚህ ኃላፊነት መመረጥ ታላቅ ክብር መሆኑን ገልጸው፣ የተመረጡትም ከሳቸው በፊት የነበሩት ጠባቂ በተናዘዙት መሠረት መሆኑን ነገሩኝ፡፡ እሳቸውም የማይቀረው ሞት ከመምጣቱ ጥቂት ቀደም ብለው ተከታያቸውን እንደሚመርጡ ተናገሩ፡፡

"ለዚህ ኃላፊነት ለመብቃት ምን ማሟላት ያስፈልጋል?

"የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የልብ ንጽሕና፣ የኅሊናና የአካል ቅድስና፡፡"

"ከርስዎ ሌላ ጽላቱን ለማየት የሚፈቀድለት አለ?" ስል ጠየቅኳቸው፡፡

"የለም፡፡ እኔ ብቻ ነኝ ማየት የምችለው፡፡"

"በዚህ ዓይነት ጽላቱ ከቤተ መቅደሱ ወጥቶ አያውቅም ማለት ነው?"

መነኩሴው ጥያቄዬን ከመመለሳቸው በፊት ለረዥም ጊዜ በዝምታ ቆዩ፡፡ በመጨረሻ ጥንት በተለያዩ ዓበይት የቤተ ክርስቲያን በዓላት ወቅት ይወጣ እንደነበርና ወደበኋላው ግን በዓመት አንዴ በበዓለ ጥምቀት ብቻ እንዲወጣ ተደርጐ እንደነበር ገለፁልኝ፡፡

"በሚቀጥለው ጥር ወር ብመጣ ታቦቱን የማየት እድል ይኖረኛል ማለት ነው?"

ጠባቂው ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ትኩር ብለው አዩኝና "በአካባቢው ጦርነት እንዳለ ማወቅ አለብህ፡፡ መንግሥታችን ክፉ ነው፡፡ ሕዝቡም እየተቃወመው ስለሆነ ጦርነቱ ከቀን ወደቀን ወዳለንበት እየቀረበ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ታቦቱ ዳግም በበዓላት ወቅት ይወጣል ብዬ አልገምትም፡፡ ይህን መሠል ክቡር ዕቃ አውጥተን ችግር ውስጥ መውደቅ አንፈልግም፡፡ . . . በሰላም ጊዜም ቢሆን ታቦቱን ማየት አትችልም፡፡ በበዓላትም ቢሆን ልዩና ወፍራም በሆነ መጐናጸፊያ ከሸፈንኩት በኋላ ነው የሚወጣው፡፡"

"ለምንድነው የሚሸፍኑት?"

"ምእመናኑን ከታቦቱ ለመጠበቅ፡፡"

የተናገሩት ግልጽ ስላልሆነልኝ እስተርጓሚዬን፣ "መነኩሴው ያሉት ምእመናኑን ከታቦቱ ለመጠበቅ ነው ወይንስ ታቦቱን ከምእመናኑ ለመጠበቅ?" ስል ጠየቅኩት፡፡

መልስ ያገኘሁት ከቆይታ በኋላ ነበር፡፡ "ምእመናኑን ከታቦቱ ለመጠበቅ ነው፡፡ ታቦቱ ታላቅ ኃይል አለው" አሉ በመጨረሻ፡፡

## ታላቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር

በዘመነ አሪት እስራኤላውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያ በመሆኑ የሚያመልኩትና በምድር ላይ ያኖረው ምልክቱና ማኅተሙ፣ እንዲሁም የኃይሉ መገለጫ ነው ብለው ያምኑ ነበር፡፡ አሠርቱ ቃላት የተጻፉባቸው ሁለቱ የድንጋይ ጽላቶች የሚቀመጡበት ታቦት ከእንጨት የተሠራ ሆኖ ሁለት ክንድ ርዝማኔ፣ አንድ ክንድ ተኩል ቁመትና ወርድ ያለው በውስጥና በውጭ በወርቅ የተለበጠ ነው፡፡ ከተቀጠቀጠ ንፁህ ወርቅ የተሠሩ ሁለት ኪሩቤል፣ አንዱ

ኪሩብ በአንድ ወገን፣ ሁለተኛው ኪሩብ በሌላ ወገን [illegible] ወደላይ ዘርግተው ወደመክደኛው በትይዩ ሲመለከቱ የሚያሳይ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎችም ጥንታውያን መዛግብት እንደሚሉት ታቦተ ሕጉ በሚንቀለቀል ብርሃኑና እሳቱ በነቀርሳማ እባጮና በለምጽ የመለወጥ፣ የመምታት፣ የማቃጠል፣ ተራራዎችን ወደሜዳማነት ወንዞችን የማድረቅ፣ ታላላቅ ሠራዊትን የመደምሰስ፣ ከተማዎችን የማፈራረስ ኃይል አለው።

እነዚሁ ምንጮች አክለውም ታቦተ ሕጉ የአይሁዶች የእምነት መሠረት እንደሆነና ንጉሥ ሰሎሞንም የመጀመሪያውን ቤት መቅደስ በኢየሩሳሌም የሠራው ይህንኑ ታቦት በክብር ለማኖር አስቦ መሆኑን ይገልጻሉ። ይሁንና ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንድ ሺህና ስድስት መቶ ዓመታት መካከል በነበረው ጊዜ ይህ እጅግ ድንቅና ተአምራዊ ታቦት የትና ወዴት እንደሄደ ሳይታወቅ በመሠወሩ ጉዳዩ ለብዙ ሺህ ዓመታት እንቆቅልሽ ሆኖ ቆይቷል።ማስረጃው እንደሚጠቁመው በ587 ዓመተ ዓለም የናቡከደነጾር ሠራዊት ኢየሩሳሌምን ባቃጠለበት ጊዜ ታቦቱ በቦታው አልነበረም። በጦርነቱ የተማረኩ እስራኤላውያን ከባቢሎን ወደሀገራቸው ኢየሩሳሌም በ538 ዓመተ ዓለም ተመልሰው ሁለተኛውን ቤተ መቅደስ በሠሩበት ወቅትም ታቦቱ በዚያ አልነበረም። ይህም ቀደም ሲል ታቦቱ በባቢሎናውያን አለመዘረፉን ያረጋግጣል።

በካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ተማራማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ሪቻርድ ኤሊየት ፍሬድማን በ1987 ይህን ጉዳይ አስመልክተው ሲጽፉ "የታቦቱ መጥፋት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስደናቂ ምሥጢሮች እንደ አንዱ ይቆጠራል" ብለዋል።

"ታቦቱ ወደሌላ ቦታ ስለመወሰዱ፣ ስለመውደሙ (መቃጠሉ) ወይም ስለመደበቁ የተፃፈ ነገር የለም። 'ከዚህ በኋላ ታቦቱ ጠፋ። በምን ሁኔታ ላይ እንዳለም አናውቅም' ወይም 'የት እንዳለ ማንም አያውቅም' የሚሉ አስተያየቶች እንኳን አልተፃፉም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዓለም ካሉ ነገሮች ሁሉ ትልቅ ሥፍራ የተሰጠው ክቡር ዕቃ፣ እንደዋዛ ይጠፋል።"

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እስከ ንጉሥ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት (970 - 931ቅድመ ልደተ ክርስቶስ፤ ቅ.ል.ክ) ድረስ ከሁለት መቶ ጊዜ በላይ ስለታቦቱ ተጠቅሷል። ከዚህ ብልህና አስተዋይ መሪ ዘመነ መንግሥት በኋላ ግን ታሪኩ አንድም ጊዜ እንኳን ተነስቶ አያውቅም። ይህን የመሰለ ክቡርና ውድ ቅርስ፣ በተለይ ደግሞ ሃይማኖታዊ ክበሬታ ያለው፣ በብሉይ ኪዳን የኋለኞቹ መጻሕፍት ጨርሶ አለመወሳቱ የሚያስገርም ነው።

በዚህም የተነሳ በዘመኑ የነበሩት ፀሐፍትና ቀሳውስት የዚህን ቅዱስ ቅርስ የመሰወር ምሥጢር ላለማሳወቅ ከፍተኛ የሆነ የመሸፋፈን ጥረት ያደረጉ አስመስለዋቸዋል። የተሰወሩ ቅርሳ ቅርሶችን የሚያስሱ [illegible] ወገኖች የዚህን ታላቅ ቅርስ መሰወር አውቀው በርካታ [illegible] ቢያካሂዱም እንዳቸውም አልተሳካላቸውም። በ1981 የጠፋው [illegible]



ዘራፊዎች (Raiders of the Lost Ark) በሚል ርእስ ሐሪሰን ፎርድ እንደ ኢንዲያና ጆንስ ሆኖ የተወነችበት የሆሊዉድ ፊልም በአሜሪካና በአውሮፓ ታይቶ ነበር። እኔም በ1983 ናይሮቢ ውስጥ ይህንኑ ፊልም የማየት ዕድሉ አጋጥሞኝ ነበር። ፊልሙን ካየሁ በኋላ የታቦቱን ዱካ አነፍንፌ የማግኘት ሃሳብ አደረብኝ። ከጥቂት ወራት በኋላም ሃሳቤን ለመተግበር ወደኢትዮጵያ አመራሁኝ። ጉዞዬንም ወደትግራይ አቅንቼ የኢትዮጵያውያን ቅድስት ከተማ የምትባለውን አክሱምን ጎበኘሁ። በዚህን ጊዜ ነበር ጠባቂውን መነኩሴ ያገኘኋቸው።

## 1983፤ ኢትዮጵያ በጦርነት ውስጥ

ከዓመታት ከባድ ውጊያ በኋላ ግንቦት 28፣ 1991 የኢትዮጵያ መንግሥት በተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት ሲወገድ በህብረቱ ውስጥ ትልቅ ሚና የነበረው ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ ነበር። በ1983 ወደ አክሱም በሄድኩበት ወቅት ግን ሕወሐት ኢነስተኛ የሽምቅ ተዋጊ ግንባር ነበር። በጊዜው የአክሱም ከተማ በሽምቅ ተዋጊዎች ብትከበብም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ነበረች። በ1974 በተካሄደው አብዮት አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ከተወገዱና በአፍሪካ ከተነሱት ጨካኝ መሪዎች አንዱ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በትረ መንግሥቱን እንደጨበጡ፣ አክሱም የነበሩት የእንግሊዛውያን አርኪዎሎጂስቶች ተባረው ነበር። ከዚያ ወዲህ ወደከተማይቱ የመጣሁ የመጀመሪያው የውጪ ዜጋ እኔ ነበርኩ።

የሚያሳዝነው በወቅቱ ወደአክሱም እንድሄድ የተፈቀደልኝ በራሴ ተነሳሽነት ወይም ልዩ ጥረት ሳይሆን፣ ለመንግሥቱ አንድ ሥራ ለመስራት በመስማማቴ ነው። ወደበኋላ ከፉኛ ብፀፀትበትም በ1983 ኢትዮጵያን በተመለከተ አንድ መጽሐፍ ለማዘጋጀት ከኮሎኔሉ መንግሥት ጋር ውል ተፈራርሜ ነበር። በመጽሐፉ ውስጥ የሀገሪቱን ሕዝቦች የባህልና የግዛት አንድነት በማጉላት እንዳቀርብ ነበር የተፈለገው። በተፈራረምኩት ኮንትራት መሠረትም የባለ ሥልጣናትን ስም በማንሳት ማመስገንም ሆነ መንቀፍ (መንግሥቱ ኃ/ማርያምን ጨምሮ) እንደሌለብኝ ተነግሮኛል። እንደዛም ሆኖ ማንም ሰው እንዲጎበኘው ያልፈቀዱለትን ቦታ ለኔ መፍቀዳቸውና ገንዘብም መክፈላቸው ባለሥልጣናቱ ጥቅም ቢያገኙበት መሆኑ ግልጽ ነበር። ሆኖም በአካባቢው የተጠናከረ የሽምቅ ተዋጊዎች እንቅስቃሴ ስለነበር፣ በመኪና ወደአክሱም መጓዝ የሚታሰብ አልነበረም። የነበረው አማራጭ በአውሮፕላን መብረር ብቻ ነው። በዚህም መሠረት ከተመራማሪዋ ባለቤቴ ካሮልና ከፎቶግራፍ አንሺዬ ደንካን ዊሊስ ጋር ወደአሥመራ በረርን።

የኤርትራ ሽምቅ ተዋጊዎች መንግሥትን የሚፋለሙበት ወቅት ስለነበረ አሥመራን ውጥረት ነግሶባታል። ሆስፒታሎቿም ከትግራይና ከኤርትራ የውጊያ ቀጣናዎች በመጡ ቁስለኞች ታጭቀዋል። በደጋማ

አምባ ላይ የተቆረቆረችው አሥመራ ከበባት በረሃማ የጠረፍ አካባቢ ጋር ስትነፃፀር የምትስብና የደስደስ ያላት ከተማ ናት። ከ1889 ጀምሮ በኢትዮጵያ እስከተያዘችበት 1950ዎቹ ድረስ በኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ሥር የቆየችው አሥመራ የላቲኖችን ገፅታ የተላበሰች ናት። መንገዶቿ ውብ የሐረግ አበባ ባጌጡ ዛፎች ቢያሸበርቁም፣ በወቅቱ ክላሺንኮቭ የታጠቁ የሶቪየትና የኩባ የጦር አማካሪዎች ይታዩባት ነበር።

የጦር አማካሪዎቹ ምክር ግን ለኢትዮጵያ ሠራዊት የፈየደው ነገር አልነበረም። ምክንያቱም የአሥመራን ሆስፒታሎች ከአቅማቸው በላይ በቁስለኞችና በጦር ጉዳተኞች ከመታጨቅ አላዳኗቸውም። ለመንግሥት ባለሥልጣናቱም የተረፋቸው ቢኖር ውጥረት፣ ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ ነበር።

ስጋታችን ይበልጥ የጨመረው አሥመራ ከተማ አምባሶይራ ሆቴል ውስጥ ጥቂት ቀናት ከቆየን በኋላ ሁለት ዛምቢያውያን ፓይለቶችን ባገኘንበት ወቅት ነበር። እዚህ አገር የመጡት ለስድስት ወራት የንግድ አውሮፕላኖችን የማብረር ችሎታቸውን ለማሻሻል ቢሆንም፣ የገጠማቸው ዕጣ ግን ከትግራይና ከኤርትራ የውጊያ ግንባሮች የቆሰሉ ወታደሮችን ወደአሥመራ ማመላለስ ነበር። ይህን ድርጊት በመቃወም አየር መንገዱን በዚህ አደገኛ ሥራ ላይ እንዳይመድባቸው ጠይቀዋል። ሆኖም የኮንትራት ውላቸውን በጥንቃቄ ሲመረምሩት በዚህ ዓይነት የበረራ ግዳጅ መሳተፍ እንዳለባቸው ተረዱ። ለበርካታ ሳምንታትም ይህንኑ የመሠለ በረራ በማካሄድ ቁስለኞችን ሲያመላልሱ ቆዩ። እንዳጫወቱኝ ከሆነ በየዕለቱ የሚያዩትን የወታደሮች ስቃይና ሐዘን ለመርሳት በየምሽቱ ሰክረው መተኛት ነበረባቸው።

በተለይ አንድ ቀን ጧት ያዩት እግሩ በፈንጂ የተቆረጠና የራስ ቅሉ በሞርታር የተመታ ወታደር ሁኔታ ከአዕምሮአቸው ሊጠፋ አልቻለም። ከፍተኛ ጉዳት በወታደሮቹ ላይ ሲደርስ የዲሲ-3 አውሮፕላኖቻቸውን የጭነት መጠን በመተላለፍ ወደአርባ የሚጠጉ ቁስለኞችን የሚጭኑበት ጊዜም ነበረ። ይህ ሁኔታ አደጋ ሊያስከትል ቢችልም ቁስለኞቹ ሲሞቱ ከማየት ይልቅ ይህን መሰል እርምጃ መውሰድን ይመርጡ እንደነበር አጫውተውኛል።

አልፎ አልፎ በየቀኑ እስከ አራት በረራዎች ድረስ እንደሚያደርጉና ወደአክሱም ባደረጓቸው ሁለት በረራዎችም አውሮፕላናቸው በአየር መቃወሚያ ጥይት ሁለት ጊዜ በመመታቱ ወደዛ መብረሩን እንደሚፈሩ ጭምር ነግረውኛል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ አርማ ያሉባቸውን አውሮፕላኖች ቢያበሩም የሕወሓት ተዋጊዎች በረራው ለወታደራዊ ተልዕኮ መዋሉን ስለሚያውቁ ሊታለሉ አልቻሉም። "ሥራቸው እኛን ዒላማ ማድረግ ሆኗል" በማለት አብራሪዎቹ አጫወቱኝ። ሩስያውያንና ኩባውያን ያልሆኑ የውጪ ዜጎችን በማግኘታቸው የተደሰቱት እነዚህ ዛምቢያውያን ይህን ሁሉ ሲያጫውቱን ስለኛ ማንነት አልጠየቁም ነበር። በመጨረሻ ግን ለመንግሥት በሥዕል ያሸበረቀ ስለኢትዮጵያ ቡና የሚያወሳ መጽሐፍ



ለማዘጋጀት መምጣታችንንና ወደአክሱም ለመጓዝም እንደምንፈልግ በገለጽንላቸው ጊዜ በድንጋጤ ተዋጡ።

"ለምን?" ሲሉም በድንጋጤ ጠየቁ።

"ምክንያቱም አክሱም ጥንታዊ የአገሪቱ መናገሻ ከተማ፣ የክርስትና እምነት መሠረትና የአርኪዎሎጂ ጥናት የሚካሄድባት ቦታ በመሆንዋ መጽሐፋችን ይህን ካላካተተ ጣዕም የለሽ ስለሚሆንብን ነው።"

"ምናልባት ልንወስዳችሁ እንችል ይሆናል" ሲል አንዱ ፓይለት ጠቆም አደረገ።

"ቁስለኞችን ለማምጣት ስትሄዱ ማለትህ ነው?"

"የለም። በንደዚህ ዓይነቱ በረራ እንድትሄዱ አይፈቀድላችሁም። ነገር ግን ከነገ በስቲያ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች አክሱም ወደሚገኘው የጦር ሰፈር ስለሚሄዱ ከነሱ ጋር መጓዝ ትችሉ ይሆናል። በርግጥ ይህን ለማድረግ የሚያስችላችሁ ውሳኔ ከአዲስ አበባ መገኘቱ ወሳኝ ነው። ለሁሉም ግን ለምን አትሞክሩም።"

## ጉዞ ወደአክሱም

የፕሮጀክታችን ተቆጣጣሪ ወደነበሩት ሚኒስትር ስልክ በመደወል ከተነጋገርኩ በኋላ ወደአክሱም በሚበረው ዲሲ-3 አውሮፕላን ቦታ ማግኘት ቻልን። ከበረራው በፊት በነበረው አንድ ሠዓት የቆይታ ጊዜና ሰላሳ አምስት ደቂቃ በፈጀው በረራ ወቅት ስለምንጓዝበት ጉዳይ በቂ ግንዛቤ ለማግኘት የሚቻለኝን ያህል አነበብኩ።

የቀድሞ የታሪክ ጥናቶች እንደሚያስረዱት አክሱም ታዋቂ ከተማ ነበረች። ለምሳሌ፣ ማንነቱ ያልተገለጸ አንድ የግሪክ ንግድ መፅሐፍ ደራሲ "ፔሪፕለስ ኦፍ ዘ ኤርትሪያን ሲ" (Periplus of the Erythrean Sea) በተባለው መጽሐፉ ውስጥ የአክሱም ገዢ የነበረው ልዑል ከብዙዎቹ የላቀና የተማረ፣ እንዲሁም የግሪክም ቋንቋ ዕውቀት የነበረው መሆኑን ገልጿል። ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ደግሞ ጁሊያን የተባለ የሮማው ንጉሠ ነገሥት ጀስቲንያን አምባሳደር እንደገለጸው አክሱም ከመላው ኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ የምትበልጥ ታላቅ ከተማ ነበረች። ንጉሡም በወርቅ የተለበጠ አነስተኛ ጨርቅ በዕንቁ ማንገቻ አያይዞ ከወገቡ በታች ከመልበሱ በስተቀር ዕርቃኑን ነበር ማለት ይቻላል። በእጆቹም ላይ የወርቅ አምባሮችን አጥልቋል። በአንገቱም ላይ የወርቅ ሐብል ሲያደርግ ራሱ ላይ ደግሞ በወርቅ የተንቆጠቆጠ ጨርቅ ጠምጥሟል። ንጉሡ የአምባሳደሩን የሹመት ደብዳቤ ሲቀበል፣ በአራት ዝሆኖች የሚጎተት ባለአራት እግር ሠረገላ ላይ ሆኖ ነበር። ሠረገላውም ትልቅና በወርቅ ያጌጠ ነበር ሲል አምባሳደሩ አብራርቷል።

በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ ኮስማስ ኢንዲኮፕሌስተስ የተባለ ተጓዥ ክርስቲያን መነኩሴ የጁሊያንን አባባል የሚያጠናክር፣ በአክሱም የነበረው "የኢትዮጵያው ንጉሥ ቤተመንግሥት አራት

ምሰሶዎች ሲኖሩት"፣ በውብ ቅርጻ ቅርጾችም ያጌጠ እንደነበር በአድናቆት ጽፏል፡፡ በንጉሡ ትዕዛዝ የተያዙ ለማዳ ቀጭኔዎችም ትርኢት ሲያሳዩ ተመልክቷል፡፡

ይህም ሥዕል የአክሱም መንግሥት በሮማውያንና በፋርስ ግዛቶች መካከል የነበረ ኃያል መንግሥትና የንግድ መርከቦቹንም እስከ ግብጽ፣ ሕንድ፣ ቻይናና ሲሎን ድረስ ይልክ እንደነበረ ከሚነገረው ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ የአክሱም መንግሥት የክርስትና እምነትን የመንግሥት ሃይማኖት አድርጐ የተቀበለውም በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነበር፡፡

ስለኢትዮጵያ የክርስትናን እምነት መቀበል በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖር በነበረው ሩፊኖስ በተባለ የሃይማኖት ምሁር የተፃፈ ታሪክ ይገኛል፡፡ ሩፊኖስ በዘመናዊ ታሪክ ጸሐፍት ዘንድ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው ሰው ነው፡፡ በሩፊኖስ ታሪክ መሠረት አንድ ሜሮፒየስ የተባለ ክርስቲያን ነጋዴና ፈላስፋ ስለርኅራኄና ደግነት ያስተምራቸው የነበሩትን ሁለት ሶርያውያን ወንድማማቾች ይዞ ወደሕንድ እየተጓዘ ነበር፡፡ ከሁለቱ ወጣቶች ታላቅየው ፍሬምናጦስ ሲባል፣ ታናሹ ኤዲሲየስ ይባላል፡፡ በመልስ ጉዟቸው በቀይ ባህር በኩል በሚያልፉበት ወቅት መርከባቸው ኢትዮጵያ ጠረፍ ስትደርስ ተማረከች፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የምስራቅ ሮማውያን ነጋዴዎች ከጠረፉ አካባቢ ሰዎች ጋር የገቡትን ውል በማፍረሳቸው የአካባቢው ሰዎች እነሱን ለመበቀል እርምጃ በመውሰዳቸው ነበር፡፡

በተካሄደው ውጊያ ሜሮፒየስ ሲገደል፣ ልጆቹ ግን ስለተረፉ በወቅቱ የአክሱም ንጉሥ ወደነበረው አልአሜዳ ተወሰዱ፡፡ ንጉሡም ኤዲሲየስን አሳላፊው ሲያደርገው፣ ብልህና ጠንቃቃ የነበረውን ፍሬምናጦስን ፀሐፊና እቃቤንዋይ አድርጐ ሾመው፡፡ ንጉሥ አልአሜዳ ብዙም ሳይቆይ በመሞቱ፣ ኢዛና የተባለው ሕፃን ልጁ የመንግሥቱ ወራሽ ሆነ፡፡ ንጉሥ አልአሜዳ ከመሞቱ በፊት ለሁለቱ ሶርያውያን ነፃነታቸውን ሰጥቷቸው የነበረ ቢሆንም፣ የንጉሡ ሚስት፣ ልጇ ኢዛና ለንግሥና እስኪደርስ፣ በተለይ ፍሬምናጦስን እንዲቆይ ለመነችው፡፡ በቤተ-መንግሥቱ ውስጥም የፍሬምናጦስ ተሰሚነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄደ፡፡ ከውጪ አገር ክርስቲያን ነጋዴዎች ጋር ግንኙነቱን በማጠናከር በሀገሪቱ ውስጥ የጸሎት ቤቶች እንዲታነጹና ክርስትና እንዲስፋፋ አደረገ፡፡

ኢዛና ለንግሥና ሲደርስ፣ ኤዲስየስ ወደቲር ተመለሰ፡፡ ፍሬምናጦስ ግን በዘመኑ የክርስትና ታላቅ ማዕከል ወደነበረችው ወደአሌክሳንድርያ በመጓዝ በዚያ ከነበሩት ፓትርያርክ አትናቴዎስ ጋር ተገናኝቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለአከናወነው ሥራ በመግለጽ በኢትዮጵያ ላሉት ምእመናን አቡን እንዲላኩላቸው ተማጸነ፡፡ አትናቴዎስም ጉዳዩን በጥንቃቄ ካመዛዘኑ በኋላ ፍሬምናጦስን ጉባዔ ጠርተው አቡን አድርገው በመቀባት ወደኢትዮጵያ ተመልሶ የጀመረውን ሃይማኖታዊ ተልዕኮ እንዲቀጥል አዘዙት፡፡



ፍሬምናጦስም ወደአክሱም ተመልሶ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ አቡን በመሆን ንጉሥ ኢዛናን ከማጥመቅ ጀምሮ (በ331ድህረ ልደተ ክርስቶስ 2 ድ.ል.ክ) ሐዋርያዊ ተልዕኮውን መፈጸም ቀጠለ፡፡

በመሆኑም ከኢዛና ንግሥና በፊት የነበሩት ሳንቲሞች የሙሉና ግማሽ ጨረቃ ምስልን የያዙ ሲሆኑ፣ በኢዛና ዘመንና ከዚያ በኋላ ያሉት ግን የመስቀልን ቅርጽ የያዙ ናቸው፡፡

አክሱም የክርስትና እምነት ዘር የተዘራባትና ከ1ኛው እስከ 10ኛው መቶ ክፍለ ዘመንም ድረስ የነገሥታት መዲና መሆኗ ትልቅ የትኩረት ነጥብ ቢሆንም፣ ጥንታዊቷ አክሱም ለአሁኑ ሥራዬ ያላት ጠቀሜታ ግን ሠፋ ይላል፡፡ በበረራዬ ወቅት ያነበብኩት መጽሐፍ አክሱም በወቅቱ ታላላቅ ሐውልቶች፥ ቤተመንግሥቶች ወዘተ በብዛት እንደነበሯት የጥንታዊ ቅርሶች ፍርስራሾችን በአካባቢው በማየት ማረጋገጥ እንደሚቻል ይገልፃል፡፡ ከተማዋ የምትታወቅባቸውና አሁንም በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኙት ከሁለት ሺ ዓመታት በላይ ያስቆጠሩት ሐውልቶቿ ከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ላይ የነበረች ለመሆኗ፥ ከሰሃራ በታች በአፍሪካ ውስጥ በሥነ ጥበብ፣ ሥነ ሕንፃ ሥራ የላቀ ደረጃ ላይ እንደደረሰች በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ቀደም ሲል ያነበብኩት ታሪካዊ ጽሑፍ ያስገረመኝ ደግሞ በኢትዮጵያውያን አፈ.ታሪክ መሠረት የቃል ኪዳኑ ታቦት በዚህች ከተማ ውስጥ በአንድ ቤተክርስቲያን አጠገብ በምትገኝ አንዲት አነስተኛ መቅደስ ውስጥ መኖሩን ማውሳቱ ነበር፡፡ ሆኖም ይኸው መጽሐፍ በኢትዮጵያ ይገኛል የተባለውን ይህን ክቡር ታቦት እና ከንግሥተ ሳባ ጋር የተገናኘውን ታሪክ ልብወለድ ነው ብለው የታሪክ ሰዎች እንደሚናገሩ ያወሳል፡፡

በኢንዲያና ጆንስ የተሰራውን "የጠፋው ታቦት ዘራፊዎች" (Raiders of the Lost Ark) የተባለውን ፊልም በቅርቡ ስላየሁ ይህ ከጠፋ ወደ3ሺ ዓመታት ገደማ ይሆነዋል የተባለው የቃል ኪዳኑ ታቦት ምናልባት በዚህች ከተማ ይኖር እንደሆነ ለማወቅ ጓጓሁ፡፡ ይህን ሃሣብ በማውጣትና በማውረድ ላይ እያለሁ ነበር የአውሮፕላኑ አብራሪ አክሱም መድረሳችንን ያስታወቀን፡፡

## ቤተመንግስቶች፥ መካነ መቃብሮችና ሐውልቶች

እንደደረስን ሥራ ጀመርን፡፡ ከአውሮፕላን ስንወርድ የተቀበለን ሙሉ ልብስ ከነሠደርያው የለበሰ ብርሃነ መስቀል ዘለለው የተባለ የባህል ሚኒስቴር ባልደረባ ነበር፡፡ ስለኛ መምጣት ከአዲስ አበባ በሬዲዮ እንደተነገረውና እንዳስተርጓሚና እንዳስጎብኚም እንዲያገለግለን መታዘዙን ገለፀልን፡፡ ሥራውም አክሱም የሚገኙትን ታሪካዊ ቅርሶች መጠበቅ እንደሆነና የ1974ቱ አብዮት ከፈነዳ በኋላ የብሪታኒያ አርኪዎሎጂስቶች ሥራ ተቋርጦ ከአገር እስከወጡበት ጊዜ ድረስ አብረዋቸው ይሠራ እንደነበር አወጋን፡፡

የቀረበልን አረንጓዴ ላንድሮቨር ውስጥ ገብተን ጉዞ እንደጀመርን ስለመጣንበት ጉዳይና ስለመጉብኘት ስለአቀድናቸው ቦታዎች ገለጽኩለት፡፡ በማያያዝም አክሱም ውስጥ አለ ስለሚባለው የቃል ኪዳኑ ታቦት ጉዳይ ጠየኩት፣

"ታቦቱ እዚህ አለ ብለህ ታምናለህ?"

"አዎን፣ እርግጠኛ ነኝ፡፡"

"በትክክል የት ነው ያለው?"

"ከተማው መሃል በሚገኘው ቤተመቅደስ ውስጥ ነው የተቀመጠው፡፡"

"ቤተመቅደሱ በጣም አርጅቷል?"

"አላረጀም፡፡ በ1965 ገደማ ንጉሡ ባሠሩት አዲስ ሕንፃ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ከዚያ በፊት ታቦቱ ለብዙ መቶ ዓመታት፣ በጽዮን ማርያም ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ተቀምጦ ነበር . . ." አለና ብርሃነ መስቀል ለአፍታ ያህል ዝም አለ፡፡ በመቀጠልም "ኃይለሥላሴ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውት ነበር፡፡ በነገራችን ላይ እርሣቸውም ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ልጅ፣ ከምኒልክ ጀምሮ ሲቆጠር 255ኛው ንጉስ ናቸው፡፡ ታቦቱን ወደአገራችን ያመጣውም ቀዳማዊ ምኒልክ ነበር. . .፡፡

ወዲያውኑ ሄጄ ቤተመቅደሱን ለማየት ብፈልግም ብርሃነ መስቀል "ወደታቦቱ ግን ምንም የሚያስቸኩል ነገር እንደሌለ ነገረኝ፡፡ "ወደታቦቱ ግን ምንም የሚያስቸኩል ነገር እንደሌለ ነገረኝ፡፡ ያረፈበት ቦታ ቅዱስ ነው፡፡ እንደሆነ የሚያቀርብህ የለም፡፡ ያረፈበት ቦታ ቅዱስ ነው፡፡ የተቀደሰ መነኩሴዎቹና የአክሱም ነዋሪዎች ስለሚጠብቁትም ይህን የተቀደሰ ቦታ የሚደፍር ሰው ካገኙ ከመግደል አይመለሱም፡፡ ዘለቄ መግባት የሚፈቀድለት አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡ እሳቸውም ጠባቂው መነኩሴ ናቸው፡፡ ወደበኋላ ልናገኛቸው እንሞክራለን፡፡ ,መጀመሪያ ግን የንግሥተ ሳባ ቤተመንግሥትን እንጎብኝ፡፡"

ከዚያም በኮረኮንቻማና አቧራማ መንገድ ላይ የደቡብ ምስራቅ አቅጣጫን ይዘን ጉዞአችንን ጀመርን፡፡ ከመሐል አክሱም አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል ያህል ርቀን እንደተጓዝን፣ ብርሃነ መስቀል አሻገር በቅርበት ወደሚታዩት ኮረብታዎች እያመላከተ፦ "ከዚህ ውጪ ያለው የሕወሐት ነው፡፡ ስለዚህ መሄድ አንችልም... ያሳዝናል፡፡ ብዙ የሚታዩ ነገሮች ነበሩ... ለአክሱም ሐውልቶች መሥርያ የሚሆኑ ድንጋዮች ይወጡበት የነበረ ሥፍራ በዚያ አለ፡፡ እንዲያውም የቤት አንበሳ ሐውልት አለ፤ ቆንጆና ጥንታዊም ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ክርስትና ከመምጣቱ በፊት የነበሩ ናቸው፡፡"

ከመንገዱ ወጥተን በስተሰሜን አቅጣጫ ወዳለው ገላጣ መስክ እንደደረስን የሕንፃ ፍርስራሽ አየን፡፡ ብርሃነ መስቀል "ይህ የንግሥተ ሳባ ቤተ መንግሥት ነበር፡፡ እኛ ማከዳ ነው የምንላት፡፡ መናገሻ ከተማዋም አክሱም ነበር፡፡ መቼም እናንተ የውጪ ሰዎች ኢትዮጵያዊት መሆኗን አታ ምኑም፡፡ ቢያም ሆኖ ግን እኛ ኢትዮጵያዊት መሆንዋን በጽኑ እናምናለን አለ፡፡

"ይህን የምትለኝን አፈታሪክ ለማረጋገጥ ቁፋሮ ተካሂዷል?"



"አዎን፡፡ በ1960ዎቹ በኢትዮጵያ አርኪዎሎጅ ጥናት ተቋም ቁፋሮ ተካሂዷል፡፡ ሆኖም የተገኙት ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት በጣም ረጅም ዕድሜ ስለሌላቸው የንግሥተ ሳባ መኖሪያ ላይሆን ይችላል የሚል አስተያየት ነው ያለው፡፡"

በአካባቢው የአርኪዎሎጅ ተመራማሪዎች ቆፍረው ያወጡት የአንድ ትልቅ ሕንፃ ፍርስራሽ ይታያል፡፡ ህንፃው ትልቅና በጥሩ ሁኔታ የተገነባ ሲሆን፣ ግድግዳዎቹም በሚገባ የተለሰኑ ናቸው፡፡ የህንፃው መሠረትም ጠለቅ ያለና የፍሳሽ ማስተላለፊያ መስመሮች የተዘረጉበት ነበር፡፡ ሌላ ጠፍጣፋ ድንጋይ የተነጠፈበት ወለልም አየን፡፡ ይህም ዙፋኑ የተቀመጠበት ክፍል እንደነበር ብርሃነ መስቀል ይናገራል፡፡ የደረጃዎች መኖር ደግሞ ምናልባት ተጨማሪ ፎቅ እንደነበር ይጠቁማል፡፡ የተዋቡና የተራቀቁ የገላ መታጠቢያዎችና በመልካም ሁኔታ የሚገኙ ከሸክላ የተሠሩ ማብሰያዎችም ይታያሉ፡፡ ባሻገር ደግሞ ከአለት ደንጊያ የተጠረቡ ቁመታቸው ወደ አምስት ሜትር የሚጠጋ ትክል ድንጋይ መሰል ቅርጾች አሉ፡፡ ገሚሶቹ ወድቀው ተሰብረዋል፡፡ ሌሎቹ ቆመዋል፡፡ ብርሃነ መስቀል እንደሚለው ከሆነ የከተማዋ ነዋሪዎች እነዚህ ከአናታቸው ሾጠጥ ተደርገው የተቀረጹ ረጃጅም ግዕዘንግ ድንጋዮችን የንግሥተ ሳባ መካነ መቃብር ምልክቶች ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ በዚህ ሥፍራ ምንም ዓይነት ቁፋሮ አልተካሄደም፡፡ መሬቱም ለአክሱሙ ጠር ሠፈር እህል ለሚያመርቱ ገበሬዎች ሙሉ በሙሉ ተሰጥቷል፡፡ እዚያው ሳለን ሁለት ወጣት ገበሬዎች በሬዎቻቸውን አጥምደው ማረስ ጀመሩ፡፡ ዙሪያቸው ስላለው ታሪክ ደንታ ሳይኖራቸውና የኛም መኖር ስሜት ሳይሰጣቸው መሬቱን ማረስም ቀጠሉ፡፡

የምንፈልጋቸውን አካባቢዎች ፎቶግራፍ ካነሳንና ማስታወሻ ከወሰድን በኋላ በከተማይቱ በስተሰሜን ምስራቅ ወደሚገኝ ጥንታዊ ቤተ መንግሥት አመራን፡፡ ቤተመንግሥቱ የሚገኘው የኩረብታ አናት ላይ ስለሆነ ከበታቹ ያለውን አካባቢ በደንብ ማየት ይቻላል፡፡ ስድሣ ሜትር በስድሣ ያክል የሚሆነው የዚህ ህንፃ ግድግዳዎች ቢፈራርሱም በአራቱ ማዕዘናት የድንጋይ መሠረቶች ላይ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ መነኩሴው ከስማስ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጽሑፉ የገለጸውም ይህን ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምሽግ ከሚመስለው ከዚህ ሕንጻ በታች ብርሃነ መስቀል እየመራን በደረጃዎቹ ወደምድር ቤቱ ሄድን፡፡ ቃኛ ያሉት ክፍሎችና ግምጃ ቤቶች ጣሪያዎችና ግድግዳዎች ከጥርብ አለት የተሠሩና ያለምንም ማያያዣ የተገጣጠሙ ናቸው፡፡ እንደአገሬዎቹ አፈታሪክ እነዚህ ቀዝቃዛና ጨለማ ክፍሎች የንጉሥ ካሌብ (514 - 542 ድ.ል.ክ) እና የልጁ የገብረ መስቀል ግምጃ ቤቶች የነበሩ ናቸው፡፡ ከድንጋይ የተጠረቡ ሳጥን መሰል ቅርጾች አሏቸው፡፡ ለንገሥታቱ ወርቅና ጌጣጌጥ ማስቀመጫ የተሠሩ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ ገና ተቆፍረው ያልወጡ ክፍሎችም በወፍራም የአለት ግድግዳ ተዘግተዋል፡፡

ከኩረብታው ወርደን ወደአክሱም ስንጓዝ፣ አንድ በአለት ደንጊያ የተከበበ ጥልቅ የውሃ ማከማቻ ኩሬ ተመለከትን፡፡ ይህ ማይ ሹም የሚባል ቦታ የንግሥተ ሳባ የገላ መታጠቢያና መዋኛ እንደነበርና በኋላ ግን በየዓመቱ የጥምቀት በዓል የሚከበርበት የመጠመቂያ ቦታ መሆኑን አስጎብኚያችን ነገረን፡፡

ቀጥሉ የተመለከትነው የአክሱም የአርኪዎሎጂ ጥናት መታወቂያ የሆነውን የትክል ድንጋዮችን ክልል ነው፡፡ ከነዚህም ትልቁና አንድ የሆነውን የትክል ድንጋዮችን ክልል ነው፡፡ ከነዚህም ትልቁና አንድ ወጥ ከሆነ ድንጋይ የተጠረበው ሃውልት ከወደቀ ከአንድ ሺህ ዓመታት በላይ እንደሆነው ይገመታል፡፡ ቆሞ በነበረበት ጊዜም በአካባቢው ጎላ ብሎ ሳይታይ አልቀረም፡፡ የዚህ የወደቀው ትክል ድንጋይ ቁመት ወደ 33ሜትር ሲሆን፣ ክብደቱም ከ500ቶን ይበልጣል፡፡ በጥንታዊው ዓለም ውስጥ ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ ተወዳዳሪ የሌለው ትክል ድንጋይ መሆኑም ይታመናል፡፡ በከፍተኛ ጥንቃቄና ድካም የተጠረበው ይህ ትክል ድንጋይ የ13 ፎቆች ከፍታ ያለው ሆኖ በላዩ መስኮቶችና ሌሎችም ቅርጾች አሉት፡፡ ከመሠረቱ በላይም የመግቢያ በር ከነቁልፎቹ ተቀርፀውለታል፡፡

ብርሃን መስቀል እንደነገረን በ1935-1941 የኢጣልያ ወረራ ወቅት መሶሎኒ አንዱን ሐውልት በከፍተኛ ድካም አጓጉዞ በመውሰድ ዛሬ ሮም ከተማ ላይ ተክሎት ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥትም ሃውልቱ እንዲመለስለት እየጉተጎተ መሆኑን አስጉብኚያችን ገለፀልን፡፡ ጉብኝታችንን በመቀጠል በርካታ የቆሙ የድንጋይ ሐውልቶችን ተመለከትን፡፡ ከሰሐራ በታች በአፍሪቃ ውስጥ እንኳንስ እነዚህን የመሰሉ ሐውልቶች ቀርቶ በትንሹ እንኳን የሚመሳሰሏቸው ተሠርተው አያውቁም፡፡

## የታቦቱ ቤተ መቅደስ

ከመንገዱ ባሻገር፣ ከሐውልቶቹ ፊትለፊት በግንብ በታጠረው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሁለት አብያተክርስቲያናት ይታያሉ፡፡ አንዱ ጥንታዊ፥ ሌላኛው ዘመናዊ ቢሆኑም፥ ሁለቱም የጽዮን ማርያም ናቸው፡፡ አዲሱ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በ1960ዎቹ የተሠራ ሲሆን፣ ጥንታዊው ግን በንጉሥ ፋሲለደስ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ የተሠራ ነው፡፡ ንጉስ ፋሲለደስ ዋና ከተማቸውን በሌላ ስፍራ ያደረጉ ቢሆኑም ከሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ እንደነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ ሥርዓተ ንግሥናቸውን የፈጸሙት በአክሱም ጽዮን ነበር፡፡

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተሠራው ዘመናዊው "ካቴድራል" የሚስብና የሚያምር አይደለም፡፡ በመሆኑም ትኩረታችንን ፋሲለደስ ወዳሠሩት ቤተክርስቲያን አደረግን፡፡ ሕንጻው፥ ቤተመንግሥትንና ቤተክርስቲያንን አጣምሮ የያዘ ይመስላል፡፡ይህም በጥንታዊት ኢትዮጵያ



የቀሳውስትና የጦር መሪዎች ሚና ብዙውን ጊዜ እንደሚደበላለቅ ያሳየናል፡፡

ውስጥ እንደገባሁ በደብዛዛው ብርሃን ሕንጻው ግድግዳዎች ላይ ለዓይን የሚስቡ በርካታ ሥዕሎችን አየሁ፡፡ ከነዚህም መካከል የቅድስት ድንግል ማርያምን ታሪክና ተአምራት፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥቅለትና ትንሣኤ፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የዜማ ደራሲና ሊቅ የቅዱስ ያሬድ ታሪክ ይገኙባቸዋል፡፡ በተለይ የቅዱስ ያሬድ ሥዕል ንጉሥ ገብረ መስቀል በቅዱስ ያሬድ ዝማሬ ከመመሰጡ የተነሳ ጦሩ ከእጁ አምልጦ የቅዱስ ያሬድን እግር ሲወጋው፣ ሁለቱም ሰዎች በጸናጽልና በከበሮ በታጀበው ዜማ ተመስጠው ሁኔታውን ፈጽሞ አለማስተዋላቸውን ያሳያል፡፡

ከዚህ ጥንታዊ ቤተክርስቲያን ጥቂት ራቅ ብሎ የቀድሞው ቤተክርስቲያን ፍርስራሽና መሠረት ይታያል፡፡ ብርሃን መስቀል እንዳስረዳን ይህ የመጀመሪያው የጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን ሲሆን፣ የተሠራውም በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አክሱም ክርስትናን በተቀበለችበት ጊዜ ነበር፡፡ ሆኖም ከአንድ ሺ ሁለት መቶ ዓመታት በኋላ በ1535 ከሐረር የተነሣው የአህመድ ግራኝ ወራሪ ጦር ቤተክርስቲያኑን አወደመው፡፡ በዚያን ወቅትም የክርስትና እምነት ከኢትዮጵያ ወደመጥፋቱ ተቃርቦ ነበር፡፡

የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን ከመውደሙ ጥቂት ቀደም ብሎ ግን ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ የተባለ ፖርቱጋላዊ መነኩሴ ጎብኝቶት የሚከተለውን ጽፏል፡፡

> ቤተክርስቲያኑ በጣም ትልቅ ሲሆን፣ ጣሪያቸው የተዋበና በመጋረጃ የተሸፈኑ አምስት የፀሎት አዳራሾች አሉት፡፡ ጣሪያዎቹና ግድግዳዎቹም ባማረ ቀለም የተዋቡ ናቸው፡፡ የኛ ቤተክርስቲያኖችን አይነት የመዘመሪያ ቦታም አለው ... ይህ ታላቅ ቤተክርስቲያን ዙሪያው ሠፊና ወለሉም በጥርብ ድንጋይ የተሸፈነ ነው፡፡ ዙሪያውንም በሁለት አጥሮች ታጥሯል፡፡

የዚህ ቤተክርስቲያን ሥራ የተጀመረው በ372 ድ.ል.ክ መሆኑን ብርሃን መስቀል በትክክል ተናግሯል፡፡ ይህም ቤተ ክርስቲያኒቱን ከሰሃራ በታች በአፍሪቃ የመጀመሪያዋ ያደርጋታል፡፡ ይህ አምስት ክፍል የጸሎት አዳራሽ የያዘ ትልቅ ካቴድራል ተመርቆ ከተከፈተ ጀምሮ በኢትዮጵያ ትልቁ ቅዱስ ሥፍራ ሁኖ ቆይቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ቤተክርስቲያኑ የተሠራው የቃል ኪዳኑን ታቦት ለማስቀመጥ ስለሆነ ነው፡፡ አፈ ታሪኩም እውነትነት ካለው ታቦቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቷል፡፡ በመሆኑም የአክሱም መንግስት የክርስትናን እምነት እንደተቀበለ ታቦቱን ከአዲሱ ሃይማኖት ጋር ተቀብሎታል ማለት ነው፡፡

በ1520 አካባቢ አልቫሬዝ የቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን በጉበኘበት ወቅት የቃል ኪዳኑ ታቦት በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ነበር ማለት ነው፡፡ ሆኖም ብዙ ሳይቆይ በ1530ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ

የአህመድ ግራኝ ወራሪ ጦር ወደከተማዋ በተቃረበ ጊዜ ለታቦቱ ደህንነት ሲባል፣ ወዳልታወቀ ቦታ በመወሰዱ ከዝርፊያና ከውድመት ሊተርፍ ቻለ፡፡

ከመቶ ዓመት በኋላ ግን ሰላም ሲሰፍን ከቀድሞው ቤተ መቅደስ ፍራሽ አጠገብ አጼ ፋሲል ባሠሩት ሁለተኛው ቤተ መቅደስ ውስጥ በክብር መጥቶ ገባ፡፡ እስከ 1965 ድረስም እዚሁ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከቆየ በኋላ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወዳሠሩትና ለጥበቃ ወደሚያመቸው ቤተክርስቲያን ተዛወረ፡፡

በዚህ አጼ ኃይለሥላሴ ባሠሩት ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ነበር ከታቦቱ ጠባቂ መነኩሴ ጋር የተነጋገርኩትና ታቦቱ "ኃያል" እንደሆነ ያስጠነቀቁኝ፡፡

"ኃያል ነው ሲሉ ምን ማለትዎ ነው" ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡

በዚህን ጊዜ የመነኩሴው ሰውነት ልውጥውጥ አለ፡፡ ዝምታም ሠፈነ፡፡ ከዚያም ፈገግ ብለው፣

"ሐውልቶቹን አይተሃል?" ሲሉ ጠየቁኝ፡፡

"አዎን፣ አይቻቸዋለሁ፡፡"

"እንዴት እንደዛ ቀጥ ብለው መቆም የቻሉ ይመስልሃል?"

እንደማላውቅ ነገርኳቸው፡፡

"በታቦቱ ኃይል ነው፤ በታቦቱና በሰማያዊ እሳት፡፡ ሰዎች ይህን ብቻቸውን ከቶውኑ ሊሠሩ ባልቻሉም ነበር፡፡"

ወደአዲስ አበባ ስመለስ መነኩሴው የነገሩኝን ከታሪክ ጋር ለማገናዘብ ጥቂት ምርምር አደረግሁ፡፡

ንግሥት ሳባ እውን ኢትዮጵያዊት ነበረች? በርግጥ ንግሥተ ሳባ ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት ወደእሥራኤል በመሄድ ከንጉሥ ሰሎሞን ፀንሳ ምኒልክን ወልዳለች? ልጅዋ ምኒልክ ካደገ በኋላ ወደኢየሩሳሌም በመጓዝ በአባቱ ቤተመንግሥት ለአንድ ዓመት ያህል ቆይቶ ሲመለስ ታቦተ ሕጉን ይዞ መጥቷል? የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችን ማሰላሰል ጀመርሁ፡፡



# ምዕራፍ ሁለት

## ባዶ ተስፋ

የቃል ኪዳኑን ታቦት በተመለከተ ቀደም ሲል ያነሳኋቸውን ጥያቄዎች አዲስ አበባ ባነሳ ማንም የሚወድልኝ እንደሌለ ተገነዘብሁ፡፡ በ1983 አዲስ አበባ ውስጥ ጥርጣሬ፣ ፍርሃትና ጥላቻ እንደነገሠ ነበር፡፡ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ከወደቀ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላም አብዮታዊ መፈክሮች ይስተጋባሉ፡፡

በዚህ አስፈሪ ድባብ ውስጥ ነበር ታቦቱ ከመጨረሻው የኢትዮጵያ ንጉስና ከሰሎሞናዊ ሥርወ መንግስት ጋር ግንኙነት ያለውን ቁርኝት ለማወቅ የመንደርደሪያ ጥናቴን የጀመርኩት፡፡ በዚህ መካከል አንድ ጓደኛዬ የንጉሡን የዘር ግንድ በተመለከተ ተሻሽሎ የወጣውን የ1955 ሕገ መንግሥት እንዳነበው ሰጠኝ፡፡ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 2 ውስጥ ንጉሡ ሥዩመ እግዚአብሔር እንደሆኑና ሥርወ መንግሥታቸው ከቀዳማዊ ምኒልክ፣ ከንግሥተ ሳባና ከንጉሥ ሰሎሞን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑን አነበብኩ፡፡ ከዚህ አኳያ ብርሃነ መስቀል ስለንጉሡ የዘር ግንድ የነገረኝን በማስታወስ እውነት መሆኑን አረጋገጥኩኝ፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ካነጋገርኳቸው ኢትዮጵያውያን መካከልም የዚህን አባባል እውነተኛነት የተጠራጠሩት በጣም ጥቂት ነበሩ፡፡ ፕሬዝዳንት መንግሥቱ ኃይለማርያም የአፄ ኃይለሥላሴን ከንጉሥ ሰሎሞን የተወረሰ የጣት ቀለበት አውልቀው ጣታቸው ላይ ማድረጋቸውንና ይህንንም ያደረጉት በቀለበቱ አማካይነት እንደ ንጉሡ ግርማ ሞገስንና ምትሃታዊ ኃይልን ለመቀዳጀት ነው ተብሎ ይወራ ነበር፡፡

የሚናፈሱት ወሬዎች የሚስቡ ቢሆኑም፣ ለኔ ጥያቄዎች ግን መልሶች አልሆኑም፡፡ በወቅቱ ያገኘኋቸው ኢትዮጵያውያን ስለታቦቱም ሆነ ስለቀድሞው ንጉስ ሳነሳባቸው በከፍተኛ ፍራቻ ተውጠው ዝምታን ይመርጡ ነበር፡፡ ከአብዮቱ በፊት ስለነበሩት ማናቸውም ጉዳዮች ለመነጋገር ፈቃደኞች አልነበሩም፡፡ በዚህ መካከል ለመንግስት በማዘጋጀው መጽሐፍ ተባባሪ እንዲሆኑኝ ጠይቄያቸው የነገሩትና ስለኢትዮጵያ የጠለቀ ዕውቀት ያላቸው የሥራ ባልደረባዬ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ከእንግሊዝ ወደአዲስ አበባ መጡ፡፡

ስለሴቶች መብት ተሟጋች የነበሩት የታዋቂዋ እንግሊዛዊት የኤምሊን ፓንክረስት የልጅ ልጅና በአምስቱ ዓመት የጣሊያን [illegible] ወቅት ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር በቆራጥነት የተዋጉት የሲልቪያ ፓንክረስት ልጅ ናቸው፡፡ ሪቻርድ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ [illegible] መንግስት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ታዋቂውን የኢትዮጵያ [illegible] ምርምር ኢንስቲትዩት መስርተዋል፡፡ [illegible] ከነቤተሰቦቻቸው ወደአገራቸው [illegible] የመጡት ስለመጽሐፋችን [illegible] ጥያቄ መሠረት ነበር፡፡

ስለኢትዮጵያ ታሪክ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ስላላቸው፣ በመጀመርያ የጠየቅኋቸው ኢትዮጵያውያን እኛ ዘንድ አለ ስለሚሉት ታቦት ጉዳይና አክሱም ውስጥ ስለመኖሩ የሚያውቁት ነገር እንዳለ ነበር።

ስለንጉሥ ሰሎሞንና ንግሥተ ሳባ በቅድስቲቱ ከተማ የሰማሁት ታሪክ ኢትዮጵያ ውስጥ ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፍ የቆየ ታሪክ መሆኑን አረጋገጡልኝ። በቃልና በጽሑፍ በተለያየ መልክ ሲቀርብ የኖረ ታሪክ ሲሆን፣ በተለይ ደግሞ ስለዚህ ጉዳይ “ክብረ ነገሥት” የተባለው በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈ ጽሑፍ ረጅም ዕድሜ ካላቸው ውስጥ እንደሚጠቀስ ገለፁልኝ። ይህንም ብዙ ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ እውነት ነው ብለው የሚቀበሉት ነው። ነገር ግን በታሪክ ባለሙያነታቸው እሳቸው ይህን አይቀበሉም። ምክንያቱም በሳቸው እምነት የንግሥተ ሳባ መኖርያ አረቢያ እንጂ ኢትዮጵያ አይደለችም። ሆኖም ክብረ ነገሥት ውስጥ የተጠቀሱ አንዳንድ እውነት የሚመስሉ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። በርግጥ በኢትዮጵያና በኢየሩሳሌም መካከል እስከ ንጉስ ሰሎሞን ድረስ ባይዘልቁም ግንኙነቶች ስለመኖራቸው የተመዘገቡ ማስረጃዎች አሉ። በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያውያንን ባሕል ስንመለከት፣ ጠንካራ የአይሁዶች ተጽዕኖ ይታይበታል። በአገሪቱ ውስጥ የአይሁዶች ወይም የፈላሻዎች በሰሜን ተራሮች፣ ከአክሱም በስተደቡብና በጣና ሐይቅ አካባቢ ወዘተ መገኘት ይህን ያጉላዋል። ብዙ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችም ከጉረቤቶቻቸው ከፈላሻዎች የወረሷቸው በርካታ ባህሎችና ልምዶችም አሉ። ለማስረጃ ያህል ግርዘትና በኦሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ስለተከለከሉና ስለሚፈቀዱ ምግቦች፣ እንዲሁም ቅዳሜን (በተለይ ባንዳንድ ገጠር አካባቢዎች) እንደሰንበት ማክበር ያሉት የአይሁድ ባሕሎች በአካባቢው የሚታዩ ተጨባጭ ማስረጃዎች ናቸው።

ስለፈላሻዎች በኢትዮጵያ መኖር አስቀድሜ አውቅ ስለነበር ለመጎብኘት ፈቃድ ጠይቄ እየተጠባበቅኩ ነበር። በዚያውም ጣና ሐይቅንና አካባቢውን፣ ጎንደርንና የሰሜን ተራሮችን ለመጎብኘት አስቤአለሁ። ስለነዚህ ‘የኢትዮጵያ ጥቁር አይሁዶች” ስለሚባሉት ሰዎች ምንም ነገር አላውቅም። ስለዚህም ሪቻርድን ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጡኝ ጠየቅሁዋቸው።

ሪቻርድ፣ ፈላሻዎቹ በቁመናቸውና በአለባበሳቸው ከደገኞቹ ኢትዮጵያውያን እንደማይለዩ ገለፁልኝ። የራሳቸው አፍ መፍቻ ቋንቋ ያላቸው ሲሆኑ፣ የአገው ቋንቋ ዘዬም አለበት። ዳሩ ግን በአሁኑ ወቅት በፍጥነት በአማርኛ ቋንቋ እየተተካ ይገኛል። ፈላሻዎች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን የሚለዩት በሃይማኖታቸው ነው። ይኸውም እጅግ ጥንታዊ የሆነ የአይሁድ ሥርዓትና ባህል ሲሆን፣ በየትኛውም የአይሁድ ሕዝብ ዘንድም ፈጽሞ የማይታወቅ ነው። በዚህም የተነሣ “የጠፋው የእስራኤል ነገድ” እስከመባል ደርሰዋል። ባለፉት አስር ዓመታት በኢየሩሳሌም ያሉት አሽከናዚና ሴፋርዲ ዋና ረቢ በይፋ



የፈላሻዎችን አይሁድነት በማረጋገጥ ወደእስራኤል እንዲመለሱና የእስራኤል ዜግነትን ለማግኘት እንዲችሉ አድርገዋል።

ፕሮፌሰሩን፣ ፈላሻዎች በመጀመሪያ ከየት እንደመጡና እንዴትስ ሦስት ሺህ ኪሎሜትር አቋርጠው መሐል ኢትዮጵያ ሊደርሱ እንደቻሉ? ጠየቅኳቸው።

ሪቻርድ ለነዚህ ጥያቄዎች በቀላሉ መልሶች ሊገኙ እንደማይችሉ ገለፁልኝ። ብዙ ምሁራን የሚያምኑት፣ በርካታ አይሁዶች ወደኢትዮጵያ ምድር የገቡት ከደቡብ ምዕራብ ዓረቢያ በ1ኛውና በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን፣ በደረሱበት ቦታም ከነዋሪዎቹ የጥቂቶቹን እምነት በመቀየር የዛሬዎቹን ፈላሻዎች እንዳስገኙ ነው። በተጨማሪም የሮማውያንን ወረራ በመሸሽ ከፍተኛ የአይሁድ ማህበረሰብ በየመን መከማቸቱ ይታወቃል። ከነዚህም አይሁዶች መካከል ለሃይማኖትና ለንግድ ተግባር ቀይ ባህርን በባብ ኤል መንደብ ባህረሰላጤ በኩል ተሻግረው ወደኢትዮጵያ ገብተው ይሆናል የሚል ግምት አለ። ሆኖም ፕሮፌሰሩ ስለዚህ ጉዳይ አሳማኝ ታሪካዊ ማስረጃ ስለመኖሩ አያውቁም።

ፈላሻዎችስ ስለራሳቸው ምን ይላሉ?

ሪቻርድ ፈገግ ብለው፣ “ከንጉሥ ሰሎሞን የተወለድን ነን ነው የሚሉት። አፈታሪካቸው በመሠረቱ ከክርስቲያኖቹ የተለየ አይደለም። ሆኖም ዝርዝር ያለ ነው። ባልሳሳት በነርሱ አባባል ንጉሥ ሰሎሞን የወለደው ከንግስተ ሳባ ብቻ ሳይሆን፣ ከገረዷም ጭምር ነበር። ከገረዷ የተወለደው ልጅ ነው የፈላሻዎችን ሥርወ መንግሥት የመሠረተው። በኢትዮጵያ ዛሬ ያሉት አይሁዶች ሁሉ ከእስራኤል ሰዎች የበኩር ልጅ የተውጣጡና ከንጉስ ምኒልክና ከታቦቱ ጋር አብረው የመጡ ናቸው ይላሉ።”

“ይህ አፈታሪክ እውነት ሊሆን ይችላል? ማለት ታቦቱን ከኢየሩሳሌም ከንጉስ ሰሎሞን ቤተመቅደስ ሰርቀው አክሱም አምጥተውት ይሆን?”

“አይመስለኝም፣ በፍፁም ሊሆን አይችልም። ይህ ነገር ተፈጸመ በተባለበት ዘመን አክሱም የሚባል ከተማ አልነበረም። ...ልብ አድርግ፣ ሰሎሞን የሞተው፣ በትክክል ጊዜውን ባላውቅም በ940 ወይም በ930 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው። ታዲያ ምኒልክ ልጁ ከሆነ፣ ታቦቱን ወደኢትዮጵያ ያመጣው በነዚህ ዓመታት አካባቢ፣ ምናልባትም ከአስርና ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት ሲሆን፣ ያኔ አክሱም አልተቆረቆረችም። እየሁ፣ አክሱም ከ3ኛው መቶ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በፊት አልተመሠረተችም። ምናልባትም ከ2ኛው መቶ ዓመት በፊት። ይህም ማለት ከተባለው የታቦት ስርቆት ሰባት ወይም ስምንት መቶ ዓመታት ገደማ በኋላ ማለት ነው።”

“በዚህ ዓይነት ጠቅላላው ታሪክ ዋጋ አጣ ማለት ነዋ?!”

“አዎን፣ ሆኖም ታቦቱ ወደዚህች [illegible]ር መጥቶ ሌላ ቦታ አርፎ ሊሆን ይችላል። በኋላ ግን ሲወርድ ሲወራረድ ታሪኩ ከአክሱም ጋር

ሳይደበላለቅ አልቀረም፡፡ በአፈ.ታሪኩ ውስጥ በርካታ የሚቃረኑና ትክክል የልሆኑ ነገሮች-ስለአሉበት ማንም የታሪክ ተመራማሪም ሆነ የአርኪዎሎጂ ተመራማሪ ይህንን ታሪክ ተቀብሎ ምርምር ለማድረግ አይፈልግም፡፡ ቢሆንም ፈላሻዎች ስለራሣቸው የሚናገሯቸው ነገሮች በሙሉ ፍጹም ልብወለድ ተደርገው መወሰድ አይኖርባቸውም፡፡ እንዲያውም ምንጫቸውን አስመልክቶ ተጨማሪ ምርምር መደረግ ይኖርበታል፡፡"

"ለምሳሌ በምን ላይ?"

"ቀደም ብዬ የጠቀስኩልህ የፈላሻ ሥርወ መንግሥት በ15ኛው እና በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ገደማ እንደነበረና በአገሪቱ ውስጥ እንደ አንድ ኃይል ይታይ እንደነበር ነው፡፡ አልፎ አልፎም ከክርስቲያን ገዢዎች ጋር ተዋግተው አሸንፈዋል፡፡ ሆኖም ከጊዜ ወደጊዜ ኃይላቸው እየተዳከመ በመሄዱ ከ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቁጥራቸው በእጅጉ ተመናምኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያሉት ቁጥራቸው ከ20ሺህ አይበልጥም፡፡ ብዙዎቹም ወደእስራኤል ለመሄድ እየሞከሩ ነው፡፡"

ሪቻርድና እኔ ለሦስት ቀናት አብረን ቆየን፡፡ ከቆይታችንም የኢትዮጵያን ታሪክና ባህል በተመለከተ ብዙ ቁምነገሮችን ለመገብየት ቻልኩ፡፡ ሥራችንን እንዳበቃን ሪቻርድ ወደለንደን ተመለሱ፡፡ እኔም ከካሮልና ከደንካን ጋር ወደጣና ሐይቅ፣ ጉንደርና ስሜን ተራሮች ለመጓዝ ተዘጋጀሁ፡፡

## ጽላቶች – የቃል ኪዳኑ ታቦት አምሳያዎች

መንግሥት ባቀረበልን የተጐሳቆለ ቶዮታ ላንድክሩዘር ጉዞአችንን ወደሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በማድረግ፥ በባሀር ዛፍ የተሸፈነውን የእንጦጦ ተራራ አቋርጠን ወደሰሜን ምዕራብ ከተጓዝን በኋላ በደብረሊባኖስ ጥቂት ቆይታ በማድረግ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሠራውን የኢትዮጵያዊውን የአቡነ ተክለሃይማኖትን ገዳም ጐበኘን፡፡ በዚያም ቦታ የእኚህን ጻድቅ የሕይወት ዘመን ሥራና ተአምራት ለመዘከር የተሰበሰቡ ብዙ ምዕመናን ነበሩ፡፡

ከዚያም ወደሰሜን በመቀጠል፥ የአባይ ሸለቆን በማቋረጥ ባህር ዳር ደረስን፡፡ በዚህች ከተማ ለበርካታ ቀናት ቆይታ ከማድረጋችንም ሌላ በቀረበልን የዲዝል ሞተር ጀልባ ወደሃያ የሚሆኑ ገዳማትንና ደሴቶችን ጐበኘን፡፡

እነዚህ ገዳማት ከሌላው ክፍል "የተገለሉ" በመሆናቸው ብዙ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ ችግር ሲከሰት የቅርሳ ቅርስና የንብረት መደበቂያ ቦታ በመሆን አገልግለዋል፡፡ ዋናው አገልግሎታቸው ግን ለመነኮሳቱ የመኖሪያ ቦታ መሆናቸው ነው፡፡ እያንዳንዱ ደሴት የመነኮሳት በዓትና የራሱ ቤተክርስቲያን አለው፡፡ ቤተክርስቲያኖቹ ክብና ጥንታውያን ናቸው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ቤተክርስቲያኑን የውጪ ግድግዳ ተከትሎ የሚዞር ገሪገራ አለ፡፡ ወደውስጥ ሲዘልቁ ደግሞ



የመጀመሪያው ክፍል በሥዕል የተጌጠው "ቅኔ ማኅሌት" ነው፡፡ ሁለተኛው የውስጥ ክፍል ደግሞ "ቅድስት" ሲሆን፥ ሦስተኛውና የመጨረሻው የውስጥ ክፍል "ቅድስተ ቅዱሳን" (መቅደስ) ይባላል፡፡

ብዙ የኢትዮጵያ አብያተክርስቲያናትን ተዘዋውሬ ጐብኝቻለሁ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የመቅደስ ትርጉም በአእምሮዬ የተቀረጸው ግን በጣና ሐይቅ ነበር፡፡ እንደተረዳሁት ወደዚህ የተቀደሰ ነገር ማኖሪያ መቅደስ ውስጥ መግባት የሚችሉት አገልጋይ ካህናት ብቻ ናቸው፡፡ ክብራን ገብርኤል በተባለ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተሠራ ገዳም ቆይታዬ ወቅት፥ አስተርጓሚዬን "ይህ የተቀደሰ ነገር" የተባለው ምን እንደሆነ ቁሱን እንዲጠይቃቸው ነገርኩት፡፡ "ታቦት ይባላል" አሉኝ የዘጠና ዓመቱ አባ ኃይለማርያም፡፡ ቃሉን የማውቀው መሰለኝ፥ ወዲያውኑም አክሱም ላይ እንደሰማሁት ትዝ አለኝ፡፡ ይኸውም ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጠባቂ መነኩሴ ጋር በተነጋገርኩበት ጊዜ ነበር፡፡

"ታቦት ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?" አስተርጓሚዬን ጠየቅኩት፡፡ "የቃል ኪዳኑን ታቦት ማለታቸው ነው? ከጥቂት ሳምንታት በፊት አክሱም ሳለሁ እዚያ እንደነበር ነግረውኛል፡፡ ስለዚህ እንዴት እዚህም፣ እዚያም ሊኖር ይችላል?"፡፡

ጥያቄዬ በመነኮሳቱ መካከል ረጅም ውይይትን አስከተለ፡፡ ከነዚህ ሰዎች ምንም ፋይዳ ያለው ነገር አላገኝም ብዬ እያሰብኩ ሳለሁ የተከፈተው ውይይትና ክርክር ወደማብቃቱ ደረሰ፡፡ በአስተርጓሚዬ አማካይነት ጉዳዩ ቀስ፣ በቀስ ግልጽ እየሆነልኝ መጣ፡፡

እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የራሱ የሆነ መቅደስ አለው፡፡ እያንዳንዱ መቅደስ ደግሞ በውስጡ ታቦት አለው፡፡ ሆኖም እነዚህ ታቦታት የመጀመሪያው የቃል ኪዳኑ ታቦት እንዳልሆኑ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም አንድ የመጀመሪያ የቃል ኪዳን ታቦት እንዳለና እርሱም ታቦተ ጽዮን ተብሎ የሚጠራው ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ያመጣውና አክሱም የሚገኘው ብቻ ነው፡፡ በተቀረ በአገሪቱ ያሉት ሁሉ የመጀመሪያው ታቦት አምሳያ ናቸው፡፡

አምሳያ ቢሆኑም ግን ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ አባ ኃይለማርያም በርጋታ እንደገለጹልኝ "አብያተክርስቲያናቱ በራሳቸው የተቀደሱ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የተቀደሱ የሚያደርጋቸው የታቦቱ በውስጣቸው መኖር ነው፡፡ በመቅደሱ ውስጥ ታቦት የሌለበት ቤተክርስቲያንም ባዶ ቀፎ ማለት ነው፡፡ ከሌላው ሕንፃ በምንም አይለይም፡፡"

## የኢትዮጵያ ጥቁር አይሁዶች

በጣና ሐይቅ የገዳማት ጉብኝታችንን አጠናቀን ወደባሕር ዳር ተመለስን፡፡ ከዚያም ወደሰሜን በመጓዝ የጉንደርን መንገድ ተያያዝነው፡፡ ጉንደር በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ፋሲል

የተቆረቆረች ከተማ ስትሆን፣ እኒሁ ንጉሥ የአክሱም ጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያንን እንደገና ያሳነጹ ናቸው።

ወደጎንደር እያመራሁ ሳለሁ ስለሰማሁት የታቦት ጉዳይ ማሰላሰሌን አላቋረጥኩም። በዚህን ጊዜ በተለይ ቀልቤን የሳበው አንድ ነገር ነበር። ይኸውም ኢትዮጵያውያን ለቃል ኪዳኑ ታቦት ታላቅ ትኩረት መስጠታቸውና እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዚሁ ታቦት አምሳያ መቀመጥ አስፈላጊነት ነበር። እንደገባኝ የቃል ኪዳኑ ታቦት በቅድመ ክርስትና ጊዜ የነበረ ሲሆን፣ ከኢየሱስ ትምህርትም ጋር ምንም የሚያገናኘው የለም። ታዲያ እዚህ አገር ምን እየተካሄደ ነው? አልኩ ለራሴ።

በጉዞዬ ላይ አክሱሞች ስለንጉሥ ሰሎሞንና ንግስተ ሳባ እንዲሁም ልጃቸው ምኒልክ የሚናገሩትን ታሪክ እውነተኛነት ማሰላሰሌ አልቀረም። ምናልባት እነዚህ አፈ-ታሪኮች የተወሰነ እውነት ሊኖራቸው ይችላል። ደግሞም የጥቁር አይሁዶች በአገሪቱ ውስጥ መኖር ከንግስተ ሳባና ከታቦቱ ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይችላል። ለዚህ ሁሉ መፍትሄው ፈላሻዎችን መጎብኘትና ስለነርሱ ማንነት ከራሳቸው ጠይቆ መረዳት ነበር።

ከጎንደር ከመነሳታችን በፊት ግን በምንም ዓይነት ፈላሻዎችን ፎቶግራፍ እንዳላነሳና እንዳላነጋግር ማስጠንቀቂያ በባለሥልጣናት ተሰጥቶኝ ነበር። አስተርጓሚዬና በመንግሥት የተመደበልኝ አስጎብኚዬ በግልጽ "መንግሥት ፈላሻ የሚባል ሕዝብ የለም ነው የሚለው። ከሌሉ ደግሞ ከየት አምጥተህ ነው የምታናግራቸው?" አለኝ።

አስር ደቂቃ ካልሞላ ጉዞ በኋላ፣ ከከተማው ዳርቻ በአንድ የሣር ቤት አናት ላይ የዳዊት ኮከብ ምስል ተሰቅሎ ስለተመለከትኩና አስተርጓሚዬ ባልቻን "ይህ የፈላሻ ቤት አይደለም?" ስል ጠየቅኩት።

ባልቻ ብልህና፣ የተማረ ሰው ነው። ብዙ ዓመታትም አሜሪካ ቆይቷል። አዲስ አበባ ያሉት ቢሮክራቶች ድርጊት ያበሳጩታል። "የኛ ባለሥልጣናት አቋም ከቀን ወደቀን ተለዋዋጭ ነው። እምና በነርሱ ፈቃድ አንድ የካናዳ ፊልም ቡድን ይዤ መጥቼ ነበር። ሰዎቹ ፎቶግራፍ አነሱ፤ ፊልምም ቀረጹ። ስለሃይማኖት፣ ስለፖለቲካ፣ ስለነፃነትና ስለጭቆና ወዘተ ቃለመጠይቅ ሲያደርጉ አስተርጓሚ እኔ ነበርኩ። በመጨረሻ በፀጥታ ፖሊሶች ተይዤ፣ ለጥቂት ሳምንታት በፀረ መንግስትነት ታሰርኩ። ታዲያ አሁንም ልታሳስረኝ ትፈልጋለህ?" አለኝ።

"በፍጹም። እኔ'ኮ የምሠራው ለመንግሥት ነው። የአገሪቱን ሕዝቦች ባሕል ለማስተዋወቅና የሚጠቅማቸውን መጽሐፍ ለማሳተም ነው የምንቀሳቀሰው። እዚህ ላይ ነው ልዩነቱ።"

"እንደዚያ ላይሆን ይችላል። ባለፈው ዓመት ከፊልም ቀራጮች ጋር ስመጣ መንግስት የፈላሻዎችን ሕልውና አልካደም ነበር። እንዲያም ሆኖ ግን እስር ቤት ተወረወርኩ። አሁን ደግሞ የሉም ብሏል። ስለዚህ ወደጄ ባስጎብኝህ ችግር ውስጥ እገባለሁ።"



ባልቻ ትክክል ነበር። ተራራማውን አካባቢ ስንወጣ፣ የመንግስትን አቋም እንዲያስረዳኝ ጠየቅኩት። "የችግሩ ከፊል መንስዔ አብዛኛዎቹ በአዲስ አበባ ያሉት ባለሥልጣናት የአማራ ብሔር አባላት መሆን ነው። ፈላሻዎች ደግሞ በጎንደርና በጎጃም በዋነኛው የአማራ ግዛት ውስጥ ይኖራሉ። በዚህም የተነሣ በመካከላቸው ብዙ ጊዜ ውጥረት አለ። አልፎ አልፎም ግድያ ይፈፀምባቸዋል። እነዚህ አይሁዶች፣ በአማራ ጎረቤቶቻቸው የተናቁ ናቸው። የኢኮኖሚ ጭቆናም ይደረግባቸዋል። ከአብዮቱ በኋላ መጠነኛ መሻሻል የታየ ቢሆንም፣ ገዢዎቹ የሠሩት በደል ሕሊናቸውን ኃረፍት የሚነሳው ይመስለኛል። ማንም የውጪ ዜጋ ስለፈላሻዎች እንዲያውቅ አይሹም። በተለይ ከ1980ዎቹ መጀመሪያ አንሥቶ ፈላሻዎችን በተመለከተ የአሜሪካና የእንግሊዝ አይሁድ ነብኘዎች ተቃውሟቸውን በግልፅ ማሰማት ስለጀመሩ መንግስት ጭንቀት ውስጥ ገብቷል። ከዚህም በተጨማሪ ሌላ ውስብስብ ጉዳይ አለ። በአረቦችና በእስራኤሎች መካከል በነበረው ጦርነት ምክንያት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል አገሮች ከእስራኤል ጋር የነበሩቸውን የዲፕሎማቲክ ግንኙነት በማቋረጣቸው ኢትዮጵያም ተመሣሣይ እርምጃ ወስዳ ነበር። ሆኖም ዛሬም በሁለቱ አገሮች መካከል ምስጢራዊ ግንኙነት አለ። እስራኤል መጠነኛ ወታደራዊ ዕርዳታ ለኢትዮጵያ ስለምትሠጥ ፈላሻዎች ወደእስራኤል በምስጢር እንዲጓዙ መንግሥት ፈቃድ ሰጥቷል። ችግሩ ግን በርካታ ፈላሻዎች በአየር ወደቴልአቪቭ ለመጓዝ ድንበር እያቋረጡ ወደጎረቤት ሱዳን መሄዳቸው ነው። በመሆኑም ጉዳዩ አሳሳቢ ሆኗል። መንግስት ይህ ሰውን በጠብመንጃ የመለወጥ ተግባሩ እንዳይታወቅበት ይፈራል። ምክንያቱም በአንድ በኩል ምሥጢሩን አለድ እንዲያውቅበት አይፈልግም። በሌላም በኩል የፈላሻዎች የብዙ ኢትዮጵያውያን ወዳጅ ወዳልሆነ ጎረቤት አገር መጉረፍ መንግሥትን ደካማ አድርጎ ስላስቀጠረው ጉዳዩ ባለስልጣናቹን አስቆጥቷቸዋል" አለኝ።

በቀጣዮቹ ሦስት ቀናት ውስጥ ብዙም ስለፈላሻዎች ለመጠየቅ ጊዜ አልነበረኝም። ጉዞአችንን ቀጥለን ወደሰሜን ተራሮች እምብርት ደረስን። እሸሃማ ቁጥቋጦ የወረሰውና ሰው የማይኖርበት ሥፍራ ስድስት ሺህ ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። ዘጠኝ ሺ ሜትር ከፍታ የሚደርስ አካባቢም አለ። የተወሰነው አካባቢም አሥራ ሦስት ሺህ ሜትርና ከዚያም በላይ ይሆናል። ከፍተኛው ግን በበረዶ የተሸፈነው የራስ ዳሽን ተራራ ነው። ከኢትዮጵያ አንደኛ፣ ከአፍሪካ አራተኛ የሆነው ይህ ተራራ 14,910 ሜትር ከፍታ አለው።

ወረድ ብለው የተበታተኑ መንደሮች ይታያሉ። የከብት ጋጣዎችንና የእርሻ ማሳዎችንም ተመለከትን። በዚህም ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮ ለውጥ ሳያሳይ ሲወርድ፣ ሲወራረድ የመጣ የግብርና ኑሮ መኖሩን አረጋገጥኩ። የፈላሻ መንደሮች ከመካከላቸው ቢኖሩም ባልቻ ስላስጠነቀቀኝ ማንንም አላነጋገርኩም። አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች ግን አማሮች ናቸው። የሚኖሩትም በመንደሮች ሳይሆን፣ እምስት

ወይም ስድስት በመሆን ተበታትነው ነው፡፡ በአካባቢው ያነጋገርናቸው ገበሬዎች ኑሮአቸውን በመሬት ላይ የመሠረቱ ድሆች ናቸው፡፡ ቢሆኑም ግን ኩሩዎች ናቸው፡፡ የዚህም ባሕርያቸው ምንጭ የገገር ው መደብ ዝርያዎች መሆናቸው እንደሆነ ባልቻ ነገረኝ፡፡ ከ1270 ጀምሮ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እስከ ወደቁበት 1974 ድረስ ለስድስት መቶ ዓመታት ከአንድ ንጉስ በስተቀር የኢትዮጵያ ነገስታት አማሮች ነበሩ፡፡ አፍ መፍቻቸው የአማርኛ ቋንቋም የአገሪቱ የሥራ ቋንቋ ተደርጓል፡፡

የክርስትና እምነትን መሠረት ያደረገው የአማራው ባሕል በሌሎች ብሄር፣ ብሄረሰቦች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ ባለፉት ጥቂት ምዕተ ዓመታት፣ ብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ የአማራውን ባህልና ቋንቋ እንዲቀበሉ ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ፈላሻዎች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን መለያ ይዘው መቆየታቸውም የሚያስደንቅ ነው፡፡

ወደጉንደር ስንመለስ፣ ባልቻ አንድ የፈላሻ መንደር አጠገብ እንድንቆም በማድረግ፣ "በሉ ሂዱ፣ አስር ደቂቃ ሰጥቻችኋለሁ" በማለት እንቅልፍ እንዳሸለበው ሁሉ መኪና ውስጥ ተኛ፡፡

ከመኪና እንደወረድን "ሻሎም፣ ሻሎም" በሚሉ የመንደሩ ሕጻናት ተከበብን፡፡ ልጆቹ ከዚህ ሌላ የሚያውቁት ቃል አልነበረም፡፡ የመንደሩ ስም ወለቃ ይባላል፡፡ ሰዎች ተሰባስበው መጡ፡፡ አይሁዶች መስለናቸው ይሆናል፡፡ ግማሾቹ የሠሯቸውን ሸክላዎች ለመሸጥ ተሰባሰቡ፡፡ በሸክላዎቻቸው ላይ የዳዊት ኮከብ ምስል ተቀርጾውባ ቸዋል፡፡ ንጉሥ ሰሎሞንና ንግሥተ ሳባ በመኝታ ላይ ሳሉ የሚያሳይ ሥዕል ያለበት ሸክላም ይዘዋል፡፡ ወደመንደሩ ዘለቅን፡፡ ሸማኔው ጉድጓዱ ውስጥ ይሠራል፡፡ ብረት ቀጥቃጩ ደግሞ የወዳደቁ ብረታ ብረቶች ዙሪያውን ከበውት መጥረቢያ ይሠራል፡፡ ሴቶቹ ሸክላ ይሠራሉ፡፡ ባልቻ በኋላ እንደነገረን አማራዎቹ እነዚህን ሰዎች ይንቋቸዋል፡፡ ለሸክላ ሠሪም የተሰጠው መጠሪያ "ጠይብ" ሲሆን ትርጉሙም "ቡዳ" ማለት ነው፡፡

ከወለቃ ስንመለስ በጣም ደክሞኝ ነበር፡፡ ሪቻርድ ፓንከረስት ስለመካከለኛው ዘመን የፈላሾች ታሪክ ስለነገሩኝና አክሱም ውስጥም የሰማሁት የቃል ኪዳኑ ታቦት ታሪክ ከነዚህ ሰዎች ጋር ይገናኝ እንደሆነ በማለት ተጨባጭ ያልሆነና የተጋነነ ግምት አሳድሬ ነበር፡፡ ለማየት የጓጓሁት ጥንታዊና የተከበረ የአይሁዳውያንን ባሕልና ሥልጣኔን ሲሆን፣ ያጋጠመኝ እውነታ ግን የፈረጆችን ፍላጉት ለማርካት ጉጉ የሆነ የተጉሳቆለና ድህነት ያጠቃውን አርሶ አደር ህዝብ ነበር፡፡ መስጂድ የተባለው የአምልኮት ሥፍራ ከእስራኤል በመጡ ትርኪ ምርኪ መሰል ስጦታዎች ተሞልቷል፡፡ ከቴል አቪቭ ታትሞ የመጣው ቶራ የተባለው የዕብራውያን መጽሐፍም ጥግ ተቀምጧል፡፡ በዕብራይስጥ ቋንቋ ስለነበር የሚያነበው የለም፡፡



ከመንደሩ ስንመለስ ሰሎሞንና ሳባ ተኝተው የሚታዩበትን አንድ ትንሽ የሸክላ ዕቃ ገዛሁ፡፡ የጠበቅኩት ሁሉ ባዶ ተስፋ ስለሆነብኝም በብስጭት ውጪ፣ ውጪውን እየተመለከትሁ ወደጉንደር ተመለስን፡፡

## ግብዐተ መሬት

በ1983 መጀመሪያ አካባቢ አክሱማውያን እንዳላቸው ስለሚናገሩት የቃል ኪዳን ታቦት ለማወቅ የነበረኝ ጉጉት ፈጽሞ ተሟጠጠ፡፡ ይህ ግን በፈላሻዎች መንደር የጠበቅኩትን ካለማግኘቴ ጋር ግንኙነት አልነበረውም፡፡ ይህ ስሜት ቢፈጠረብኝም በሁሉም አብያተክርስቲያናት የቃል ኪዳኑ ታቦት እምሳያዎች መኖራቸው ደግሞ በቃል ኪዳኑ ታቦትና በእምሳያዎቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማወቅ እንድጓጓ አደረገኝ፡፡ ጉዳዩን በ1983 ፀደይ ላይ በለንደን ከተማ ሐምፕስቴድ የሚኖሩትን ሪቻርድ ፓንከረስት ለመጉብኘት በሄድኩበት ወቅት አነሳሁባቸው፡፡ ታቦታቱ የመጀመሪያው ቃል ኪዳን ታቦት እምሳያዎች መሆናቸውን ያረጋገጡልኝ እኚህ የታሪክ ሰው፥ "ግር የሚል ነገር ነው፡፡ እስከማውቀው ድረስ ግን በሌሎች የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ይህ አይታወቅም" አሉ፡፡

ታቦታቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከመቼ ጀምሮ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ጠየቅኋቸው፡፡ ስለጉዳዩ ምንም እንደማያውቁ ገለጡልኝ፡፡ "ሆኖም በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ውስጥ (ስለታቦት) ያወሱት ፖርቱጋላዊው ቄስ ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ ነበሩ፡፡ ለረጅም ዘመን የቆየን ልምድ መዘገባቸው ግን በግልፅ ይታወቃል፡፡" ወዲያውኑም ሪቻርድ አንድ መፅሐፍ ከመደርደሪያቸው አወጡ፡፡

ከዚያም፣ "ይሄ አፊሴላዊ የቤተክርስቲያኗ ፅሁፍ ስለሆነ፣ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠን ግንዛቤ ካለ አብረን እንየው" አሉ ፕሮፌሰሩ፡፡ መጽሐፉ በ1970 የታተመ ሲሆን ርዕሱ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን" ይላል፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ "የቤተክርስቲያን ቅድስና፡፡" የሚል ርዕስ አገኘን፡፡ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

> የቤተክርስቲያን መባረክ ሥነ ሥርዓት ከፍተኛ በዓል ነው፡፡ ምክንያቱም ሕንፃው የአምልኮ ሥርዓት የሚከናወንበትና የተቀደሰ አገልግሎትም የሚሰጥበት ነውና... ጥንታዊነት ያላቸው ብዙ ዓይነት የአገልግሎት ሥርዓቶችም አሉ፡፡ ጽላቱ አስቀድሞ በፓትርያርኩ ከተባረከ በኋላ በከፍተኛ ክብር ወደመንበሩ የመግባቱ ሂደት ዋነኛው የበዓሉ ገጽታ ነው፡፡

ሌላ ምዕራፍ ላይ ደግሞ "ለቤተክርስቲያኑ ሕንፃ ቅድስናን የሚያሰጠው ጽላቱ ነው ይላል፡፡" በመጨረሻም ቃላት መፍቻውን ሳነብ ታቦት የሚለውን ቃል ትርጉም ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር አንድ ሆኖ አገኘሁት፡፡

"እንደመጽሐፍ ቅዱስ አባባል ከሆነ የመጀመሪያው ታቦት ከእንጨት የተሠራና በውስጥና በውጪ በወርቅ የተለበጠ ነው፡፡ ታቦቶቹ በርግጥ ይህን ይመስላሉ?" ስል መልሼ ሪቻርድን ጠየቅኳቸው፡፡

"አይመስሉም፡፡ ደግሞም ለተራው ምዕመን ታቦት ማየት አይፈቀድለትም፡፡ ጽላቶቹ ለበዓል በሚወጡበት ጊዜ እንኳን በመጐናጸፊያ ይሸፈናሉ፡፡ እርግጠኛ ነኝ እነዚህ ጽላቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው ጋር ሲነጻጸሩ ትንንሾች ናቸው፡፡ ለማየት ከፈለግህ ወደብሪትሽ ሙዚየም ብቅ በል፡፡ ወደመቅደላ የዘመተው የናፒየር ወታደራዊ ልዑክ ከኢትዮጵያ ሲመለስ ዘርፎ ወደእንግሊዝ ያመጣቸው ታቦቶች አሉ፡፡ ነገር አሁን፣ አሁን እንኳን ለሕዝብ ዕይታ መቅረባቸው ቀርቷል፡፡ ነገር ግን ሐከኔይ በሚገኘው የሰው ልጅ ዘር ጥናት ግምጃ ቤት ታገኛቸዋለህ፡፡"

በሚቀጥለው ቀን እስራም መንገድ፣ ለንደን ኤን 1 ወደሚገኘው ግምጃ ቤት አመራሁ፡፡ ሕንፃው ዘመናዊና የማይስብ ነበር፡፡ ሆኖም ከፍተኛ ጥበቃ እየተደረገለት ነበር፡፡ "ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ሰብረው ያሉንን ቅርሶች ለመስረቅ ይሞክራሉ" አሉኝ የግምጃ ቤቱ ጠባቂ፡፡ አብረን በአሳንሰር ወደላይኛው ፎቅ ወጣንና ወዳንድ ትልቅ መጋዘን አመራን፡፡ ክፍሉ ውስጥ መደርደሪያዎች ከወለሉ እስከጣራው ድረስ ተገጥመዋል፡፡ በየመደርደሪያዎቹ መካከል ጠባብ መተላለፊያዎች አሉ፡፡ ጠባቂው አንድ ወፍራም መዝገብ ካገላበጡ በኋላ፣ "ተከተለኝ" አሉ፡፡ እየተጠማዘዝን በኮሪደሮቹ መካከል መሄድ ጀመርን፡፡

"የጠፋው ታቦት ዘራፊዎች" የሚለው ፊልም በሐሳቤ መጣ፡፡ በመጨረሻው ክፍል ያየሁት ጽላቱ በአንድ የእንጨት ሳጥን ተቆልፎ በፌዴራል ግምጃ ቤት ውስጥ ከሌሎች ብዙ ዕቃዎች ጋር ተመሰቃቅሎ መቀመጡን ነበር፡፡ ጠባቂው በመጨረሻ ቆሙ፡፡ ከዚያም አንድ ትልቅ ሳጥን ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ እየሳቡ አወጡ፡፡ ሰውነቴን ውርር የሚያደርግ የደስታ ስሜት ተሰማኝ፡፡ ሣጥኑ እንደተከፈተ ያልጠበቅኩትና ተመሣሣይነት የሌለውን ነገር አየሁ፡፡ ዘጠኝ ከእንጨት የተጠረቡ ሠሌዳዎች፣ የያንዳንዳቸው ወርድ በሁሉም በኩል እኩል የሆኑና ሌሎች ደግሞ ወርድና ቁመታቸው የተለያዩ፣ ውፍረታቸው ቢበዛ እስከ አንድ ሳንቲ ሜትር የሆኑ ሁሉም ጽሑፍ የሠፈረባቸው ነበሩ፡፡ ጽሑፉ ግእዝ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ አንዳንዶቹ ላይ የመስቀል ቅርጽ ታትሞባቸዋል፡፡ ሌሎችም ምልክቶች አሉባቸው፡፡

መዝገቡን ሲመለከቱ ምናልባት ተሳስተው እንዳይሆን በማለት ጠባቂውን መለስ ብዬ እርግጠኛነታቸውን ጠየቅሁዋቸው፡፡

ጠባቂው በእጃቸው ያለውን ዝርዝር እያስተዋሉ፣ "የሆልምስ ስብስብ ናቸው፡፡ በ1867/68 ወደአቢሲኒያ የተጓዘው የብሪትሽ ወታደራዊ ልዑክ ያመጣቸው ናቸው፡፡ ጽሑፉ ይህን ነው የሚለው" አሉኝ፡፡



ምስጋናዬን አቅርቤ ወጣሁ፡፡ የጥረቴ መቋጫ ነበር፡፡ ሆኖም አንድ ነገር አረጋገጥኩ፡፡ እነዚህ የእንጨት ሠሌዳዎች፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት ወይም ጽላተ ሙሴ አይደሉም፡፡ ፍፁም ተሳስቻለሁሳ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የቅዱስ ፅዋው ምስጢራዊ ጽሑፍ

በ1983 አክሱምን በጐበኘሁበት ወቅት ነበር ኢትዮጵያ አለኝ ስለምትለው የቃል ኪዳን ታቦት የመቀመጫ ሥፍራ ያወቅሁት፡፡ ያኔ ስለምትለው የቃል ኪዳን ታቦት የመቀመጫ ሥፍራ ያወቅሁት፡፡ ያኔ ቤተሰቦቼን ይዤ አፍሪካ ውስጥ ኗሪ ነበርኩ፡፡ በ1984 አፍሪቃን ትቼ ቤተሰቦቼን ይዤ ወደ እንግሊዝ አገር ተመ ነኩ፡፡ ሆኖም ለመንግሥት የማዘጋጃቸው በርካታ ጽሑፎች ስለነበ በቀጣዮቹ ዓመታት ወደአዲስ አበባ ኢመላለስ ነበር፡፡ በዚሁ ሥራዬ የተነሣ ከባለሥልጣናቱና ከፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ጋር ሳይቀር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥሬ ነበር፡፡ አምባገነኑ መሪ ሰብዓዊ መብቶችን በመርገጥ የታወቁ ቢሆኑም፣ በነበረኝ የቅርብ ግንኙነት የተነሣ ለውጪ ዜጐች የተከለከሉ ቦታዎች ለጉብኝት እንዲፈቀዱልኝ ከማድረጌም በላይ አንዳንድ ጠቃሚ ጉዳዮችንም ለማስፈጸም ችያለሁ፡፡ ብፈልግ ኖሮ ስለጽላቱም ጉዳይ ለመከታተል እችል እንደ ነበር እርግጠኛ ነኝ፡፡ ጉጉቱ ግን አልነበረኝም፡፡ በዚህ መካከል በ1988 የሕወሐት ተዋጊዎች አክሱምን በተቆጣጠሩ ጊዜ ከመንግስቱ ኃይለ ማርያም ጋር በነበረኝ ቅርበት ምክንያት የተቀደሰችው ከተማ በራፍ ጥርቅም ብሎ ተዘጋብኝ፡፡ ሕወሐት ባደረገው ያንድ ቀን ጥቃት ከሁለት ሺህ በላይ የመንግሥት ወታደሮች ተገድለውና ተማርከው አክሱም ተያዘች፡፡ ነገር ግን ከእንግዲህ ወደዚያ ከተማ የምሄድበት ጉዳይ አልነበረኝም፤ ወይም እንደዚያ አሰብሁ፡፡

## ንግስተ ሳባ በሻርትር

የ1988ትን አጋማሽና የ19897 የመጀመሪያ አጋማሽ ዓመቶች የሰሜን ኢትዮጵያ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ሥነሥርዓቶችን የሚመለከቱ ሥዕላዊ ጽሑፎችን በማዘጋጀት አሳለፍኩ፡፡ ይህ ፕሮጀክት በመንግሥት ሳይሆን፣ ዓለም አቀፍ ዕውቅና ባላቸው ሁለት ፎቶ አንሺዎች፣ እንጂላ ፊሸር እና ካሮል ቤክዊዝ አገዛ የሚዘጋጅ ነበር፡፡

ከያዝኩት የምርምር ሥራ ጠባይ የተነሣ ስለኢትዮጵያ የተለያዩ ጉሣዎች፣ በኢትዮጵያ ደጋማ ሥፍራ ስለሚኖሩት ፈላሾች ጭምር ዝርዝር ጥናት፣ ቅድመ ዝግጅትና ምርምር ማድረግ ነበረብኝ፡፡

በተጨማሪም ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት የጠቀሱልኝንና ድህረ ልደተ ክርስቶስ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግእዝ የተጻፈውን ክብረ ነገሥትን ማግኘት ነበረብኝ፡፡ ይህ መጽሐፍ ስለጥንታዊው የአክሱም ታሪክ፣ ስለንግሥተ ሳባና ንጉሥ ሰሎሞን፣ ስለልጃቸው



ምኒልክ መወለድ፣ እንዲሁም ስለታቦቱ ከመጀመሪያይቱ የኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ መዘረፍ ያወሳ ነበር፡፡

ጽሑፌ እስከ መጋቢት፣ 1989 አልተጠናቀቀም፡፡ ሚያዚያ ላይ ሙሉ በሙሉ እረፍት ለማድረግ፣ ከቤተሰቦቼ ጋር ወደፈረንሳይ ተጓዝኩ፡፡ ከፓሪስ ከተማ መኪና በመከራየትም የተወሰነ መድረሻ ባይኖረንም እንኳን ወደደቡብ አቅጣጫ አቀናን፡፡ ቨርሳይል እንደደረስን ቤተመንግስቱንና ሌሎቹን ህንፃዎች እየጎበኘን ጥቂት ቀናት አሳለፍን፡፡ ከዚያም ወደሻርትር ከተማ አመራን፡፡ ሻርትር ጥንታዊትና ውብ ከተማ ስትሆን ይበልጥ የምትታወቀው ጉልላቶቹ በሾሉት ግዙፍ የጐቲክ ካቴድራሏ ነው፡፡ የአክሱም ቤተክርስቲያን በቅድስት ማርያም ስም እንደተሰየመ ሁሉ ሻርትር ያለው ካቴድራልም የተሰየመው በቅድስት ማርያም ስም ነው፡፡

ሻርትር ድህረ ልደተ ክርስቶስ ከ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከፍተኛ የክርስትና ማዕከል ሆና ቆይታለች፡፡ ከ9ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ፣ ማለትም ሻርል ዘ ቦልድ የተባለው የሻርለማኝ የልጅ ልጅ ቅድስት ማርያም፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ስትወልድ ተጐናጽፋው የነበረውን አይነርግብ ካበረከተ በኋላ ለቅድስት ማርያም ታላቅ አትኩሮት የሚሰጥበት ቦታ ሆነ፡፡ በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሻርል ዘ ቦልድ አሠርቶት የነበረው ቤተክርስቲያን በመቃጠሉ፣ በምትኩ በዚያው መሠረት ላይ የሮማውያንን የሕንፃ አሠራር የተከተለ ካቴድራል ተሠራ፡፡ ይህም ካቴድራል በበኩሉ በደረሰበት የእሳት ቃጠሎ ክፉኛ ተጐድቷል፡፡ በ12ኛውና በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከቃጠሎው የተረፈው አካል በሰፊው ተለውጦና ተስፋፍቶ፣ እንደ ቀስት የሾለ ቅርጽ ያላቸው አዳዲስ ጉልላቶች ታክለውበት በአዲስ መልክ ተሠራ፡፡ በስተሰሜን ያለው ሾጣጣ ግንብ በ1134 ተጠናቀቀ፡፡ ይህ በዓለማችን የጐቲክ የሕንፃ ጥበብ የቀደምትነትን ሥፍራ የያዘ ሲሆን፣ የደቡቡ ሾጣጣ ጉልላቱና ሌሎቹ ገፅታዎቹ በተከታዮቹ ሃያ ዓመታት ውስጥ ተጠናቀቁ፡፡ በ1194 እና በ1225 መካከል በተጧጧፈ ሥራ ቀሪው የሕንፃ ክፍል ዕፁብ ድንቅ በሆነ አሠራር ተጠናቀቀ፡፡ እነሆ ከዚያን ዘመን ጀምሮም እስከአሁን ሳይለወጥ አለ፡፡

ሻርትር በቆየሁበት ወቅት በካቴድራሉ ሕንጻ ውስጥ ከማየው ባሻገር ስለታሪኩ ለማወቅ ፍላጐት አልነበረኝም፡፡ በካቴድራሉ ዙሪያ የተገጠገጡትን ቅርፆች ማጥናት ቢያስፈልግ፣ የአንድ ሰው ዕድሜን ይፈጃል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ስለዚህ ይህን ጥናት አላቀድኩትም፡፡ ሌሎች ጉዳዮች ስለነበሩን ግን መቆየት ነበረብን፡፡ ሦስቱን ቀናትም በመዛኙ ይህን ካቴድራል እየተዟዟርኩ በጥሞና በመመልከት አሳለፍኩ፡፡

የገዛኋቸው የጉብኚዎች መመሪያ መፃህፍት እዚህ የሚታየው ሁሉ ያለምክንያት የተሠራ አለመሆኑንና፣ መላው ሕንጻ ሲነደፍ ጥልቅና ቁልፍ የሆኑ ሃይማኖታዊ ምሥጢሮችን ይዞ እንዲቆይ ተደርጐ መሠራቱን ያወሳሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ግንበኞችና አርክቴክቶቸች ሕንፃውን ሲገነቡ የተጠቀሙበት ጥንታዊ የዕብራውያን ቀመርን ሲሆን፣ ይህን ቀመር ፊደላትን በአሃዞች ተክቶ ሰውር ማኖርና

መፍቻ ቁልፍ መስጠት ነበረበት፡፡ በተጨማሪም ጠራቢዎችና የመስተዋት ላይ ምሥል ቀራጮች በሊቃውንቱ በመመራት በዚሁ ሕንፃ ላይ የሠሯቸውን የረቀቁ መልእክቶች፣ ማለትም ስለሰው ልጅ ባሕርይ፣ ስለቀደሙት ዘመናትና የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን ትርጉም የሚያሳዩ ከሺህ በሚበልጡ ቅርጻችና ዘዴዎች ተደብቀው ይገኛሉ፡፡ በተለያዩ ቀለማት የደመቁትና ብዙ ሥዕሎች የተሳሉባቸው መስተዋቶች ዓይንን የሚማርኩና የሚስቡ ቢሆኑም እያንዳንዳቸው በምሥጢሮች የተሞሉና ልዩ መልእክት ያዘሉ ናቸው፡፡ ፈተናው እነዚህን ምሥጢሮች ጠልቆ በመመርመር በውስጣቸው ያዘሉትን ምሥጢር መፍታቱ ላይ ነው፡፡

የሚታዩኝ ሕንፃውና በላዩ የተቀረጹት ምስሎች ስለነበሩ መጀመሪያው ላይ የተደበቀ ምሥጢር ይኖራል ብዬ ለመቀበል ተቸግሬ ነበር፡፡ ከሌሎች ጉብኝዎች ጋር በመቀላቀል ጉብኝቴን ምርምሬን ስቀጥል ግን፣ ሕንፃውን "አንድ ትልቅ መጽሐፍ" ሆኖ አገኘሁት፡፡ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን በማገናዘብ ቀስ በቀስ የማያቸውን ነገሮች ትርጉም እረዳ ጀመር፡፡ እነዚህንም ከያዝኳቸው የጉብኝዎች መመሪያዎች ጋር በማመሳከር ግንዛቤዬ ትክክል መሆን አለመሆኑን አጣራ ነበር፡፡

በመሐሉ አንድ ያልታሰበ ነገር አጋጠመኝ፡፡ ከካቴድራሉ ደቡባዊ መግቢያ በር ትይዩ ወደአንዲት አነስተኛ ምግብ ቤት ጎራ አልኩኝ፡፡ ስሟ (Reine de Saba) "የሳባ ዘመነ መንግስት" ይላል፡፡ የክብረ ነገሥቷ ንግስተ ሳባ ትውስ አለችኝና አሳላፊውን ለምን ምግብ ቤቷ በዚሁ ስም እንደምትጠራ ጠየቅኩት፡፡ "ምክንያቱም የንግሥተ ሳባ ሐውልት ካቴድራሉ መግቢያ ላይ ስላለ ነው" አለኝ፡፡

ጉጉቴ ስለጨመረ መንገዱን ተሻግሬ አስራ ሰባት ደረጃዎችን ከወጣሁ በኋላ ያጌጠው በራፍ ደረስሁ፡፡ መግቢያው ሰፊ በር ነበረው፡፡ ሕንፃው በመቶዎች በሚቆጠሩ ሐውልቶች የተሞላ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ሙሉ አካልን የሚያሳዩ ቢሆኑ፤ ንግሥተ ሳባን የሚመስል ምሥል ግን ለማግኘት አልቻልኩም፡፡ ስለዚህ የጉብኝዎች መመሪያ መጽሐፍቴን፤ በተለይም "ሻርትር የካቴድራሉ የጎብኚዎች መምሪያን" ተመለከትኩ፡፡ የት መመልከት እንዳለብኝ መራኝ፡፡

> በውስጥ በኩል ያለው የውጪኛው የመግቢያ ታዛ በአራት ዘመን የነበሩ የሃያ ስምንት ነገሥታትና ንግሥቶችን ሐውልት ያሳያል፡፡ የምንለያቸው፣ ዳዊትን በበገናው፤ ሰሎሞንን በበትረ መንግሥቱ፤ ንግስተ ሳባን በግራ እጇ በያዘችው አበባ ነው፡፡ ከበላይ አራት ጢማቸው የተንዠረገ ታላላቅ ነቢያት፣ ከበታቻቸው ካሉ አራት ታናናሽ ነቢያት ጋር ሲነጋገሩ ያሳያል፡፡

ይህ መጽሐፍ በተጨማሪ የገለጸልኝ ነገር፤ ይህ ደቡባዊው መግቢያ በር በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የተሠራና ዘመኑም በኢትዮጵያ ክብረ ነገሥት ስለንግሥተ



ሳባና ምኒልክ እንዲሁም ስለታቦቱ መሰረቅ ከተጻፈበት ጊዜ ጋር አንድ መሆኑን ነው፡፡

የነገሮቹ መገጣጠም አስገራሚ ስለሆነብኝ፣ የንግሥተ ሳባን ሐውልት በጥንቃቄ መመርመር ጀመርኩኝ፡፡ ምንም አዲስ ነገር ለማየት ግን አልቻልኩም፡፡ የተለየ የመሰለኝ ነገር ቢኖር የዚህች ንግሥት ሐውልት በበርካታ የአይሁድ ነገስታትና ነቢያት መካከል መገኘቱ ነበር፡፡ ክብረ ነገሥት ንግሥቲቱ የአይሁድ እምነት ተቀብላ እንደነበር ቢናገርም፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለጉዞዋ የሚያወሳው ክፍል ስለዚህ አያነሳም፡፡ በስም በተጠቀሰችባቸው በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማይ ምዕራፍ 10 እና በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልእ ምዕራፍ 9 መሠረት ወደኢየሩሳሌም ስትመጣ አረማዊት ነበረች፤ ስትመለስም እንዲሁ፡፡ እንግዲህ አረማዊነቷ ነው ልዩ ሊያደርጋት የቻለው፡፡ አለበለዚያ ካቴድራሉን የገነቡት ሰዎች ኢትዮጵያዊውን የክብረ ነገስት ታሪክ ያውቁ ነበር ማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ያለው ታሪክ ይህች ንግሥት ከኢትዮጵያ ስለመምጣቷ የሚገልጽ አንዳችም ነገር የለውም፡፡ ብዙዎች ተመራማሪዎች የሚያምኑት የደቡብ አረቢያ በተለይም ሳባ ወይም ሳቢያ የምትባለው የዛሬይቱ የመን ንግስት እንደሆነች ነው፡፡

ጉጓዬን በዚሁ ልተወው አስቤ ነበር፡፡ ነገር ግን ሌላ የንግሥተ ሳባ ሐውልት በሰሜኑ በኩል ባለው መግቢያ ታዛ ውስጥ መኖሩን ከጉብኚዎች መመሪያዬ ለመረዳት ስለቻልኩ ወደዚያው አመራሁ፡፡ ይህ መግቢያ ያተሠራው ከ1200 እስከ 1225 ባለው ጊዜ ገደማ ነው፡፡ ያተኮረውም ዝርዝር ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ጋር ጭብጦችን በማሣየት ላይ ነው፡፡

## የቃል ኪዳኑ ታቦትና የድንጋይ ላይ ጽሑፎች

በመጀመሪያው ቀን በሰሜኑ መግቢያ አካባቢ በድንጋይ ስለተቀረጸው ውስብስብ ታሪክ ሳውጠነጥን ወደሁለት ሰዓት ገደማ ፈጀሁ፡፡ በስተግራ በኩል፣ በምሰሶዎቹ መካከል ባለው መተላለፊያ፣ የድንግል ማርያም እና የልጇ የክርስቶስ እንዲሁም ከብሉይ ኪዳን ነቢያት የኢሳይያስና፣ የዳንኤል ሐውልቶች ተቀርጸውበታል፡፡

በተጨማሪ፣ ደግነት በከፋት ላይ የተቀዳጀውን ድል የሚያሳይ የነፍስንና የሥጋን መቀደስ በተመለከተ በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታዋቂ በሆኑት በክሌየርቮው ቅዱስ በርናርድ የተገለጹ ታሪኮች ይገኛሉ፡፡

የመካከለኛው መተላለፊያ ደግሞ በብሉይ ኪዳን ዘመን ፓትርያርኮችና ነቢያቶች የተሞላ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ካህንና የሳሌም ንጉሥ የነበረው የዘር ትውልዱ የማይታወቀው የመልከ ጼዴቅ ሐውልትም በዚያ ይገኛል፡፡ ስለመልከጼደቅ በዘፍጥረት ምዕራፍ 14 እና በመዝሙረ ዳዊት መዝሙር 109 ተጠቅሷል፡፡ አብርሃም፣

ሙሴ፥ ሳሙኤል፥ ዳዊት፣ ኤልያስና ቅዱስ ጴጥሮስም ይታያሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኤደን ገነት በአራቱ ወንዞቿ እንደተከበበችና ቅድስት ማርያም ዘውድ ጭና በሰማያዊ ዙፋን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጐን ተቀምጣ ትታያለች፡፡

ንግሥተ ሳባን ያገኘኋት በስተቀኝ በሚገኘው መተላለፊያ በር ነበር፡፡ ያየሁት ሐውልት በደቡባዊው መግቢያ በኩል እንዳየሁት ግልፅነት የጐደለው ሳይሆን ሙሉ ቁመት ያለው ሐውልት ነበር፡፡ ንግሥተ ሳባ የቆመችው ከንጉሥ ሰሎሞን አጠገብ በመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ታሪክ ጋር የተገናዘበ ትርጉም ይሰጣል፡፡ በድንገት ዓይኔን የሳበው ጉዳይ ግን ከእግሮቿ ሥር አጐንብሶ የሚታይ አፍሪካዊ ነበር፡፡ ከጐብኚዎቹ መመሪያ መፅሀፎቹ አንዱ “ጥቁር አገልጋይ” በማለት ሲገልፀው፣ ሌላው “ኢትዮጵያዊ ባሪያዋ” ይላል፡፡ ተጨማሪ ማብራሪያ አልተሰጠም፡፡ ሆኖም ግልጽ የሆነልኝ ነገር በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሻርትር ካቴድራል የሰሜኑን መግቢያ ያነጹት ጠራቢዎች ንግስቲቱን ያለምንም ጥርጥር በአፍሪካ ውስጥ ነው ያስቀመጧት፡፡ በዚህም የተነሳ ጠራቢዎቹ የኢትዮጵያን ከብረመንግስት ታሪክ ሊያውቁ አይችሉም ብሎ በቀላሉ ማጣጣል አልተቻለኝም፡፡ “አረማዊት” ንግሥት በክርስቲያን ካቴድራል ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ሊሰጣት የቻለበት ምክንያት ካቴድራሉን የሠሩት ሰዎች ስለክብረ ነገስት ማወቃቸውን ይገልፃል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እምነቷን በተመለከተ የተገለጸ ነገር ባይኖርም፣ በክብረ ነገስት ውስጥ አረማዊነትን ትታ እውነተኛውን የፓትርያርኮች እምነት መቀበሏ ተገልጿል፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ታሪክ በዚያ ዘመን እንዴትና በምን መንገድ ሰሜናዊ የፈረንሳይ ግዛት ድረስ ሊዘልቅ ቻለ የሚለው ጥያቄ ግን መነሳቱ አይቀርም፡፡

ይህን እያሰላሰልኩ ባለሁበት ወቅት ነበር በመካከለኛውና በቀኝ ክንፍ በኩል ባለው ምሰሶ መካከል አንድ ታላቅ መልዕክት ያለው የተጠረበ ቅርጽ የተመለከትኩት፡፡ በትንሹ ከጥቂት ሳንቲሜትሮች ቁመትና ስፋት ባልበለጠ አንድ ሳጥን ወይም መሳቢያ የመሰለ ነገር በበሬ በሚጐተት ጋሪ ሲጓጓዝ ይታያል፡፡ ከበታቹም በትላልቅ ፊደላት እነዚህ ሁለት ቃላት ተቀርጸዋል- “ARCHA CEDERIS”

ምሰሶውን ከቀኝ ወደግራ እየዞርኩ ስመለከት ምንም እንኳን ቅርጹ የተጐዳና የተሸረሸረ ቢሆንም፣ ላዩ ላይ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት ቃላት የሚደጋገሙባቸው ሀረጎች ተቀርፀዋል፡፡ HIC AMICITUR ARCHA CEDERIS

ጽሑፉ ጥንታዊ በመሆኑ ለመረዳት የሚያስቸግር ነው፡፡ ላቲን ወይም ከላቲን ጋር የሚመሳሰል ቋንቋ መሆኑ ግን ገባኝ፡፡ “አርካ” (ARCHA) የሚለው ቃል ARK (የቃል ኪዳን ታቦት) ከሚለው ጋር የተያያዘ ትርጉም እንዳለው ተገነዘብሁ፡፡ ቅርጹ ላይ የሚታየው ሳጥን ወይም መሳቢያ (መጠኑ ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር) በኦሪት ዘፀአት ላይ ስለታቦቱ ከተገለፀው ጋር የሚቀራረብ ነው፡፡



ግምቴ ትክክል ከሆነ፣ የታቦቱ ቅርጽ ንግሥተ ሳባ አጠገብ መሆኑ በሻርትር ካቴድራል ጠራቢዎች ላይ፣ ለጊዜው ግልፅ ባልሆነ መልኩ፣ ክብረ ነገሥት ላይ የተጻፈው ታሪክ ተጽዕኖ አሳድሮባቸዋል የሚለውን መላምቴን ያጐላዋል፡፡ ቀራጮቹ ንግሥቲቱን አፍሪካ ውስጥ ማስቀመጣቸው በደቡብ ታዛ ካየሁት የበለጠ መላምቴን እውነት ያስመስለዋል፡፡ ስለሆነም በምሰሶዎቹ ላይ የተቀረጹት ምስሎች የታቦቱ ስለመሆናቸውና ከሥራቸውም በላቲን የተጻፉትን ቃላት ትርጉም ማወቅ እንዳለብኝ ወሰንኩ፡፡

ወደ ሰሜኑ ታዛ መሄጃ መንገድ ላይ ቁጭ ብዬ የጐብኚዎች መመሪያ መጽሐፎቼን ሳጠና፥ በምሰሶዎቹ ላይ ስላሉት ቅርጻ ቅርጾች ሁለት የሚስቡ ነገሮች አገኘሁ፡፡ አንደኛው፣ ምንም እንኳን የጽሑፉን ትርጉም ባይፅፍም፣ ምስሉ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል፡፡

ሁለተኛው ትርጉም ቢሰጥም፣ ባለችኝ አነስተኛ የላቲን ዕውቀት ትክክለኛነቱን ስለተጠራጠርኩ የባለሙያ ምክር እንደሚያስፈልገኝ ገመትኩ፡፡ የለንደን ዩኒቨርሲቲ የሥነጥበብ ታሪክ ምሁር የሆኑትን ፕሮፌሰር ፒተር ላስኮን ስለማውቃቸውና እሳቸውም በወቅቱ ፈረንሳይ ውስጥ ዕረፍት ላይ ስለነበሩ ስመለስ ይህን ጉዳይ ላነሳባቸው ወሰንኩ፡፡

በመሆኑም ጽሑፎቼን በጥንቃቄ ገለበጥኩ፡፡ የሰሜናዊውን መግቢያ በር ገጽታ በሥዕል መልክ መንደፍ ጀመርኩ፡፡ ይህን እያደረግኩ እያለሁ አንድ ትልቅ ትርጉም ያለው ነገር ተመለከትኩ፡፡ የታቦቱ ቅርጽ ያለው ከመግቢያው ታዛ ፊት ለፊት ባለው ቋሚ ምሰሶ ላይ ቢሆንም፣ የተቀመጠው የብሉይ ኪዳን ካህንና ንጉሥ በነበረው በመልከ ጼዴቅና በንግሥተ ሳባ መካከል ለሁለቱም እኩል ርቀት ባለው ቦታ ላይ ነበር፡፡ የንግሥተ ሳባ ሐውልት በቀኝ ክንፍ መተላለፊያው በኩል ቆሟል፡፡ ሦስቱንም ቅርጾች በምስለው ንድፍ ላይ በሦስት ማዕዘን መስመሮች ማያያዝ ቻልኩ፡፡ መልከ ጼዴቅና ንግሥተ ሳባ በአንድ ተርታ ቆመዋል፡፡ ታቦቱ ደግሞ ከበላይ ይታያል፡፡

ይህን ብቻ አይደለም የተመለከትኩት፡፡ ታቦቱ ከመልከጼዴቅ አቅጣጫ ወደንግሥተ ሳባ አቅጣጫ በጋሪው ሲጓዝም ያመለክታል፡፡ የነዚህን ቅርጾች ቅንጅት ልብ ብሎ ለተመለከተው ሁኔታው በአጋጣሚ የተፈጠረ ሳይሆን ሆን ተብሎ መልዕክትን ለማስተላለፍ የተቀረፀ ይመስላል፡፡ በሻርትር ሕንፃ ላይ ያሉትም ቅርጾች እንዲሁ በዘፈቀደ የትለያዩ ታሪኮችን ለመግለጽ የተደረደሩ አልነበሩም፡፡ ይልቁንም የሻርትር ቀራጮች፥ በክብረ ነገሥት ላይ የተገለጸውን የንግሥተ ሳባን ታሪክ ማወቅ አለባቸው፡፡ መቼም ከተመለከትኳቸው የቅዱሳን ቅርጾች በመነሳት በርግጠኛነት ይህ ነው ብዬ ከአንድ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ባልችልም፥ መልከ ጼዴቅ ታቦቱ ከእስራኤል መወሰዱን ሲያመለክት፣ ንግስተ ሳባ ደግሞ የታቦቱን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ታመለክታለች፡፡

እንደገና ትኩረቴን በመልከ ጼዴቅ ሐውልት ላይ አደረግሁ፡፡ ቀሚም ምስሉን መንደፍ ጀመርኩ፡፡ ቀስ በቀስ በርካታ ነገሮች እየተከሰቱልኝ መጡ፡፡ ክቀኝ እጁ በታች ጽንሐሕ (የመስዋዕተ ዕጣን ማሣረጊያ) ይታያል፡፡ ይህን የመሰሉ ጽንሐሖች በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የቅዳሴ ሥርዓት ላይ አይቻለሁ፡፡ በተጨማሪ መልከ ጼዴቅ በግራ እጁ መያዣው ቀጠን፣ ረዘም ያለ ጽዋ ይዟል፡፡ በውስጡ ግን ፈሳሽ ሳይሆን የያዘው የዓምድ ቅርጽን ነው፡፡

የጉብኚዎች መመሪያ መፃሕፍትን ባገላበጥ፣ ስለጽንሐው የተሰጠ መግለጫ የለም፡፡ ስለጽዋው ግን የተምታታ መግለጫ ነበረ፡፡ አንዱ መግለጫ የለም፡፡ ስለጽዋው ግን የተምታታ መግለጫ ነበረ፡፡ አንዱ ምንጭ የመልከ ጼዴቅ እዚህ የመኖር ትርጉሙ የክርስቶስን መምጣት የሚያመለክት ሲሆን፣ በእጁ ያለው ጽዋና በውስጡ ያለው ነገር የሚገልጸው "ሕብስቱንና ወይኑን፣ የቅዱስ ቁርባን ምልክትን ነው" ይላል፡፡

ሐውልቱን የሚያሳየው ፎቶ ሥር "መልከ ጼዴቅ ጽዋውን ጨብጧል፡፡ በውስጡም ድንጋይ አለው" ይልና ቀጥሎ "ከዚህም ጋር የፖልፍራም ቮን ኢስከንባኽን ግጥም ማገናኘት ይቻላል" ይላል፡፡ "እርሱም ቅዱስ ጽዋ የተባለው ድንጋይ ነው ብሏል፡፡"

ምንም የተጨበጠ ነገር ሳላገኝ የሰሜኑን መግቢያ በር ለቅቄ በካቴድራሉ ጀርባ ካለው መናፈሻ በመሄድ ከባለቤቴና ከልጆቼ ጋር ተቀላቀልኩ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ሻርትርን ለቀን ወደቦርዶ እና ቢያሪትዝ አቅጣጫ አመራን፡፡ በስተምሥራቅ ወደኮት ዳዙር በማምራትም በታርን ኤ ጋሮንኢኔ ወረዳ ወደምትገኘው ቱሉዝ ከተማ ደረስን፡፡ ከዚያም በያዝኩት ጥሩ ካርታ ረዳትነት የሥነ ጥበብ ታሪክ ተመራማሪ የሆኑትን የፕሮፌሰር ፒተር ላስኮን ቤት ፈልገን አገኘን፡፡

## ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን?

ከፒተር ላስኮን ጋር ግማሽ ቀን አሳለፍን፡፡ ቀደም ሲልም ስለአፍሪካ ቀንድና ስለኢትዮጵያ እንደምጽፍ ያውቃሉ፡፡ ዛሬ ድንገት አቅጣጫዬን ቀይሬ በመካከለኛው ዘመን ስለተሠራው የፈረንሳይ ካቴድራል ጉትት ማሳደሬ ገርሟቸው ጠየቁኝ፡፡ እኔም በሻርትር ሰሜናዊ መግቢያ በር ታዛ ላይ ያየሁት ሐውልት የተቀረጸው በክብረ ነገሥት ታሪክ ላይ ተመርኩዞ ሳይሆን አይቀርም አልኳቸው፡፡ ካህንና ንጉሥ የነበረው መልከ ጼዴቅ ከነጽዋው ጥንታዊቷን እስራኤል ሊወክል ይችላል፡፡ ንግሥተ ሳባም ከአፍሪካዊ ባርያዋ ጋር ኢትዮጵያን ልትወክል ትችላለች፡፡ በመካከላቸው ደግሞ ታቦቱ አለ፡፡ አቅጣጫውንም ወደኢትዮጵያ አድርጓል፡፡ ስለዚህም መልእክቱ ታቦቱ ከእስራኤል ወደኢትዮጵያ መሄዱን ይጠቁማል፡፡ ክብረ ነገሥትም ይህንኑ ነው የሚለው፡፡ እርስዎንስ ምን ይመስልዎታል?" ስል ጠየቅኋቸው፡፡

"እውነቱን ለመናገር ይሄ ሊታመን የማይችል ነገር ነው፡፡"

"ለምን?"

"የኢትዮጵያን ልምዶች የሚመለከቱ አንዳንድ ነገሮች በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደአውሮፓ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ይህንም በተመለከተ አንድ ጽሑፍ ማንበቤ ትዝ ይለኛል፡፡ እውነተኛነቱን ግን እጠራጠራለሁ፡፡ የክብረ ነገሥት ታሪክ በሻርትር በወቅቱ ቢታወቅም በምን ምክንያት ተነሳስተው የካቴድራሉ ቅዱሳን ቅርጾች ውስጥ ታሪኩን ሊያስገቡ እንደቻሉ ሊገባኝ አይችልም፡፡ ፍፁም የማይመስል ነገር ነው፡፡ በተለይ በሰሜኑ መግቢያ ላይ የሰፈረው የብሉይ ኪዳን ታሪክ የክርስቶስን መምጣት የሚያመለክቱ ነቢያትን የያዘ ነው፡፡ የመልከ ጼዴቅም መኖር ይህንኑ ለማመልከት ነው፡፡ በዕብራውያን መጽሐፍም መልከ ጼዴቅ ከክርስቶስ ጋር ተቆራኝቷል፡፡"

"በእጁ ጽዋ እንደያዘ ነው የሚታየው፡፡ ጽዋውም ውስጥ የዓምድ ቅርጽ የመሠለ ነገር አለ፡፡"

"ምናልባት በቅዱስ ቁርባን ጊዜ የሚቀርበውን ሕብስትና ወይን ሊወክል ይችላል፡፡"

"ከያዝኳቸው የጉብኚዎች መመሪያ መፃህፍት አንዱ የሚለውም ይህንኑ ነው፡፡ ሌላ ቦታ ደግሞ በጽዋው ውስጥ ያለው ድንጋይ ነው ይላል፡፡"

ፒተር ላስኮን ግር ብሏቸው፣ "እንዲህ ያለ ነገር ሰምቼም አላውቅም፡፡ ይሄ ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት አለው ከምትለውም የባሰ ነው..." ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ካሰቡ በኋላ "እስ ቡዬ የጠቀስኩልህ ጽሑፍ ስለኢትዮጵያዊ አለተባበሮች ወደአውሮፓ አሕጉር በመካከለኛው ዘመን ዘልቆ መግባት..."

"አዎን፡፡"

"ግር የሚለው ግን የሚያወሳው ስለቅዱሱ ጽዋ ነው፡፡ በትክክል ካስታወስኩ በፖልፍራም ቮን ኢስከንባኽ የድንጋይ ጽዋ መባሉ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ባሕል ተጽዕኖ የተነሳ መሆኑን ይናገራል፡፡"

"ይገርማል፡፡ ፖልፍራም ቮን ኢስከንባኽ በጉብኚዎች መመሪያው ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ለመሆኑ እሱ ማን ነው?"

በመካከለኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከታወቁት ገጣሚዎች አንዱና ስለ ቅዱሱ ጽዋ የጻፈ ሰው ነው፡፡ በ"ፓርዚቫል" በሚል ርዕስ ጉዳይ ላይ ትልቅ መጽሐፍ ጽፏል፡፡

"ይሄ የእሮፒራ ስም አይደለም እንዴ?"

"አዎን፣ ዋግነር፣ በፖልፍራም ሥራ ላይ ተመርኩዞ የሠራው ነው፡፡"

"ፖልፍራምስ መቼ ነው መፅሀፉን የጻፈው?"

"በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ወይም በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ፡፡"

"የሻርትር ካቴድራል ሰሜናዊ መግቢያ በር የተሠራበት ዘመን መሆኑ ነው?"

"አዎ ነ።"

ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለን ቆየን። ቀጥሉ "የዎልፍራም ሥራ ላይ የኢትዮጵያ ባሕል ተጽዕኖ አለበት የሚለውን ጽሁፍ ርእስ ያስታውሱታል?" ስል ጠየቅኋቸው

"አላስታውሰውም። ካነበብኩት ቢያንስ ሃያ ዓመታት አልፈዋል። ብቻ! ማነው? አዶልፍ መሰለኝ የፃፈው። ይህ ስም አእምሮዬ ውስጥ ተቀርፆአል። ዎልፍራም ጀርመናዊ ስለነበር ስለጀርመን ሥነጽሑፍ የሚያውቅ ሰው መፈለግ አለብህ።"

በልቤ ያን እንደማደርግ እየወሰንኩ ከሻርትር ካቴድራል የለቀምኳቸውን ቃላት በመተርጎም እንዲያግዙኝ ጠየቅኋቸው። በቅድሚያ የጉብኚዎቹ መጽሐፍ የሰጠውን ትርጉም ብነግራቸው ትርጉሙ ፊጽሞ የተሳሳተ መሆኑን በመግለጽ ARCHA ማለት ARK (ታቦት) ማለት ሲሆን፣ CEDERIS የተባለው ግን የተደቃቀለ ቃል መሆን አለበት። FOEDERIS ለማለት ይመስላል። ትርጉሙም COVENANT (የቃል ኪዳን) ማለት ነው። ስለሆነም ARCHA CEDERIS ተብሎ ያየኸው ሲተረጎም፣ ቃል ኪዳኑ ያደረበት ታቦት "ARK OF THE COVENANT" ማለት ነው አሉ።

ሌላው አማራጭ CEDERIS የተባለው ሥርወ ግሥ Cedere ተብሎ ከተወሰደ ትርጉሙ መልቀቅ ወይም መተው አለያም ወደሌላ ቦታ መሄድ ይሆናል። በዚህ መልኩ ከተተረጎመ ARCHA CEDERIS የተወሰደው የቃል ኪዳን ታቦት፣ የተውከው ወይም ትቶህ የሄደውን ማለት ሊሆን ይችላል።

ረዘም ያለውን ሀረግ በተመለከተ ችግሩ የሁለተኛው ቃል አራተኛው ፊደል አለመነበብ (አለመታየት) ነው። በጉብኚዎች መመሪያዩ መሠረት ቃሉ "T" ነው። ሁለት "T" ፊደላትን በምህፃረ ቃል ለማስቀመጥ የተደረገ ሙከራ መሆን አለበት። ምክንያቱም በላቲን ቋንቋ ውስጥ አንድ "T" ያለበት "AMITITUR" የሚባል ቃል የለም። እንዲያ ከሆነ HIC AMITTIUR ARCHA CEDERIS ሲተረጎም "እነሆ ታቦት ሆይ፣ ከኛ እጅ ወጥተሃል" ወይም በሌላ አማራጭ "እነሆ ይሄድ CEDERIS የተባለው ቃል መሆን ከነበረበት ትርጉሙ "እነሆ ይሄድ ከኛ የወጣው የቃል ኪዳኑ ታቦት" ማለት ይሆናል። ደግሞም የሁለተኛው ቃል አራተኛው ፊደል "T" ከመሆን "C" ከሆነ (በርግጥም ሲያዩት ይህን ይመስላል) ዐረፍተ ነገሩ ሲነበብ HIC AMICITUR ARCHA CEDERIS ሲተረጎም፣ "የቃል ኪዳኑ ታቦት እዚህ ተደብቋል"፣ ወይም "ከእኛችሁ የሚወጣው ታቦት እዚህ ተደብቋል" ማለት ነው።

ፒተር ላስኮ መዝገበ ቃላቱን እየዘጉ "ይህ AMICITUR የሚለው ቃል መሸፈንም ሊሆን ይችላል። ብቻ መሸፈንም ሆነ መደበቅ ነገሩ የሚያስተላልፉት ሃሳብ አንድ ዓይነት ነው። አይመስልህም? ነገሩ ሁሉ ግን እንቆቅልሽ ነው የሚመስለው" አሉ በመጨረሻ።



በዚህ ከልቤ ተስማማሁ። በርግጥም ሁሉም ነገር እንቆቅልሽ ነበር። በፈረንሳይ በቆየሁባቸው ጊዜያት የማስበው በሰሜናዊው መግቢያ በር በሻርትር ካቴድራል ስለተቀረጹ ኀውልቶች ነበር። በተለይ በሬዎቹ በሚጉትቱት ጋሪ ላይ የተቀመጠው ሳጥን የጉዞ አቅጣጫ ወደንግሥተ ሳባ ሐውልት መሆን ከአዕምሮዬ ሊጠፋ አልቻለም። በመሆኑም ጉዞው ወደኢትዮጵያ ተደርጓል የሚለውን ግምት ከአእምሮዬ ላውጣው ብል አልተቻለኝም።

በይሆናል ውስጥ ስጥሚ ምንም ግሪጋሪዎች በሌለው ጉዳይ ውስጥ መዳከሬ ይታወቀኛል። የሻርትር ሕንፃ ሠሪዎች በምንም ዓይነት ሁኔታ ይህን የመሰለ ርእስ በኢትዮጵያ እፈታሪክ ላይ ተመርኩዘው ይሠራሉ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው ያሉትን የፕሮፌሰር ፒተር ላስኮን አባባል ሙሉ በሙሉ ተቀበልኩኝ። ይሁንና በሌላ በኩል ደግሞ የሚያጓጓ ነገር በአእምሮዬ ተጫረ። ይኸውም ምናልባት የሰሜኑን መግቢያ ያነጹት ሰዎች ለሚመጣው ትውልድ ምሥጢራዊ ኮድን በመሥራት ይኼ በዓለም እጅግ ክቡርና ውድ የሆነ ቅርስ የሚገኝበትን ቦታ ለመጠቆም አስበው ሠርተውት እንደሆነስ ብዬም አሰብኩ። በእውነት ይህ የቃል ኪዳን ታቦት በእሬት ዘመን ከእስራኤል ወጥቶ በኢትዮጵያ ተደብቆ ይሆን? ምናልባት የትንሿ ቅርጽና በሥሯ የተጻፈው እንቆቅልሽ ጽሑፍ እውነተኛው ትርጉም ይህ ሊሆን ይችላል? ከሆነ ነገሩ የሚመስጥ ስለሆነ በ1983 ዘግቼው የነበረውን ጉዳይ በመከለስ የአክሱማውያኑን ጥንታዊ ታሪክ በድጋሚ መመርመር ሊኖርብኝ ነው።

## ቅድስት ማርያም፣ ጽዮውና የቃል ኪዳኑ ታቦት

ሚያዝያ፣ 1989 ከፈረንሳይ እንደተመለስኩ ረዳቴን በፕሮፌሰር ፒተር ላስኮ የተነገረኝን የአዶልፍ ጽሑፍ እንዲያፈላልግ ነገርኩት። ጽሑፉ የትና መቼ እንደታተመ የማውቀው ነገር የለም። በምን ቋንቋ እንደተጻፈም አላውቅም። ሆኖም ረዳቴን ስለዚሁ ጉዳይ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችን እንዲጠይቅና በተለይ የጀርመን ሥነ ጽሑፍ በሚገኝባቸው ቦታዎች ላይ እንዲያተኩር አደረግኩት።

በበኩሌም ስለጽዋው የተጻፉ የተለያዩ መጻሕፍትን ገዛሁ። ከነዚህም ውስጥ በክሬቲየን በ1182 የተጻፈ "ኮንት ዱ ግራል" የተባለ ያልተቋ ጽሑፍ፣ በሮር ቶማስ ማሎሪ የተደረሰ "ለ ሞር ደ አርትር" የተባለ በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈ እና በዎልፍራም ቮን ኢስከንባኽ የተደረሰው "ፓርዚቫል" የተባለው የሻርትር ካቴድራል ሰሜናዊ ታዛ በታነጸበት ዘመን፣ ማለትም በ1195 እና በ1210 መካከል የተጻፉ ይገኙባቸዋል።

እነዚህን መፃህፍት ሳነብ ከሁሉም በላይ የማሎሪ ድርሰት ጽዋውን ፍሊጋ ዙሪያ የተተረኩ ታሪኮችና ፊልሞች መነሻ መሆኑን ተገነዘብሁ። በተቃራኒው የዎልፍራም ደግሞ ምድራዊና የሰውን ልጅ

ባሕርይ የሚያንጸባርቅና የጽዋውን ተምሳሌትነት በተመለከተ ምንም የማይል ነው።

በማሉሪ አባባል፥ ቅዱሱ ነገር፣ "ከወርቅ የተሠራ ጽዋ" እና "ንጽሕት በሆነች-አገልጋይ የተወሰደ፡" "የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ደም ከፋይ ያለበት ነው።" እንደማስታውሰው ይህ ቅዱስ ነገር ብዙ ጊዜ በጽዋው ይመሰላል። (እንዲያውም የአርማትያው የሴፍ ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ጊዜ መስቀሉ ሥር ተገኝቶ ደሙን የተቀበለበት ጽዋ ነው ይላል"።

እኔም የዚህ አስተሳሰብ ተፅዕኖ ስለነበረብኝ ጽዋው ከዚህ የተለየ ነገር ሊሆን ይችላል ብዬ ማሰብ አዳገተኝ። ሆኖም የፓርዚቫል ደራሲ ፈረንሳይ አገር ከተገነዘብኩት በተመሳሳይ ድንጋይ ነው ብሎ ፅፏል። ይህንን አባባሉን ከድርሰቱ እንመልከት።

> ለመሞት የተቃረበ ሰው ቢሆንም እንኳን፡ ድንጋይዋን ካየ ከዚያች ዕለት አንስቶ ሳምንቱን ሙሉ አይሞትም። የሰውነት ወዘናውም አይለወጥም። ሌላው ቀርቶ ማንም ሰው (ወንድ ይሁን ሴት) ጽዋዋን ለሁለት መቶ ዓመታት ያህል ቢመለከታት የፊቱ ገጽታ የልጅነት ወዘናውን ሳይለቅ ሊቆይ ይችላል። ድንጋዩ ይህንን በሰባሽ የሆነውን የሰው ሥጋና አጥንት የማለምለም ኃይል አለው። ይህም ድንጋይ "ጽዋ" ይባላል።

ክሬቲዬን የተባለው ፈረንሳዊ ደራሲም በሌላው ታሪክ ውስጥ ይህን ቅዱስ ነገር የያዘች ንጽሕት አገልጋይ መሆኗን ይናገራል። ቅዱሱ ነገር ጽዋ መሰል መሆኑንም ያምናል።

"የቅዱሱ ደሙን" ተምሳሌት፥ ከ"ቅዱሱ ዕቃ" ጋር ማያያዝ የመጣው የክሌርቮው ቅዱስ በርናርድ በ1112 የደናግላን መነኩሳትን ሥርዓት ማህበር በተቀላቀለ ጊዜ ነው። ይህ ሰው ቃላቅ ተደማጭነት የነበረውና የጉቲክ ሥነሕንፃ እንዲስፋፋ ያደረገ ሲሆን፣ የሻርትር ካቴድራል የሰሜኑ ክፍል ሲሠራ በ1134 ወከፍተኛ ስልጣን ላይ የነበረ ሰው ነው። በ1153 በሞት ከተለየም በኋላ ሐሳቦቹና የደነገጋቸው ሥርዓቶች ሥራ ላይ ውለዋል። ስለሆነም በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ በደናግላን መነኩሳት አማካኝነት፣ የቅዱሱ ነገር ምንነት ትርጉም ከሐዲስ ኪዳን ጋር በመያያዙ ቀድሞ የነበረው የቅድመ ክርስትና ትርጉሙ ተለውጧል። ስለሆነም ዎልፍራም በቅኔው ለቅዱሱ ነገር ድንጋይነት የተናገረው ሙሉ በሙሉ ተረስቶ ክሬቲዬን (ጻሕል/ጽዋ መሰል) ያለውን በመቀበል የክርስቶስ ደም ማስቀመጫ ተባለ። በጣም ያስገረመኝ ነገር፣ በአውሮፓ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ይህን ሃሳብ ተቀብለው እንዴት እንደተረጎሙት ነው። በየመዝሙሮቻቸው፣ በየቅዳሴዎቻቸውና፣ በየመልእክቶቻቸው ውስጥ ጽዋውን ከተቀደሰችው ከድንግል ማርያም ጋር አመሳስለውታል። ጽዋው የክርስቶስ ደም በውስጡ እንደሚቀመጥበት ሁሉ፣ እሱን ከመውለዷ በፊት ቅድስት ማርያም ክርስቶስን በማህጸኗ ውስጥ ተሸክማዋለች። ስለሆነም የማርያም ምሳሌ ነው ይላሉ።



በዚህ አመለካከት መሠረት "ማርያም ወላዲተ አምላክ (እግዚአብሔርን የወለደች)"፥ የተቀደሰች ጽዋ በመሆኗ ሥጋ የተዋሐደውን መለኮት ተሸክማለች። በዚህም የተነሣ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሉሬቶ የመዝሙር (የፀሎት) መፃህፍት ማርያም መንፈሳዊ የክብር ጽዋ፥ ራስን መሰዋዕት የማድረግ ጽዋ ተብላለች።

ይህ ተምሣሌት ለምን ሊስበኝ ቻለ? በቀላሉ የሉሬቶ የፀሎት መፅሃፍት ቅድስት ድንግል ማርያምን ARCHA FOEDERIS ስላላት ነበር። በላቲን የዚህ ቃል ትርጉም "የቃል ኪዳኑ ታቦት" ማለት መሆኑን አውቄያለሁ። በተጨማሪ ባደረግኩት ምርምር የክሌርቮ ቅዱስ በርናርድ በብዙ ጽሑፎቹ፥ ማርያምን ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ያመሳስላታል። ወደ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ስንመለስ፥ የሚላኑ ጳጳስ ቅዱስ አምብሮዝ "የቃል ኪዳኑ ታቦት ትንቢታዊ መልእክት የማርያምን ተምሳሌት ማስተላለፉ ሲሆን፥ ታቦቱ የብሉይ ኪዳን አሠርቱ ትዕዛዛትን በውስጡ እንደያዘ ሁሉ እርሷም የአዲስ ኪዳን ሕግ ባለቤት የሆነውን ክርስቶስን በማኅፀኗ ውስጥ ተሸክማለች።" ብለዋል።

ይህ አስተሳሰብ በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብቻ ሳይሆን፥ በዘመናችን የክርስትና አምልኮት ውስጥ ይታያል። ለምሳሌ[1] ወደ እስራኤል በተጓዝኩበት ወቅት በ1924 የተሠራች አንዲት ትንሽ ቆንጆ የዶሚኒካን ቤተክርስቲያን ላይ "ለማርያም ድንግል የቃል ኪዳኗ ታቦት" የተሠራ የሚል ፅሁፍ አለ።

ቤተክርስቲያኗ በቴልአቪቭና በኢየሩሳሌም መካከል ባለው በኪሪያት ጄሪም የምትገኝ ስትሆን ሰባት ሜትር ከፍታ ያለው የሕንፃው ጉልላት የታቦቱን ቅርጽ ያሳያል።

የቤተክርስቲያኒቱ አስተዳዳሪ የሆኑት አማሆይ ራፋኤል ሚካኤል እንዳስረዱኝ፣

> እኛ ማርያምን እንደ ሕያው ታቦት እንቆጥራታለን። ማርያም የኢየሱስ እናት ነች፤ እሱም የታቦቱና የሕጉ ጌታ ነው። አሠርቱ ትዕዛዛት የተጻፉበትን ጽላት በታቦቱ ውስጥ ሙሴ እንዳስቀመጠው ሁሉ፥ እግዚአብሔርም በማርያም ማህፀን ኢየሱስን አስቀመጠው። ስለዚህም እርሷ ሕያው ታቦት ናት።

ታቦቱና ጽዋው በእጅጉ የተለያዩ ነገሮች ሆነው ሳሉ፥ ለአንድ ነገር የጋራ መጠሪያ ሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ የመቅረባቸው ጉዳይ ለኔ ልዩ ትርጉም ነበረው። ማርያም "ሕያው ታቦት" እና "ሕያው ጽዋ/ጻሕል" ተብላ ከተጠራች እነዚህ ሁለቱ የተቀደሱ ነገሮች የተለያዩ ነገሮች ሳይሆኑ እንደአንድ መሆናቸውን ማሰብ ጀመርኩ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ በሻርትር ካቴድራል ያየሁትን ነገር ትክክለኛነት እንደሚያረጋግጥልኝ ገመትኩ። ትክክል ከሆንኩ መልከ ጼዴቅ በእጁ የያዘው ጽዋ ከነድንጋዩ የማርያም ምሳሌ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ታቦቱን (ጽላቱን) ይወክላል።

ይኼ አተረጓጎም ደግሞ፣ በሻርትር ካቴድራል የደረስኩበትን መላ ምት አጠናከረልኝ። በሻርትር ካቴድራል ሰሜናዊ መግቢያ በር ላይ ያሉት የቅዱሳን ሐውልቶች የሚያመለክቱት ምሥጢር ይህ ቅዱስ ታቦት ወደኢትዮጵያ መወሰዱን ነበር። ሆኖም ይህን ግምቴን እውነት ሊያደርግልኝ የሚችል ተጨባጭ ማስረጃ አልነበረኝም። ነገር ግን ጊዜን የሚፈጅና ወጪን የሚጠይቅ ጠለቅ ያለ ምርምርና ጥናት ለማካሄድ መነሻ የሚሆነኝ ተጨባጭ ይዘት ያለው ጉዳይ መያዝ እንጂ፣ በአንዳንድ መልካም አጋጣሚዎች ወይም ሊከሰቱ በሚችሉ ስሜቶች ላይ ብቻ በመመርኮዝ መሳሳት እንደሌለብኝ ወሰንኩ።

ብዙም ሳልቆይ በሰኔ ወር 1989 ረዳቴ ከዚህ በፊት ፒተር ላስኮ ጠቅሰውልኝ የነበረው ጽሑፍ የሚገኝበትን ቦታ ማወቁን ገለፀልኝ። የዚህ ጽሑፍ መገኘት ያሳደረብኝ መነሳሳት ለቀጣዩቹ ሁለት ዓመታት ፍለጋዬ ብርታትን ሰጥቶኛል።

## ሥነ ጽሑፋዊ ተጽዕኖ ወይስ ከዚያ በላይ?

የጽሑፉ ርዕስ "ለፓርዚቫል መሠረት የሆኑ ምሥራቃውያን ምንጮች" (New Light on Oriental Sources for Wolfram's Parzival) የሚል ሲሆን፣ በ1947 "የአሜሪካ ዘመናዊ ቋንቋዎች ማህበር መጽሔት" (Publications of the Modern Language Association of America) ላይ ወጥቶ ነበር። ደራሲዎ ሔለን አዶልፍ ስለመካከለኛው ዘመን ጉዳዮች በመጻፍ የታወቁና በተለይ ደግሞ ስለቅዱሱ ጽዋ/ጻሕል የራሳቸው የተለየ አመለካከት የነበራቸው ናቸው።

በዚህ ምርምራቸውም ስለጉዳዩ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው ሁለት ምሁራን እንደረዷቸው ጽፈዋል። ዎልፍራም በዘመኑ የታወቀ የጀርመን ባለቅኔ ነበር። "ፓርዚቫል" በተባለው የሥነ ጽሑፍ ሥራው ውስጥ የተጠቀመበትን ሃሳብና ገፀባሕርያት የወሰደው ከርሱ በፊት ከነበረው ከፈረንሳዩ ባለቅኔ ክሬቲየን ሲሆን፣ ሥራውም "ኮንት ዱ ግራል" (Conte du Graal) ይባላል።

ታላቁ ፈረንሳዊ ገጣሚ ዝነኛ ሥራውን አላጠናቀቀውም ነበር። በጥቂት ዓመታት ውስጥ ግን ዎልፍራም ይህን ጥሩ ጅማር ያለው ፅሑፍ አስፋፋው። ሆኖም በምሬት ክሬቲየን "ስህተት መፈፀሙንና" የራሱ የዎልፍራም የሆነው ጀርመንኛ ፅሑፍ "ትክክለኛው ታሪክ" መሆኑን ይናገራል። ሆኖም የተቃውሞው አስፈላጊነት ግን ግልፅ አይደለም። ምክንያቱም ብዙውን ሃሳብ ከፈረንሳዊው ነው የወሰደው። ይሁንና በገሃድ የሚታየው ልዩነት በጽሑፉ ውስጥ "ቅዱስ ጽዋ" የተባለውን "ቅዱስ ደንጊያ" በማለት ትርጉም የለሽ ፈጠራን መጨመሩ ነው።

የሔለን አዶልፍን ጽሑፍ ሳነብ የተረዳሁት ዎልፍራም፣ "ፓርዚቫል" የተባለ ጽሑፉን በፃፈበት ጊዜ፣ ክብረ ነገሥትን በሚገባ ያውቅ እንደነበር ነው። ቅዱስ ታቦት የተባለው ነገር በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መኖሩም የሚያመለክተው፣ የመጀመሪያው



የቃል ኪዳን ታቦት በክብረ ነገሥት ውስጥ እንደተጻፈው ወደዚያች አገር መሄዱን በመሆኑ፣ በዎልፍራም ሥራዎች ውስጥ ክብረ ነገሥት በተዘዋዋሪ መንገድ ተንጸባርቋል ባይ ነች ሔለን አዶልፍ።

ሔለን "የክብረ ነገሥት ታሪክ በዎልፍራም እጅ እንዴት ሊገባ ቻለ?" የሚለውን ጥያቄ መልስ በርግጠኛነት አያውቁም። ምናልባት በጊዜው ይዘዋወሩ የነበሩ አይሁዶች ወደአውሮፓ ይዘውት መጥተው ይሆናል ነው የሚሉት። ምክንያቱም "በዚያን ዘመን በአይሁዶች፣ በአረቦችና በክርስቲያኖች መካከል እንደአገናኝ ሆነው ይሠሩ ስለነበርና በኢትዮጵያም ውስጥ በወቅቱ የአይሁድ ሕዝብ ይኖር ስለነበር፤ የታሪኩ ወደአውሮፓ መዝለቅ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል።"

በአጭሩ የሔለን አዶልፍ ጽሑፍ ዓይኔን ከፈተልኝ። ምክንያቱም የጀርመኑ ባለቅኔ ዎልፍራም ክብረ ነገሥት ላይ በመንተራስ ልብ ወለድ ታሪክ አስመስሉ ቢጽፈውም፣ በውስጡ ግን ሆን ብሉ ምሥጢራዊ "ኮድ" ስለታቦቱ ማስቀመጡ ስለሆነ ይህንኑ ለመፍታት ጥረቴን ቀጠልኩ።

በመጀመሪያ ዎልፍራም የጻፈው ድርሰት የቃል ኪዳኑን ታቦት መገኛ የሚገልጽ ሥውር ጽሑፍ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ነበረብኝ። ለጊዜው በሔለን አዶልፍ የተገለጸውንና ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት ወደጐን በመተው የዎልፍራምን ጽሑፍና ስለጽላቱ በብሉይ ኪዳን የተነገሩትን፣ እንዲሁም በሌሎች የአይሁዳውያን የታሪክ ምንጮች የተነገሩትን በማነጻጸር አሳማኝ ነገር አገኝ እንደሆን ምርምሬን ለመቀጠል ተነሣሁ። ዎልፍራም፣ በክሬቲየን ታሪክ ውስጥ የተነገረውን ጽዋ ወደደንጊያ ቀይሮ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያስፈረበት ምክንያት፣ የፈረንሳዩ ባለቅኔ ስለጽዋው ምንነት በግልጽ ባለመረዳቱ የተነሣ በተፈጠረው ቀዳዳ በመጠቀም ነበር። ስለሆነም የጀርመኑ ባለቅኔ፣ ስለጽዋው ሳይሆን በውስጡ ስላለው ይዘት የራሱን አተረጓጎም ሰጧል። በርግጥም ታቦቱ እንደማህደር ይተረጐማል፤ እንደጽዋው ማለት ነው። ታቦቱ በውስጡ ደንጊያ አለው፤ ሊያውም ሁለት የከበሩ የደንጊያ ጽላቶችና በላያቸው ላይ አሠርቱ ትዕዛዛት በእግዚአብሔር ጣት የተፃፉውባቸው። ከጊዜ በኋላም እንደተረዳሁት፣ የዎልፍራምም ጽዋ ላይ እንደጽላቱ ሁሉ ሰማያዊ ሕግጋት ተቀርፀውባችዋል።

ዎልፍራም በድርሰቱ ውስጥ ጽዋ ብሉ የሰየመው ነገር ሰዎች በተጨነቁና በተቸገሩ ጊዜ ፊቱ በመንበርከክ፣ ምክርን ሲጠይቁት መልሶ ይሰጣቸው እንደነበር ያስረዳል። ከብሉይ ኪዳን ታሪክም ብዙ ጊዜ የእስራኤላውያንን ሕልውና የሚፈታተን ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ታቦቱ ከፈጣሪ ጋር ለመገናኘት ያገለግላቸው እንደነበር ይታወቃል። በመጽሐፈ መሳፍንት ም20፣ 27-28 እንዲህ ይላል።

> በዚያም ዘመን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት በዚያ ነበረና፤ በዚያም ዘመን የአሮን ልጅ የአልአዛር ልጅ ፊንሐስ በፊቱ ይቆም ነበርና፣ የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔርን፣

ከወንድሞቻችን ከብንያም ልጆች ጋር ለመዋጋት ዳግመኛ እንውጣ ወይስ እንቅር? ብለው ጠየቁ። እግዚአብሔርም፦ነገ በእጃችሁ አሳልፌ እሰጣችኋለሁና ውጡ አለ።

ወደመጨረሻው የመፅሃፍ ቅዱስ ምዕራፎች ስንደርስ ደግሞ የምንረዳው ታቦቱ እልፍ እልፍ መናገሩንና ራእይም መታየቱ "ያልተለመደ" እንደነበር ነው። ይሁንና በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 3፣ ከ3-11 ስንመለከት፣ "ሳሙኤልም ታቦቱ ባለበት በእግዚአብሔር መቅደስ ተኝቶ ሳለ፥ እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራው። ሳሙኤልም ባርያህ ይሰማልና ተናገር አለ። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው 'እነሆ የሰማውን ሁሉ ሁለቱን ጆሮዎቹን ጭው የሚያደርግ አንድ ነገርን በእስራኤል አደርጋለሁ' አለ" ይላል።

በታቦቱ አማካይነት ትንቢታዊ መልዕክቶች የሚተላለፉት ግን በራእይና በድምፅ ብቻ አልነበረም። እልፍ እልፍ በጽሑፍ ይተላለፉ እንደነበር፥ እግዚአብሔር በሰሎሞን አማካይነት ወደፊት የሚሠራለት ቤተመቅደስ ምን መምሰል እንዳለበት በጽሑፍ ለዳዊት እንደተሰጠው በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ ይገኛል። ዜና መዋዕል ቀዳማዊ፣ ምዕ ራፍ 28፣ 19ን ይመልከቱ።

## የኃጢአት መብዛት፣ ወርቃማው ጥጃና ከሰማያት የወረዱ ደንጊያዎች

ምርምሬ እየቀጠለ በሄደ ቁጥር በዖልፍራም ጽሑፍ ውስጥ በተጠቀሰው ደንጊያ እና በታቦቱ መካከል ግንኙነት መኖሩ ግልጽ እየሆነልኝ መጣ። የዖልፍራም ጽሑፍ "የልብ ንጽሕና የሌለው ሰው ደንጊያውን መሸከም አይችልም፤ ማንሳትም አይሆንለትም" ይላል።

ይህ ጉዳይ ካንድ የአይሁዳውያን አፈታሪክ ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይችላል የሚል ግምት አሳደረብኝ። አፈታሪኩ እንደሚለው ሙሴ ከሲና ተራራ ላይ በእግዚአብሔር እጅ የተጻፉ ትዕዛዛት ያሉበትን የከበሩ ድንጋዮች ተቀብሉ በመውረድ ላይ ሳለ ከበታቹ የሰፈሩት የእስራኤል ልጆች ከወርቅ የተቀረጸ ጥጃ አሠርተው ሲያመልኩ ተመለከተ። ከዚያም፣

> ይህ ወደር የሌለው ኃጢአት ነበር። የያዘውንም ጽላት ዘወር ብሎ ሲመለከት፥ በጽላቱ ላይ የተጻፉት ትዕዛዛት በቅጽበት ሲጠፉ አየ። በዚያን ወቅትም የተሸከማቸውን ጽላቶች ከፍተኛ ክብደት ለመቋቋም አልቻለም። ከሰማይ የወረዱት እነዚህ ጽሑፎች ራሳቸውን ተሸክመው ነበርና ክብደታቸው ለሙሴ አልተሰማውም ነበር። ከጽሑፎቹ መጥፋት ጋር ሁሉ ነገር ተለወጠ።

በምሥጢራዊው የዖልፍራም ድርሰት ምዕራፍ 9 ላይ እንዲሁ ስለወርቃማው ጥጃ ተጽፏል።



በኔ እምነት የዚህ ፅሁፍ ጠቀሜታ የታቦቱን መገኛ ሰማየ ሰማያት ማድረጉ ላይ ነው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎች እንደሚናገሩት ከሆነ ይህ ድንጋይ ከሰማይ የወረደ የተወርዋሪ ኮከብ ስባሪ ነው። ከሰማይ የወረደ ድንጋይ ነው ብለው በእርግጠኝነት የሚያምኑት ሙሴና ሌዋውያን ብቻ ሳይሆኑ፥ ከእስራኤል ልጆች ውስጥ የቢም ነገዶች ጭምር ናቸው።

በዚህ ባለንበት ዘመንም የቀድሞው ባሕል መዝለቁን ማየት ይቻላል። ይኸውም፥ መካ መዲና ውስጥ ካአባ እጠገብ ለሚገኘው የተቀደሠ ጥቁር ድንጋይ የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚያደርጉት አክብሮት ይህን ያሳያል። ነቢዩ መሐመድ እንደሚሉት ይህ ድንጋይ ከሰማይ የወረደ ሲሆን፣ አዳም ከገነት ሲባረር ለኃጢአቱ ማስተሰረያ የተሰጠው ነበር። በኋላም መልአኩ ገብርኤል ለዕብራዊው ፓትርያርክ ለአብርሃም ሰጠው። በመጨረሻም ዛሬ የሙስሊሙ ዓለም ማዕከል ለመሆን በቅቷል። ወደመካ ለሐጂ የሚሄድ ምዕመን ሁሉም ይሳለመዋል።

የከርሰ ምድር አጥኚዎች ይህን ጥቁር ድንጋይ ከተወርዋሪ ኮከብ ስባሪ የተገኘ ነው ብለው በርግጠኛነት ይናገራሉ። በበረሃ ነዋሪ የነበሩት አረባውያን ነገዶች ተመሳሳይ ድንጋዮችን ይዘው ከቦታ ወደቦታ ይዘዋወሩ እንደነበርና እነዚህም ድንጋዮች የእስልምና ሃይማኖት ከመምጣቱ በፊት "ቤትይል" የሚል መጠሪያ ስም እንደነበራቸው ይታወቃል።

በተጨማሪ የተረዳሁት ነገር ቢኖር፥ በመካከለኛው ዘመን እነዚህ "ቤትይል" የሚባሉ ድንጋዮች በአውሮፓ ውስጥ "ላፒስ ቤቲሊስ" የሚል መጠሪያ የነበራቸውና ከሲም ነገድ ጋር የሚጠቀሱ ሆነው ባለ ወደበኋላ በሮማውያንና በግሪኮች እንደተቀደሱ ድንጋዮች ተቆጥረው ሰማያዊ ሕይወት ያላቸው እንደሆኑ በማመን ለተለያዩ ጥንቆላዎችና ለትንበያ ይጠቀሙባቸው ነበር።

ባለቅኔው ዖልፍራም በድርሰቱ ውስጥ የጠቀሰው ድንጋይ ከሰማይ የወረደ እንደነበርና "ፍሊጂታኒስ" ብሉ በፈጠረው ገጸ ባሕርይም ውስጥ ጽፎ የሚል ስያሜ ሰጥቶታል። ከጥቂት ገፆች በኋላም ለጽዋው እግራዊ "ላፕሲት ኤግዚሊስ" የሚል እንግዳ የሆነ ስያሜ ይሰጠዋል። ይህ ላቲን መሰል የተዳቀለ ሐረግ "ላፒስ ቤቲሊስ" የሚለውን ሐረግ ምስጢራዊና ስምለሽ አድርጐ ለማቅረብ የተሞከረ ያስመስለዋል።

## የጆሥጋና ጸሎት፣ መለኮታዊ ብርሃንና የምርጫ ኃያልነት

በዖልፍራም አገላለጽ ጽዋው ወደርሱ ለሚቀርቡ ንጹሕ ልብ ላላቸው ሰዎች ሁሉ የበረከትና የዘር ማግኛ ነው። ለዚህም በፓርዚቫል ምዕራፍ 5 የተገለጸው እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል።

ጽዋው ወዳለበት ቦታ ሁሉ እጁን የዘረጋ የበሰለና፣ ትኩስም
ቀዝቃዛ ምግብ እንዲሁም ተወዳጅ ማዕድ ተዘጋጅቶ ያገኛል...
ጽዋው የፍሬ በረከት፤ የጣፋጮች ሁሉ መገኛ ነውና፡፡

ይህ አገላለፅ የተከታዩ የአይሁዶች ጥንታዊ ፅሁፎች ገደል ማሚቶ ሊሆን እንደሚችል ገመትሁ፡፡

> ሰሎሞን ታቦቱን ወደመቅደሱ ባስገባበት ጊዜ በመቅደሱ
> ዙሪያ የነበሩት ወርቃማ ዛፎች ሁሉ በልምላሜ ተሞሉ፣
> እጅግም ብዙ ፍሬ ሰጡ፡፡ ይህም ለአገልጋዮቹ ካህናት
> ከፍተኛ ደስታና ጥቅም ሰጣቸው፡፡

በምርምሬ ወቅት በተጨማሪ፤ ይህ ጽዋ የተባለው ነገርና የቃል ኪዳን ታቦት፣ ልዩ የሆነና ምድራዊ ያልሆነ እንጸባራቂ ኃይል እንዳላቸው ተገንዝቤአለሁ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አባባል በንጉሥ ሰሎሞን ቤተመቅደስ እና የቃል ኪዳኑ ታቦት ከመሰወሩ በፊት ይቀመጥበት የነበረው ሥፍራ "ድቅድቅ ጨለማ" ውስጥ ነበር፡፡ ሆኖም የአይሁድ ህጎችና ልምዶች ላይ የተመሠረቱ የጥንታዊ ፅሁፎች ስብስብ የካህናቱ አለቃ ከቃል ኪዳኑ ታቦት በሚወጣው ልዩ ብርሃን በመመራት ነበር ወደ መቅደሱ ይገባና ይወጣ የነበረው፡፡ ታቦቱ ከጠፋ በኋላ ግን ሁኔታው ተለወጠ፡፡ ምክንያቱም የካህናቱ አለቃ "በጨለማ ውስጥ መደነባበር ነበረበት"፡፡

ስለሆነም ታቦቱ ለማያቋርጥ የብርሃን ምንጭ እንደነበርና ነፀብራቅም ይረጭ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስም ያረጋግጣል፡፡ ዎልፍራምም፣ ክሬቲየን ስለጽዋው ያቀረበውን ሃሳብ በመቀበል "ፀሐይ በወጣች ጊዜ የጨረቃና የከዋክብት ብርሃን እንደሚጠፋ ሁሉ የሻማዎቹ ብርሃንም እንዲሁ ተዋጠ" በማለት የታቦቱን ኃይል ገልጾታል፡፡

የክሬቲየንም ጽዋ በተመሳሳይ "ከንጹሕ ወርቅ" የተሠራ ሲሆን፣ ታቦቱም እንደዚሁ "በውስጥና በውጭ በንጹሕ ወርቅ የተለበጠ ነው፡፡" ይህም ብቻ ሳይሆን የጽላት መክደኛው ጭምር "ከንጹሕ ወርቅ የተሠራ" ነው፡፡ ሆኖም የብርሃናቸው ምንጭ ከተሠሩበት ወርቅ የመጣ ሳይሆን ለማያቋርጥና መለኮታዊ ከሆነ ኃይል የሚመነጭ ነው፡፡ የዚህ ብርሃናዊ ኃይል ምንጩ እግዚአብሔር በጣቶቹ አሥርቱ ትዕዛዛትን የጻፈበት የድንጋይ ጽላቶች ነበሩ፡፡ ሙሴ ጽላቱን ከእግዚአብሔር እጅ ከሲና ተራራ ላይ ተቀብሎ እንደተመለሰ የፊቱ ፀዳል እንዲያበራ ያደረገው የጽላቱ ኃይል ነበር፡፡

> ሙሴም ከተራራው በወረደ ጊዜ እግዚአብሔር ከርሱ ጋር
> ስለተነጋገረ የፊቱ ፀዳል እንዳንፀባረቀ አላወቀም ነበር፡፡
> አሮንና የእስራኤል ልጆች ሁሉ ሙሴን ባዩ ጊዜ እነሆ
> የፊቱ ፀዳል አንፀባረቀባቸው፡፡ ወደ እርሱም ይቀርቡ ዘንድ
> ፈሩ፡፡

ስለሆነም በዎልፍራም ፓርዚቫል ታሪክ ውስጥ ይህ ጽዋ የተባለውን ነገር በሕዝብ ሰልፍ መካከል ተሸከመች የተባለችው የሸዬዋ ሬፓንስ ፊት እጅግ ከፍተኛ ብርሃን በማመንጨቱ የተነሳ ሰዎች የፀሐይ ብርሃን የወጣ እንደመሰላቸው መተረኩን ሳስበው



ዎልፍራም ያለምክንያት እንዳልጻፈውና ከላይ ከተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ጋር በተገናኘ መልኩ እንደሆነም አሰብኩ፡፡

## በእምላክ የተመረጡ ሕዝቦች

የሸዬዋ ሬፓንስ ድንጋዩን መሸከም የተፈቀደላት "ልዕልት" ስትሆን፣ እርሷም "ፍፁም ንጽሕት ነበረች፡፡ ዋነኛ መለያዋም በታቦቱ በራሱ መመረጧ ነው፡፡ "ታቦቱ ለራሱ መጓጓዝ ሲል መረጣት" የሚለው ዎልፍራም፤ "በሸዬዋ ሬፓንስ ባይሆን ኖሮ ታቦቱ በማንም ሊወሰድ ባልፈቀደ" በማለትም ያብራራል፡፡ ዎልፍራም አፅንኦት ያደረገውም ማንም ሰው በኃይሉ ተመክቶ ይህንን ድንጋይ ሊሸከም እንደማይቻለውና፤ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው መሆን እንዳለበት ነው፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስም ታሪክ በዎልፍራም ፓርዚቫል ውስጥ ካለው ታሪክ ጋር ይዛመዳል፡፡ በኦሪት ዘትልቁ ምዕራፍ 10፤33 የተጻፈውን ስንመለከት የቃል ኪዳኑ ታቦት እስራኤላውያን የሚጓዙበትን መንገድም ሆነ የሚያርፉበትን ሰፈር ይመርጥላቸው ነበር፡፡

ታቦቱን ለመሸከም የተፈቀደላቸውም ለተለየው የክህነት አገልግሎት የተመረጡት ሌዋውያን ብቻ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡

> ዳዊትም የእግዚአብሔርን ታቦት ይሸከሙ ዘንድ ለዘላለሙም
> ያገለግሉት ዘንድ እግዚአብሔር ከመረጣቸው ከሌዋውያን
> በቀር ማንም የእግዚአብሔርን ታቦት ይሸከም ዘንድ
> አይገባውም አለ፡፡

በዎልፍራም ታሪክ ውስጥ ድንጋዩ በእንስታይ ጾታ የሚገለጽባቸውን ሁኔታዎች አይቻለሁ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህን ማግኘት ባልችልም በሰር ኢ.ኤ ዋሊስ በጅ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው ክብረ ነገሥት ታቦትን በእንስታይ ፆታ ይጠራል፡፡

> የቃልኪዳኑ ታቦት ወደ ከተማቸው፣ ወደሀገረ ኢትዮጵያ
> ስለመሄዱ እስመልክተህ የምትናገረው፣ እግዚአብሔር ፈቃዱ
> ከሆነና የእርሷም ፈቃድ ከሆነ፣ ማንም ሊከለክላት አይችልም፡፡
> ምክንያቱም በራሷ ፈቃድ ሄዳለች፤ እናም በራሷ ፈቃድ
> ትመለሳለች፤ እግዚአብሔር የሚፈቅድ ከሆነ፡፡

ሌላው የተገነዘብኩት ነገር የቃል ኪዳኑ ታቦት የተቀደሰና ክቡር ነገር መሆኑንና ይህንም ለማሳቀመጥ የሚቻለው በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ መሆኑን በመጥቀስ የሚያወሱ የተለያዩ ፅሁፎች መኖራቸውን ነው፡፡

> ታቦቱ በፈቃዱ ወደፈለገው ቦታ ይሄዳል፤ ሆኖም ግን
> ፈቃዱ ካልሆነ ደግሞ ከተቀመጠበት ቦታ ማንም
> አያንቀሳቅሰውም፡፡
> ያለእግዚአብሔር ፈቃድ ታቦቱ የትም ቦታ ሊቀመጥ
> አይችልም፡፡

ነገር ግን በልዑል እግዚአብሔር የተመረጡት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ናቸሁ፡፡ ምክንያቱም የቃል ኪዳኑ ታቦትና የእግዚአብሔር መኖሪያ ናቸውና፡፡



# ምዕራፍ አራት

## የምሥጢሩ ቁልፍ

በ1989 በልግና በጋ ወቅቶች በፓርዚቫል ላይ ያካሄድኩት ጥናት አንድ ሊሆን የሚችል ነገር ጫረብኝ- በልብወለድ መልክ የቀረበው ቅዱስ ጽዋ የቃል ኪዳኑ ታቦት ተምሳሌት ሆኖ የቀረበ ሊሆን መቻሉን፡፡ ይህም ሌላ መላምት ላይ እንድደርስ አደረገኝ፡፡ ይኸውም ከዎልፍራም በእግዜር የተመረጠ ገጸ ባህርይ በስተጀርባ አንድ የተደበቀ ግለሰብ ይኖር ይሆናል የሚል ነው፡፡ የዚህ ግለሰብ ማንነት መታወቅ ደግሞ የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚገኝበትን አድራሻ ሊጠቁም ይችላል፡፡ ባለቅኔው የግለሰቡ ማንነት እንዳይታወቅ በተራቀቁ አገላለጾች የደበቀው ይመስላል፡፡ ይህ ግለሰብ በኢትዮጵያ አፈ-ታሪክ መሠረት የቃልኪዳኑን ታቦት ወደ ኢትዮጵያ ያመጣው የንግስተ ሳባና የንጉስ ሰሎሞን ልጅ ቀዳማዊ ምኒልክ ሳይሆን አይቀርም ብዬ ጠረጠርኩ፡፡

ሁኔታው እንደጠረጠርኩት ከሆነ፣ ሌሎች ተጨማሪ ፍንጮች በፓርዚቫል ውስጥ ተደብቀው እንደሚገኙ አመንኩ፡፡ እነዚህም ድብቅ ፍንጮች፣ በመጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተበታትነውና ድብቅ በሆኑ አሳሳች ገለፃዎች ተሸፋፍነው ይሆናል፡፡ እነዚህ የተበታተኑ ፍንጮችን ማገጣጠም ከተቻለ ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት የበለጠ ሊያጠናክሩት ይችላሉ፡፡

## ጥቁሯ ንግስትና ነጬ ንጉስ

የመጀመሪያውን ፍንጭ ያገኘሁት በፓርዚቫል የመጀመሪያው ምዕራፍ አካባቢ ጥቋቁር ሰዎች ስለሚኖሩበት "ዛዛማንክ" ስለተባለችው ቦታ በሚገልፀው ሥፍራ ላይ ነው፡፡ ወደዚህች አገር "የእንጁው ጋህሙሬት" የተባለው አውሮፓዊ መስፍን በመጣ ጊዜም ቤላካኔ በተባለች ንግስት ፍቅር ይወድቃል፡፡ ቤላካኔ የተባለው ስም ድምፀት ማከዳ ከተባለው የንግስተ ሳባ ስም ጋር ተመሣሠለብኝ፡፡ በሌላ በኩል ሙስሊሞች ንግስተ ሳባን ቢልቂስ ብለው እንደሚጠሯት አውቃለሁ፡፡ ዎልፍራም የተለያዩ ቃላትን በማገጣጠም አዳዲስ ቃላትን መፍጠር ስለሚወድ ቢልቂስንና ማከዳን በማጣመር ቤላካኔ የሚለውን ቃል እንደፈጠረ ገመትኩ፡፡ ባለቅኔው "ጥቁሯ ንግሥት" በማለት ነው የሚገልፃት፡፡

በፓርዚቫል የመጀመሪያው ምዕራፍ አካባቢ የተዘረዘረውን የንጉሱንና የንግስቲቱን የፍቅር ሕይወት ስመረምር፣ በክብረ ነገስት ላይ ካ[illegible] [illegible]ንጉ፣ ሰሎሞንና ከንግስተ ሳባ የፍቅር ታሪክ ጋር ተመሣሠለብኝ፡፡ ካላንዳች ምክንያትም መስፍኑን ልክ እንደንጉሡ ሰሎሞን ነጭ፣ ንግስቲቷን ደግሞ እንደ ንግስት ማከዳ ጥቁር

እንዳላደረገ ገመትኩ። ይህ ጋህሙራት የተባለው መስፍን ቤላካኔ የተባለችውን ንግሥት አፍቅሮ ካገባት በኋላ የ12 ሳምንት እርጉዝ ስትሆን በድንገት ትቷት ወደ አገሩ ይመለሳል። ይህች ንግስት ለጋህሙራት ወንድ ልጅ ትወልድለታለች። ስሙንም ፌየርፊዝ ብላ ትሰይመዋለች። እርሱም ከጥቁርና ከነጭ የተወለደ ዲቃላ ስለነበር የከልስ መልክ ነበረው። ጋህሙራት ግን ወደአገሩ ተመልሶ ሄርዚሎይድ የተባለች ሴት ያገባል። ከዚህችም ሴት ፓርዚቫል የተባለ ወንድ ልጅ ይወልዳል። የፌየርፊዝን ወንድም ማለት ነው። ጋህሙራት በአንድ አገር ረግቶ የማይቀመጥ ጦረኛ ሰው ስለነበር የጓለኛዋን ሚስቱንም ትቶ ጀብድ ለመሥራት ወደ ሌሎች ቦታዎች በመጓዝ ካደረጋቸው ጦርነቶች ባንዱ መሞቱን ያወሳል።

በክብረ ነገሥትና በተመሳሳይ የኢትዮጵያ አፈታሪኮች ውስጥ ከጋህሙራት፣ ቤላካኔ፣ ፌየርፊዝ፣ ፓርዚቫል እና ሌሎችም ጋር በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን የሚመሳሰሉ ታሪኮች አሉ። እነዚህን ታሪኮች ዎልፍራም ጠመዝማዛ በሆነ መንገድና ድብቅ በሆነ አገላለፁ በዚህም አገላለፁ የተያያዙ የሚመስሉ ፍንጮችን አስቀምጧቸዋል። ከመረመርኳቸው ወደ ማስቀመጡ መሆኑ ስለገባኝ በጥንቃቄ በፓርዚቫል የመጀመሪያ ገጾች ኢትዮጵያ እንደሚያደርሱኝ ገመትኩ። አካባቢ የቤላካኔ ጥቁርነትና የጋህሙራት ንጣት በዝርዝር ተገልጿል። በክብረነገስት ውስጥም ስለፍቅረኞቹ የንጉስ ሰሎሞንና የንግስተ ሳባ የቆዳ ቀለም በሥፋት ተነግሯል፡ እንደ ጋህሙራት እና እንደ ቤላካኔ እነሱም አብረው ተኝተዋል። እንደኛቸውም አንዱን ጥሎ ሄዷል። ከሁለቱ በክብረነገስት ታሪክ ማክዳ ንጉስ ሰሎሞንን ጥላ ሄዳለች። ዎልፍራም የመረጠው የተገኘውም ቀዳማዊ ምኒልክ ክልስ ነው። የተገኘ የልብወለድ ገፀ ባሕርይ ስም ፌየርፊዝ ከፈረንሳይ ቃል ሲሆን፣ ቆዳው በነጭና በጥቁር የተዥጎረጎረ ልጅ እንደማለት ነው። በሌላ አማራጭ ደግሞ እውነተኛ ልጅ ወደሚለው ይወስዳል። በክብረነገሥትም በምዕራፍ 36 ላይ ምኒልክ ከንጉሥ ሰሎሞን ሲተዋወቅ፣ "ይህ ልጄ ነው" በማለት ሰሎሞን መናገሩ ሰፍሯል። በ1904 በፕሮፌሰር ኤኖ ሊትማን ወደ እንግሊዝኛ የተተረጐመ አንድ ጥናታዊ ጽሑፍም "ምኒልክም በቀጥታ ወደእርሱ በመሄድ እጁን ይ[illegible] ጨበጠው፣ ሰሎሞንም ይህን ጊዜ "አንተ እውነተኛው ልጄ ነህ አለ" ይላል።

## ጠመዝማዛ መንገድ

እነዚህን ዓይነት አጋጣሚዎች ዎልፍራም ፌየርፊዝንና ምኒልክን ለማገናኘት ይሞክራል የሚለውን ግምቴን አጠናከሩልኝ። ለምን ሁለቱን ሰዎች አገናኛቸው? ሄለን አዶልፍ እንዳሉት በክብረ ነገሥ[illegible] ታሪክ ላይ ተመስርቶ ሳይሆን የታቦቱ የመጨረሻ ማረፊያ በ[illegible] ኢትዮጵያ መሆኗን በማወቁ ነው። ይህንንም ሁኔታ በፓርዚቫል ታሪክ ውስጥ ደብቆታል። ፓርዚቫል ሥነጽሑፍን እንደ ምስጢ[illegible]



ቁልፍ በመጠቀም ጽዋውን ለታቦቱ ድብቅ መጠሪያ እንዲሆን አድርጎታል።

ዎልፍራም የተራቀቁ ማሳሳቻዎችን በመጠቀም የታወቀ ነው። በታሪኩ ውስጥ የተደበቁ ምስጢሮችን አንባብያን በቀላሉ እንዳይረዷቸው የተጠቀመባቸውን የማሳሳቻ ዘዴዎቹን ማየት የቻልኩ መሠለኝ። ቅዱሱን ጽዋ ለማግኘት የጣረው ፌየርፊዝ አይደለም ስለተባለም አልተረበሸኩም። ፀሐፊው ይህን ያደረገው ጉዳዩን ግልፅና አመላካች ላለማድረግ ፈልጎ ነው። ዎልፍራም በጽሑፉ ውስጥ ከአንዲት ጥቁር ንግሥት የተወለደን አረማዊ ዋነኛ ገጸ ባሕርይ ለማድረግ አልፈለገም። ይህን ቢያደርግም የመካከለኛው ዘመን ክርስቲያን አንባቢዎቹን ሊያስቀይም ይችላል።

በዚህም ምክንያት ይመስላል የጀርመኑ ባለቅኔ የጊዜውን አንባቢ ለማስደሰት ነጩን ፓርዚቫል ቅዱሱን ጽዋ እንዲያገኝ ያደረገው። ሆኖም በጥንቃቄ ጽሑፉን ላነበበው የታቦቱን ትክክለኛ አድራሻ የሚያመላክተው ፌየርፊዝ እውነተኛው ልጅ ነው።

መላምቴን ለማጠናከር የተሻለና ተጨባጭ ነገር ማግኘት እንዳለብኝ ተገነዘብኩ። የተለያዩ አጋጣሚዎች የቱንም ያህል አመላካች ቢሆኑም፣ የትም እንደማያደርሱኝ ገመትኩ። በዚህም መሠረት ፓርዚቫልን እንደገና በጥንቃቄ መመርመር ጀመርኩ።

በመጨረሻም የምፈልገውን ጉዳይ አገኘሁ። ቅዱሷን የጽዋውን ጠባቂ የሾዩዋን ሬፓንስ፣ ፌየርፊዝ አግብቷት እንደነበረ ከዚህ በፊት ማንበቤ ትዝ አለኝ። በድጋሚ ሳነብ ደግሞ አንድ ጠቃሚ ነገር አገኘሁ። ይኸውም ከሁለቱ የተወለደው ልጅ ፕሬስተር ጆን መባሉን።

አንድ ትልቅ ፍንጭ እንዳገኘሁ ገባኝ። ኢትዮጵያን የጎበኙ የመጀመሪያዎቹ አውሮፓውያን፣ የኢትዮጵያን ነገሥታት ፕሬስተር ጆን እያሉ እንደሚጠሯቸው አውቃለሁ። እነዚህ ነገሥታት የዘር ሐረጋቸውን የሚቆጥሩበት ከሰሎሞናዊው ሥርወ መንግስት ሐረጋች ንጉሥ ሰሎሞንና ንግሥተ ሳባ ልጅ ምኒልክ እንደሆነ አውቃለሁ። የሾዬው ሬፓንስ ለፌየርፊዝ፣ ጆን (ዮሐንስ) የተባለ ልጅ እንደወለደችለት ሳነብ የመደነቅ ስሜት ተፈጠረብኝ። ከዚያም በላይ "ፕሬስተር ጆን (ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ) ብለው ሰየሙት። ከዚያ በኋላ የመጡ ነገሥታትም ይህንኑ ስም እንደያዙ ቆዩ" ይላል።

ሆኖም በታሪኩ ውስጥ ድንጋይ የተባለው ጽዋ ያረፈበት ምድር የካህኑ ንጉስ ዮሐንስ አገር ለመሆኗ አንዳችም ፍንጭ አልተሰጠም። በዚህም የተነሣ የታሪኩን ጭብጥ ለማግኘት ያደረግኩት ጥረት ሁሉ መውጫ ወደሌለው ጉድጓድ ያደረሰኝ መሰለኝ።

የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ አንድ በዎልፍራም ዘመን አካባቢ በጀርመናዊ ደራሲ የተፃፈ፣ ካህኑ ዮሐንስ የድንጋዩ ጽዋ ጠባቂ መሆኑን የሚገልጽ ጽሑፍ አገኘሁ። የጽሑፉ ትረካ መመሳሰል በብዙ ምሁራን ዘንድ የዎልፍራም የራሱ ሥራ ነው እስከመባል አድርሶት ነበር። "ወጣቱ ቲቱሬል" (Der Jüngerer Titurel) የተባለውን

ጽሑፍ ያጠናቀረው አልብሬኽት ቮን ሻርፌንበርግ የተባለ ጀርመናዊ ሲሆን፣ ዘመኑ በ1270 እና 1275 (ከፓርዚቫሉ ደራሲ ዎልፍራም ሞት ሃምሳ ዓመታት በኋላ) ነው። ይህ ስብስብ ሥራ የተዘጋጀው ቀደም ሲል ይፋ ያልወጡ የዎልፍራም የተለያዩ ጽሑፎችን መሠረት በማድረግ መሆኑም ተጠቅሷል። በዘመኑ የአንድን ደራሲ ያላለቀ ሥራ ለፍጻሜ ማብቃት የተለመደ አሠራር ነበር። ስለዚህም ነው የዎልፍራም "ፓርዚቫል" የፈረንሳዩ ክሬቲዬን "ቅዱስ ጽዋ" ታሪክን በመቀጠል የጻፈው። በመጨረሻም ባለቅኔው አልብሬኽት የባለቅኔ ዎልፍራምን ሥራ በመጨረስ ነበር የተቀደሰው ድንጋይ የት እንደተቀመጠ የጻፈው።

ዎልፍራም የዚህ ምሥጢር ትርጉም ለመጪው ትውልድ የሚተላለፍበትን መንገድ አመቻችቶ አልፏል። ይህ እውነት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ለኔ ግን የምርምሬን አድማስ ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ ላይ እንዳሳርፍ ረድቶኛል። ዎልፍራም፥ ካህኑ ዮሐንስን ሲጠቅስ በአእምሮው ውስጥ ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ዮሐንስን አስቦ ይሆን? በመጀመሪያ ሲያጤኑት አይመስልም። ምክንያቱም ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ የተወለደው ሕንድ ውስጥ ነው። የካህኑ ንጉስ ዮሐንስ አባት ፌየርፌዝና የሸቤው ሬፓንስ ከሄዱበት ጉዞ የተመለሱት ወደ ሕንድ አገር ነበር። በፓርዚቫል ጽሑፍ ታሪኩን የበለጠ የተወሳሰበ ለማድረግ ሕንድ የተባለችው አገር "ትራይባሊቦት" የተባለ ስም እንደነበራትና የካህኑ ንጉስ ዮሐንስ አባት የትራይባሊቦት ንጉሥም ተብሎ ይታወቅ እንደነበር ተረዳሁ። በሌላ በኩል ፌየርፌዝ የንግሥት ቤላካኔ ልጅ በመሆኑ የዛዛማንክ ንጉስም ነበር። የነዚህ ሁሉ ስሞች ብዛት ዞሮ ዞሮ የአንድ አገር ስም ነው። ነገር ግን ይህች አገር ኢትዮጵያ ናትን? ምርምሬን መቀጠል ነበረብኝ። በተለይ የካህኑ ንጉስ ዮሐንስን (ፕሬስተር ጆን) ታሪካዊ የዘር ግንድ ማወቁ ችግሩን ለመፍታት ያግዘኝ እንደሆነ ለማወቅ ልጥር ወሰንሁ።

## እውነተኛ ንጉሥ

ፕሬስተር ጆን (ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ) የሚለው ስም ከ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ከቶ አይታወቅም። 12ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓ የመስቀል ጦረኞች (Crusaders) ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ለ80 ዓመታት በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው የቆዩበት ዘመን ነው። የታሪክ ሰዎች እንደሚስማሙበት ለመጀመሪያ ጊዜ ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ የሚለው ስም የተጠቀሰው በ1145 ሲሆን፣ ይህም በፉራንሲንገኑ አቡን ኦቶ ዜና መዋዕል ውስጥ ነው። በአቡኑ አባባል፥ ስለ ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ የሰሙት ከአንድ የሶሪያ የቤተክርስቲያን ሰው ነው። ካህኑ ንጉሳ ዮሐንስ የተባለው ሰው ንጉሥም ቄስም እንደሆነና "በምሥራቅ ዳርቻ" ብዙ ሠራዊት ያለው ንጉሥ እንደነበር ተወስቷል። ይህም ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ከሚመጡት ኃይሎች የሚከላከሉትን ወገኖች ለመርዳት ፍላጎት እንደነበረውም ሶርያዊው



ሰው ነግሮኛልም ይላል። በተጨማሪም ይኸው ንጉሥ በጣም የበለፀገ ነበር።

በመሆኑም በ1165 ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ ከተባለው ሰው ለተለያዩ የአውሮፓ ክርስቲያን ነገሥታት፥ በተለይም ለቁስጥንጥንያው ንጉሠ ነገሥት ማኑኤል እና ለሮማው ንጉሠ ነገሥት ፍሬድሪክ ተጻፈ የተባለ ደብዳቤ በሰፊው መሠራጨቱ ይታወቃል። ጽሑፉም ሊታመኑ በማይችሉ ሃይማኖታዊ ገለፃዎች የተሞላ ሲሆን፣ የካህኑ ንጉሥ ግዛት በአራት የተከፈለ መሆኑንና በሕንድ መጠሪያነት የሚታወቁ ሌሎች ግዛቶች መኖራቸውን ያትታል።

በ1177 ደግሞ የቬኒሱ ጳጳስ አሌክሳንደር 3ኛ ለዚሁ የሕንዶች ንጉሥ ለተባለው "በክርስቶስ ውድ ልጄ፣ ተወዳጁና የተከበረው ዮሐንስ" በማለት በ1165 ለተጻፈው ደብዳቤ መልስ መላካቸው ቢታወቅም ቀደም ሲል ከሌላ ምንጭ ስለፕሬስተር ጆን እንደሚያውቁ ገልፅ አድርገዋል።

በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፉት እነዚህ መረጃዎች የሚያመለክቱት ይህ ዮሐንስ የተባለው ካህንና ንጉሥ ከሕንድ ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። ሆኖም እነዚህ በመካከለኛው ዘመን የነበሩ ባለሥልጣናት ሕንድ የተባለውን ግዛት የት እንደሆነ በትክክል አያውቁም ነበር። ስለሕንድ ሲጠቀስ፣ አብዛኛዎቹ መረጃዎች የሚያመለክቱት ሥፍራ ግን የሕንድ ንዑስ ክፍለ አህጉርን ሳይሆን ምናልባትም አፍሪካ ውስጥ ወይም ሌላ ሥፍራ ይመስላል።

ምርምሬ እየገፋ በሄደ ቁጥር ይህ የተፈጠረው ስም እርግጠኛ ያለመሆኑ ችግር ምን እንደሆነ እየገባኝ መጣ። ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ የሚለው ስም ከመጠቀሱ ቢያንስ ካንድ ሺህ ዓመታት በፊት "ሕንድ" የተባለው ስም "ኢትዮጵያ" ከሚለው ጋር እየተምታታ ይቀርብ ነበር። ይህም ቨርጂል የግብፁ መነሻ ምንጭ ሕንድ ነው ካለበት ከአንደኛው ዓመተ ዓለም ጀምሮ ሲነገር የቆየ ሲሆን፣ ውዥንብሩም ማርኮ ፖሎ የሕንድ ውቅያኖስን የሚያዋስኑ አገሮችን ኢንዲዝ (Indies) እስካለበት ጊዜ ድረስ ዘልቋል። "ኢትዮጵያ" እና "ሕንድ" የሚሉት ሙሉ በሙሉ በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ሲውሉ ቆይተዋል።

የዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የባዛንታይኑ መንፈሳዊ ሰው ሩፊኒየስ ስለኢትዮጵያ ወደክርስትና ሃይማኖት መለወጥ አስመልክቶ ባጠናቀረው ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል። በ1983 ያጠናሁት የዚህ ፅሁፍ ዝርዝር እንደ አክሱም ያሉ የቦታ ስሞችን እና እንደፍሬምናጦስ፥ ንጉሥ ኢዛና የመሳሰሉት ታዋቂ ሰዎችን ያካተተ በመሆኑ ሩፊኒየስ ያለጥርጥር የሚናገሩት ኢትዮጵያ ስለተባለች አገር መሆኑ ግልፅ ነው። ሆኖም ፀሐፊው በመፅሐፉ ውስጥ "ሕንድ" ይላታል።

ይህ የሆነው አንድ የታሪክ ተመራማሪ እንዳስረዱት፣ "የቀድሞዎቹ መልክአ ምድር ጠበብት ኢትዮጵያን በስተምዕራብ የምትገኝ የታላቋ የሕንድ ንጉሠ ነገሥት ግዛት አድርገው ይቆጥሯት ስለነበር ነው።"

ይህ በመልክአምድር ጠበብት የተፈጸመው ስሕተት በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘሪ ን የተሠራጨው ግልጽ ያልሆነ ደብዳቤ ታክሎበት ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ እስያዊ፣ ብሎም ሕንዳዊ ንጉሥ ተደርጐ እንዲቆጠር አድርጓል፡፡

ይህ የተሳሳተ አተረጓጐም ለብዙ ጊዜ ስርጾ ቆይቷል፡፡ የካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ ምድር በትክክል በአፍሪቃ ቀንድ ውስጥ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ እንኳን በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ገደማ ለምሳሌ፡ ማርኮ ፖሎ "አቢሲኒያ (ኢትዮጵያ) ትልቅ ክፍለ ሀገር ስትሆን መካከለኛዋ ወይም ሁለተኛዋ ሕንድ ተብላ ትጠራለች፡፡ የዚህችም አገር ገዢ ክርስቲያን ነው" ብሏል፡፡ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የፍሎረንታይን ተጓዥ ሲሞን ሲጐሊ እንደተናገረው "ፕሬስቶ ጆቫኒ" (ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ) የሚኖረው በሕንድ ነው ይልና ይህች "ሕንድ"ም የግብጽ ሱልጣን ግዛት አጐራባች መሆኗን በመግለጽ ንጉሷም "የዓባይ ውሃ ባለቤት" እና ወደግብጽ የሚፈሰውንም ውኃ የሚቆጣጠር ነው ይላል፡፡ በ1520 በቀይ ባሕር ወደብ ምጽዋ በኩል ወደመሃል አገር በመጓዝ ኢትዮጵያን ለስድስት ዓመታት የጐበኘው ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ ሳይቀር ያለጥርጥር በአፍሪቃ ምድር መጓዙን ቢያውቅም፣ ከተለመደው የቃላት ውኽንብር ለመውጣት ባለመቻሉ የጽሑፉን ርእስ "እውነተኛ መረጃ ስለኢንዲዙ ፕሬስተር ጆን አገሮች" (Verdadera Informacam das terras do Preste Joam das Indias) ብሎታል፡፡

በዚህ በአልቫሬዝ በምሁራዊ መረጃ የተጠናከረ ጽሑፍ ውስጥ አልቫሬዝ የኢትዮጵያውን ንጉሥ "ካህኑ ንጉሥ" ወይም "ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" እያለ ይጠራዋል፡፡ በተጨማሪ ለማረጋገጥ የቻልኩት ቀደም ሲል በ1352 በእስያ ቆንስላ የነበረው የማሪኚዮሊው ጆቫኒ በዜና መዋዕሉ ውስጥ "ኢትዮጵያ ጥቁር ሰዎች ያሉባትና የካህኑ ንጉስ ዮሐንስ አገር ተብላ የምትጠራ ናት" ብሏል፡፡ በተመሳሳይ በ1328 ጆርዳኑስ "ካታላኒ" የተባለ ቄስ የኢትዮጵያን ንጉሥ ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ ብሎ ጠርቶታል፡፡ ከዚያም በ1459 ፍራ ማውሮ የተባለ ሰው ያዘጋጀው የዘመኑ የዓለም ካርታ ውስጥ አንድ የታወቀች ከተማ በአሁኑ የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ እንዳለች አመልክቶ "ዋነኛ የካህኑ ዮሐንስ መኖሪያ ናት" በማለት አስፍሯል፡፡

እነዚህ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ መረጃዎች ግራ አጋቡኝ፡፡ አንዴ ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ የነበረው ኢትዮጵያ ውስጥ ይመስላል፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖረ የ"ኢንዲዝ" ገዢ እንደነበር ይነገራል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ሕንድ ውስጥ ወይም ሩቅ ምስራቅ እንደነበር ይወሳል፡፡ ከዚህ ሁሉ ውዥንብር በስተጀርባ የዚህ ልብ ወለድ ታሪክ ምንጭ የሆነው እውነተኛው ካህን ንጉሥ ዮሐንስ የኢትዮጵያ ገዢ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም በመካከለኛው ዘመን በዓለም ውስጥ አውሮፓዊ ያልሆነ ብቸኛ ክርስቲያናዊ መንግሥት በመሆኑ ዎልፍራም የፌየርፊዝ እና የሾዬዋን የሬፓንስ ልጅ በካህኑ



ንጉሥ ዮሐንስ የምትገዛ ሕንድ ውስጥ በታሪኩ ያስገባው ከዚህ ብቸኛ ሞዴል በመነሳት ሊሆን ይችላል፡፡

በመጨረሻም የማያሻማ ትርጉም ለማግኘት ኢንሳይክሎፒድያ ብሪታኒካን ላይ የሚከተለውን አገኘሁ፡፡

> ምንም እንኳን "ካህን ዮሐንስ (ፕሬስተር ጆን) የሚለው ስያሜ ለተወሰኑ ጊዜያት በእስያ አፈታሪክ ተፅዕኖ ሥር የቆየ ቢሆንም፣ ከመጀመሪያው አንስቶ የአቢሲኒያ ንጉስ መጠሪያ እንደነበር አያጠራጥርም፡፡"
>
> ቀጥሎም እንዲህ ያብራራል፡፡
>
> ጳጳሱ እስክንድር 3ኛ በ1177 ከቬኒስ ደብዳቤ የጻፉለት ገዢ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ በትክክል ባይሰፍርም የተጻፈለትና የተላከለት ሰው የአቢሲኒያ ንጉሥ ነበር፡፡ የሊቀጳጳሱ ተላላኪ የነበረው ሐኪም ፊሊፕ በምሥራቅ ጉዞው ወቅት ያገኘው የተከበረውን የንጉሡ ነገሥቱን መንግሥት ተወካይ ነበር፡፡ በጊዜውም ይህ የመንግሥት ተወካይ ለጳጳሱ ተወካይ ያቀረበው ጥያቄ በኢየሩሳሌም ውስጥ የቤተመቅደስና የመሰዊያ ቦታ እንዲሰጠው ነበር፡፡ ከዚህም በላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም መቅደስና መንበር እንዳላትም እናውቃለን፡፡

ይህ መቅደስና መንበር ለኢትዮጵያ መንግሥት የተሰጠው በ1189 መሆኑንም ማረጋገጥ የቻልኩ ሲሆን፣ የተሰጣቸው ግን በቀረበው ጥያቄ መሠረት በጳጳሱ ሳይሆን በ1187 የአውሮፓውያኑን የመስቀል ጦረኞች ድል በማድረግ ኢየሩሳሌምን በቁጥጥሩ ሥር አድርጐ በነበረው በሙስሊሙ ጀነራል ሰላዲን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ጥያቄውን ቀጥታ ለሳላዲን በማቅረቡ ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ የተካሄዱት በፈረንሳይ የሻርትር ካቴድራል ሰሜናዊ መግቢያ ላይ ስለቅዱሱ ጽዋ እና ስለቃልኪዳኑ ታቦት፣ ንግሥተ ሳባንም በተመለከተ ቀራጮቹ ሐውልቶቹን ከመቅረፃቸው አስር ዓመታት ቀደም ብሉ ነበር፡፡

የፓርዚቫል ደራሲ ዎልፍራም ሥራዎቹን ከመጀመሩ አስር ዓመታት አስቀድሞ እነዚህ ሁኔታዎች መከናወናቸው ለኔ አጋጣሚ አልመሰለኝም፡፡ በተቃራኒው የሻርትር የቅርጻ ቅርጽ ሥራዎችም ሆኑ የዎልፍራም ግጥም በግልጽ የሚያሳዩት ነገር ቢኖር፣ ሁሉም ወሳንድ አቅጣጫ የሚያመለክት ካርታን መሥራታቸው ነበር፡፡ ካርታው ላይ ጠቋሚ ምልክት በግልጽ ባይኖርበትም፣ ንድፈ ሃሳቡ ትክክል ከሆነ የእውነተኛው የቃል ኪዳን ታቦት ማደሪያ ኢትዮጵያ መሆኗን ይጠቁማል፡፡

ሆኖም ተጨማሪ ጥያቄዎች መቀስቀሳቸው አልቀረም፡፡ እነሱም፤

- የቃልኪዳኑ ታቦት ኢትዮጵያ ውስጥ ስለመኖሩ የሚገልፅ መረጃ እንዴት በ12ኛው ክፍለዘመን መጨረሻ ለጀርመን ባለቅኔና ለፈረንሳይ የቤተክርስቲያን ሰዓሊዎች ሊደርስ ቻለ?

- የመጀመሪያው ባለቅኔና የኋለኞቹ ሰዓሊዎች በምን ተገናኙ? ግንኙነት ከሌላቸውስ ሁለቱም በሥነ ጥበብ ሥራቸው ውስጥ እንዴት ተመሳሳይ መልእክቶችን ደብቀው ተገኙ?
- ለምንስ የቃል ኪዳኑን ታቦት መቀመጫ ሥፍራ በቅኔና በተጠረቡ ሐውልቶች ታሪክ አማካኝነት ለመግለጽ ተፈለገ? ይህ የተደረገው ምስጢሩን ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ታስቦ ይሆናል የሚለው ድምዳሜ ላይ ከደረስኩኝ ቆይቻለሁ፡፡ ከሁሉ በላይ ግን በዎልፍራም ግጥም ውስጥ የተቀመጠውን የምሥጢር መልእክት ትርጉም መፍታት እጅግ አስቸጋሪ ነበር፡፡ እኔ ራሴ የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባፈራው የምርምር ድጋፍ በመታገዝና እክሱምን በማየት ለመፍታት የቻልኩት ይህን ያህል ብቻ ሲሆን፥ በ12ኛውና በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት እንዴት ሊፈቱት ይችላሉ? የሚችሉ ከሌሉ ደግሞ ምሥጢራዊ ግድረት ምንም ጥቅም ስለሌለው ሊፈቱት የሚችሉ ሰዎች መኖራቸውን ምክንያታዊ ሆኖ አገኘሁት፡፡

ይህን ተግባር ሊያከናውን የሚችል የአውሮፓዊ ቡድንም አገኘሁ፡፡ ቡድኑ ከአውሮፓ የመስቀል ጦረኞች አንዱ ሲሆን[1] አባላቱ በ12ኛው መቶ ክፍለዘመን በኢየሩሳሌም ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክሮ ይገኝ ነበር፡፡ በ1145 የካህኑ ንጉስ ዮሐንስ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢየሩሳሌም በተነዛበት ጊዜና በ1177 የኢትዮጵያው ንጉሥ መልእክተኞች በቅድስቲቱ ከተማ መቅደስና መንበር ለመጠየቅ በሄዱበት ወቅት የዚህ ምሥጢራዊ ቡድን አባላት እዛው ነበሩ፡፡ በመሆኑም በመስቀል ጦረኞቹ ቡድን አባላትና በኢትዮጵያው ንጉሥ መልእክተኞች መካከል ግንኙነት ተፈጥሮ ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህም በላይ ይህ ቡድን በከፍተኛ ደረጃ ምሥጢራዊ የነበረና በዓለም አቀፍ ግንኙነቶቹም ልዩ ልዩ ምሥጢራዊ ምልክቶችንና ጽሑፎችን ይጠቀም የነበረ ነው፡፡ በተጨማሪም ቡድኑ በሻርትር ካቴድራል እንደታየው የጐቲክ አርኪቴክቸርን በማውጣትና በአውሮፓ ውስጥ በማስፋፋት የተሰማራ ነበር፡፡ ዎልፍራምም ብዙ ጊዜ በስም ይጠቅሳቸው የነበሩ ናቸው፡፡ በሻርትር ካቴድራል ሰሜናዊ መግቢያ ላይ ባለው በመልከ ጼዴቅ ሐውልት ግራ እጅ ሥርም የዚሁ ቡድን ስም መፃፉን ተመልክቼያለሁ፡፡ (በነገራችን ላይ በድፍን የመካከለኛው ምዕተ ዓመት ተሠርቶ የተገኘው ብቸኛ የመልከ ጼዴቅ ሐውልት ይህ ብቻ ነው፡፡)

የዚህ ኃያልና በሌሎች ሰዎች ላይ ተጽዕኖ በማሣደሩና በአያሌው በተጓዥነቱ የሚታወቅ ቡድን ስም ማን ይሆን?

ሙሉ ስሙ "የክርስቶስና የሰሎሞን ቤተመቅደስ ወታደሮች" ነው፡፡ በመሠረቱ ይህ ቡድን ሃይማኖታዊ ሥርዓትን የሚከተል የተዋጊ መነኮሳት ኃይል ሲሆን፥ በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሠራዊቱን ጽህፈት ቤት ኢየሩሳሌም ውስጥ በሚገኘው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በነበረበት ቦታ ላይ አድርጎ ነበር፡፡ ከዚሁ ቦታ ነው የቃል ኪዳኑ ታቦትም በዘመነ አሪት የተሰወረው፡፡



# ምዕራፍ አምስት

## ነጭ ነፍጠኞችና ጨለማው አህጉር

የሥነፅሁፍ ተመራማሪዋ ሄለን አዳምስ ሜሪ ፍላንጋ እንደምትለው (የኦክስፎርድ ቋንቋን ሊቅ የካርል ፍንግ ባለቤት) እንደምትለው[1] ቅዱሱ ጽዋ በአሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ እንደ አንድ የሥነጽሑፍ ዘርፍ ድንገት ብቅ ያለበት ሁኔታ በመስኩ የተሰማሩ ጠቢባንን ሳያስደንቅ አልቀረም፡፡ ሄለ ፍንግ የቅዱስ ጽዋውን አፈ ታሪክ በተመለከተ ባደረገችው ጥልቅ ጥናት ከዚህ ክስተት ጀርባ አንድ ታላቅ ቁምነገር ያለ መሆኑን ገምታለች፡፡ በተጨማሪም ሄለ ፍንግ "ኮንት ዱ ግራል" እና "ፓርዚቫል" የተባሉት ሁለት የሥነጽሑፍ ዘርፎች መውጣት "የከርሰ ምድር ውሃ" እንደመጥለፍ ይቆጠራል ብላለች፡፡ ይህ "የከርሰ ምድር ውሃ" ምንድነው?

እንደሚመስለኝ መልሱን የቅዱስ ጽዋው ሥነፅሁፍ መሠራጨት የጀመረበትን ዘመን ታሪክ በማጤን ማግኘት ይቻላል፡፡ ይህ ዘመን የአውሮፓ የመስቀል ጦረኞች ከአረቦችና ከአይሁዳዊ ባሕል ጋር በመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙበት[1] ኢየሩሳሌምም በክርስቲያን ሠራዊት እጅ ለ88 ዓመታት የቆየችበት ወቅት (ከ1099 ጀምሮ በሙስሊሙ ጄኔራል ሰላዲን እስከተያዘችበት እስከ 1187 ድረስ) ነበር፡፡ ባለቅኔው ክሬቲዬን ስለጽዋው ታሪክ የጻፈው ከተማዪቷ በተያዘች በ83ኛው ዓመቷ በ1182 ነበር፡፡ ዎልፍራም ደግሞ ስለፓርዚቫል መጻፍ የጀመረው ኢየሩሳሌም ከተያዘች ከጥቂት ዓመታት በኋላ ነው፡፡

ስለሆነም እነዚህ ሥራዎች ሊወጡ የቻሉት ባንድ ድርጊት ላይ በመመሥረት ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ፡፡ ምክንያቱም የመስቀል ጦረኞች ኢየሩሳሌምን በተቆጣጠሩበት ወቅት በአውሮፓ ዘማች ክርስቲያን ሠራዊት እጅ ብዙ መረጃ ሊገባ እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም፡፡ ምናልባትም ዎልፍራም ይህንን አስመልክቶ በፓርዚቫል ውስጥ የጠቀሰው ጉዳይ ይኖራል በሚል እምነት ጽሑፉን በጥንቃቄ መመርመር ጀመርኩኝ፡፡ በመጨረሻም ዎልፍራም ከአንድ ማንነቱ ከማይታወቅ "ኪዮት" ከተባለ ሰው መረጃዎችን ማግኘቱን እንደገለጸ አነበብኩ፡፡ ጉዳዩን ሲገልጸውም እንዲህ ብሏል፡፡

> ከተጠመቀ ክርስቲያን ካልሆነ በቀር ይህ ታሪክ ከቶውኑም ባልታወቀም ነበር፡፡ የማንም ያላመነ ሰው ሥነ ጽሑፍ ስለ ጽዋው ባሕርይ እንደዚሁም ስላዘለው ምሥጢር ሊገልጽልን ባልቻለም ነበር፡፡

በፓርዚቫል ጽሑፍ ውስጥ ስለቅዱሱ ጽዋ ላይ ላዩን ከሚታየው ውጪ ሌላ ተጨማሪ መረጃ ሊኖር እንደሚችልም ጠቁሟል፡፡ ይህ "ተጨማሪ መረጃ" ቃል ኪዳኑ ታቦት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም ክቡር ዕቃ በጽሑፉ ውስጥ በልቦለድነት ቀርቧል፡፡ በጽሑፉ ውስጥ ስለ "ኪዮት የሠፈሩትን መረጃዎች በማጠናበት ጊዜ ይህ ምስጢራዊ ሰው የቃል ኪዳኑ ታቦት ኢትዮጵያ ውስጥ ተደብቆ እንደሚገኝ የነገረው

ሰው ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ፡፡ በጽሑፉ አንድ ቦታ ላይ "ክዮት እውነተኛውን ታሪክ የነገረን" የሚል አገላለጽ ሠፍሯል፡፡ ይህ ግለሰብ በርግጥም ትልቅ ሰው ነበር፡፡ ዳሩ ግን ማንነቱን እንዴት ማወቅ ይቻላል?

ይህ ምሥጢራዊ ሰው በፓርዚቫል ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተጠቅሷል፡፡ ጽሑፉን በጥንቃቄ ስመረምር "ክዮት" የተባለው ሰው "ጌታ" ተብሎ ይነገርለት የነበረና እሱን የፈታበትም ቋንቋ ፈረንሳይኛ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ በዚህ ብዙ መግፋት ባለመቻሌ ስለዘመኑ ቋንቋ የሚያውቁ የታወቁ ምሁራንን ርዳታ በመጠየቅ የክዮትን ማንነት ለማወቅ ባደረግኩት ሙከራ፣ ሰውየው በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ የፈረንሳይ ባለቅኔ ሲሆን[፤] ስሙም የፕሮቫንሱ ጉዮት መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ወደኢየሩሳሌም ቅድስት ከተማ ተጉዞ እንደነበርና በሮማው ንጉሥ ፍሬድሪክ ባርባሮሳ ቤተመንግስት ለጥቂት ጊዜ ይሠራ እንደነበርም ለማወቅ ቻልኩ፡፡

የመጨረሻው ነጥብ ዕይታዬን ሳበው፡፡ ምክንያቱም ፍሬድሪክ እንደ ዎልፍራም በትውልዱ ጀርመናዊ ሲሆን፣ በ1152 ንጉሠ ነገሥት ሆኖ ከመመረጡ በፊት የስዋቢያ መስፍን ነበር፡፡ በተጨማሪ ይህ ፍሬድሪክ የተባለ ንጉስ ከብዙ ነገሥታት መካከል በስም ተጠቅሶ "ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ ደብዳቤ" በ1165 የተላከለት ነው፡፡

ምርምሬን በመቀጠል አንድ እጅግ ጠቀሜታ ያለው ፍንጭ አገኘሁ፡፡ ጉዮት/ክዮት የተባለው ሰው የሰሎሞንን መቅደስ ይጠብቁ ከነበሩት ነፍጠኞች ጋር የጠበቀ ቁርኝት እንደነበረው ኤማ ዩንግ በጥናቷ ላይ አስፍራለች፡፡የቃልኪዳኑ ታቦት ደግሞ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከሰሎሞን ቤተመቅደስ እንደተሰወረ አውቃለሁ፡፡ በፓርዚቫል ውስጥ ዎልፍራም የቅዱሱን ጽዋ ጠባቂዎች የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች ብሏቸዋል፡፡ ማረጋገጥ የፈለግኩት ግን በዎልፍራም ሥነ ጽሑፍ የተጠቀሱት ቴምፕላሮች (የሰሎሞን ቤተመቅደስ ጠባቂዎች) በዚያን ወቅት ከተመሠረተው የመስቀል ጦረኞች ሠራዊት ጋር አንድ መሆን አለመሆናቸውን ነበር፡፡

የሻርትርን ካቴድራል በጎበኘሁበት ወቅት ከገዛሁቸው የጉብኝዎች መጽሐፍ አንዱ ላይ ዎልፍራም የቤተመቅደስ ጠባቂ እንደነበር የሚነገር መሆኑንና ለዚህ አባባል ግን ምንም ማስረጃ እንደሌለ ያወሳል፡፡ የጀርመኑ ባለቅኔ ፓርዚቫልን በሚጽፍበት ወቅት ቅድስቲቱን ምድር ጎብኝቶ እንደነበር በርካታ የተከበሩ ምሁራን መናገራቸውን ተገነዘብሁ፡፡

## ቁፋሮ ተካሂዶ ይሆን?

ኤማ ዩንግ በጥናቷ ውስጥ ቴምፕላሮቹ በዎልፍራም ጊዜ "የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ጠባቂ ሠራዊት ተደርገው ይቆጠሩ ነበር" በማለት ያሰፈረችው ጽሑፍ ለጉዳዩ ይበልጥ ትኩረት እንድሰጥ አደረገኝ፡፡ ምርምሬን በቀጥልም "የኢየሱስ ክርስቶስና የሰሎሞን ቤተመቅደስ



ጠባቂ ሠራዊት (ዘብ)" የሚለውን ሕጋዊ ስያሜ ያገኙት የኢየሩሳሌም ማዕከልና የሰሎሞን ቤተመቅደስ ተሠርቶበት ከነበረው ሞሪያሕ ተራራ ጋር በተያያዘ መሆኑን ደረስኩበት፡፡ ይህ በባቢሎናውያን ወራሪዎች በ587 ቅድመ ልደተክርስቶስ የፈራረሰው ቤተ መቅደስ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደተመለከተው ለቃል ኪዳኑ ታቦት ማኖሪያ ይሆን ዘንድ የተሠራ ነበር፡፡

ቴምፕላሮች ራሳቸውን ከሰሎሞን ቤተመቅደስ ጋር በማዛመዳቸው በተዘዋዋሪ ራሳቸውን ከታቦቱ ጋር እያዛመዱ መሆኑ ተሠማኝ፡፡ እንደገባኝ ይህ ቡድን የተመሠረተው ኢየሩሳሌም በአውሮፓውያን የመስቀል ወታደሮች ከተያዘች ከሃያ ዓመታት በኋላ (በ1119) በመጡ ዘጠኝ ፈረንሳውያን ነበር፡፡ የ12ኛው ክፍለዘመን የታሪክ ምሁርና የቲር ሊቀጳጳስ ዊልያም እንደጻፉት ከነዚህ ዘጠኝ ፈረንሳውያን መካከል "ከፍተኛ ክብርና ተደማጭነት የነበራቸው የፓየንሱ ሁዩ እና የሲይንት ኦመር ጉድፍሬይ ናቸው፡፡

ሁኔታውን ይበልጥ ሳጤነው ትኩረት የሚስብ ነገር ገጠመኝ፡፡ የቡድኑ የበላይ ተቆጣጣሪ የነበሩት የፓየንሱ ሁዩ የተወለዱት በሻምፔኝ ግዛት ከምትገኘው ትሮይስ ከተማ 12 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው ፓየንስ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ዘጠኙም መሥራቾች የዚሁ ግዛት ተወላጆች ናቸው፡፡

ከዚህ ጋር የሚያያዙ አያሌ ሌሎች አጋጣሚዎችም ነበሩ፡፡ እነሱም፣

1. ሻርትር ከታላቁ ካቴድራሏ ጋር በ12ኛውና በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሻምፔኝ ገዥዎች አስተዳደር ሥር ነበረች፡፡
2. ከዘጠኙ ነፍጠኞች መካከል የሞንትባርዱ አንድሬ የተባለው የክሌርቮክሱ ቅዱስ በርናርድ አጐት ሲሆን[፤] እርሱም የሻምፔኝ ተወላጅ ነበር፡፡ ይህ ከፍተኛ ተደማጭነት የነበረው የቤተክርስቲያን አገልጋይም በጐቲክ ሥነ ሕንፃና ቅዱስ ጽዋው ላይ ልዩ ትኩትን የሚያሳይ ሰው ነበር፡፡
3. የትሮይስ ከተማ ለፓየንሱ ሁዩ የትውልድ ቦታ ቅርብ ብቻ ሳትሆን ስለቅዱስ ጽዋው ታሪክ የጻፈው የባለቅኔው ፈረንሳዊ ክሬቲዬን መኖሪያ ነበረች፡፡
4. የፓየንሱ ሁዩም የሻምፔኙ ገዢ ለነበረውና በኋላም በ1125 ቴምፕላሮችን የተቀላቀለው ሰው የአጐት ልጅ ነበር፡፡
5. የትሮይሱ ክሬቲዬን በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ታዋቂ በሆነበት ዘመንም የሻምፔኙ ገዢ የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ያደርግለት ነበር፡፡

እነዚህን የተያያዙ አጋጣሚዎች ካየሁ በኋላ የቴምፕላሮችን የቀድሞ ታሪክ ማጥናት ጀመርኩ፡፡

በርካታ እንግዳ ነገሮችም አጋጠሙኝ፡፡ ከሁሉ የሚገርመው ዘጠኙ የጥበቃው ቡድን መስራቾች በ1119 በኢየሩሳሌም ንጉሥ ቦልድዊን አንደኛ የተደረገላቸው አቀባበል ነበር፡፡ ኢየሩሳሌም እንደደረሱ፣ ዘጠኙ ሰዎች ንጉሡ በቤተመንግሥትነት ይጠቀምበት የነበረውን

የቀድሞውን አል-አቅሳ መስጊድ በመቅደሱ [illegible] እንዲሰጣ ቸው ጠየቁ። ንጉሡም ባስገራሚ መልኩ የሰሎሞን ትራታ የቤተመን ግሥቱን አብዛኛን ክፍልና "የድንጋዩ ጉልላት" አጠገብ ያለውን ተጨማሪ ሕንፃ እንዲጠቀሙበት ፈቀደላቸው። ታላቁ "የድንጋይ ጉልላት" የሰሎሞን ቤተመቅደስ የነበረበት ቦታ ነው።

ከዚህ በኋላ ቴምፕላሮቹ "በኢየሩሳሌም፣ በጠረፉ መካከል ያለውን መንገድ ከዘራፊዎች ለመጠበቅ" በሚል ሽፋን በዚህ ሥፍራ ቢቀመጡም፤ ኢየሩሳሌም በቆዩባቸው ዘጠኝ ዓመታት አንድም ጊዜ ይህንን ተልዕኮ እንዳልፈጸሙ ታውቋል። በተጻራሪው ያደረጉት ነገር ቢኖር የሰፈሩበትን ቦታ ከሕዝብ ዕይታ በመከለል ማንም ወደቦታው እንዳይገባ በማድረግ ቁፋሮ ማካሄድ ነበር።

ይህ ሥፍራ የተቀደሰ የእስልምና ቦታ ተብሎ ከሚታወቁት መካከል ሦስተኛና አራተኛ ደረጃ የያዙትን የድንጋዩን ጉልላትና የአል-አቅሳ መስጊድ ስለያዘ በመናኛ አርኪዮሎጂስቶች በዚህ አካባቢ ቁፋሮ እንዲያካሂዱ ፈቃድ አይፈቀድም ነበር። ሆኖም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከተራራው በስተደቡብ በኩል የእስራኤላውያን ቁፋሮ ቡድን ወደሰሎሞን ቤተመቅደስ የሚያመራ ዋሻ አግኝቷል። ቁፋሮውም በጥበቃው ቡድን መካሄዱን አረጋግጧል። እስራኤላውያን ተመራማሪዎች የዘገቡት የሚከተለውን ነው

> ይህ ዋሻ ወደ 30 ሜትር ያክል ወደ ውስጥ የሚዘልቅ ሲሆን፣ የዋሻው መጨረሻም በድንጋይና በፍርስራሽ እስከ ክምር ተዘግቷል። ሆኖም ይህ ሥፍራ በአሁኑ ወቅት በሙስሊሞች ቁጥጥር ሥር በመሆኑና ለመቆፈርም በመጀመሪያ ፈቃድ ማግኘት ስለሚያስፈልግ ፎቶግራፍ አንስተንና ቦታውን ለክተን ሥራችንን አቆምን።

ስለቴምፕላሮቹ ዋሻ የታወቀው ወይም ማለት የሚቻለው ይህን ያህል ብቻ ነው። አርኪዮሎጂስቶቹ ከቆሙበት በልቆ መሄዱን ብቻ ነው ማረጋገጥ የቻሉት። ዋሻው [illegible] ወደ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ወ[illegible] ቦታዎች [illegible] እንደሚችልና ቀጥታ በድንጋዩ ጉልላት ሥር አልፎም ከአል-አቅሳ መስጊድ ወደ ሰሜን መቶ ሜትር ርቀት ተጉዞ [illegible]።

የአል-አቅሳ መስጊድ በቀድሞው የሰሎሞን ቤተ መቅደስ መሠረት ላይ የተሠራ ሲሆን፣ በውስጡም ሰሎሞን ታቦቱን ያስቀመጠበት የመሠረት ድንጋይ፣ አይሁዶች "ሼቲያህ" የሚሉት ይገኛል። በ587 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን በያዙበት ወቅት ሕዝቡን ማርከው ሲወስዱ ታቦቱ ግን መወሰዱን የሚያመለክት አንዳችም ማስረጃ አልተገኘም።

በመሆኑም ከተማዋ በባቢሎናውያን እጅ በመውደቋ ጥቂት ቀደም ብለው አይሁዶች ታቦቱን ለማዳን [illegible] ቤቱ ውስጥ ከሚገኘው ድብቅ ዋሻ ውስጥ ከሸሸጉት [illegible] የሚል አፈታሪክ ተስፋፋ። ይህም በተለያዩ የአይሁድ [illegible] ጽሑፎችና አፈታሪክ ተጽፏል። [illegible] በኢየሩሳሌም

በስፋት ይነገር የነበረ "አፈታሪክ" በወቅቱ ተወዳጅ በነበረው የባሩክ ራዕይ በተለያዩ መልኩች ተገልፆ ስለነበር ዝርዝሩ ነፍጠኞቹ ጆሮ በቀላሉ ሊደርስ እንደሚችል ታወቀኝ። ከሁሉም በላይ በጥቂት ምርምር ዘጠኙ ቴምፕላሮች በ1119 ኢየሩሳሌም ከመሄዳቸው በፊት ሊሰሙት እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ቻልሁ።

የዚህ ቡድን መሥራች የነበረው የፓየንሱ ሁዩ ቀደም ሲል በ1104 ከሻምፔኝ ገዢ ጋር ወደ ቅድስቲቱ ምድር ተጉዞ ነበር። ከዚያም ሁለቱ ሰዎች ወደፈረንሳይ ተመልሰው እስከ 1113 አብረው ቆዩ። ከሦስት ዓመታት በኋላ ግን ሁዩ ብቻውን ወደኢየሩሳሌም ተመልሶ በድጋሚ ወዳገሩ በመሄድ ከስምንቱ ሰዎች ጋር ወደኢየሩሳሌም በ1119 ተጓዙ።

እንግዲህ ሁዩና የሻምፔኙ ገዢ በ1104 ባደረጉት ጉዞ ወቅት በተራራው መቅደስ ውስጥ ታቦቱ ተደብቆ መቀመጡን ሰምተው ይሆናል። ከዚህም በመነሳት ይመስለኛል ቴምፕላሮቹ ዕቅድ በማውጣት በቆራጥነት ይህን ቅርስ ለመፈለግ የተዘጋጁት።

ዘመኑ ሃይማኖታዊ ቅርሶችን ማደን የተጧጧፈበት ነበር። የቃል ኪዳን ታቦቱን ማግኘት የመሰለ ታላቅና እጅግ ውድ፣ ክቡርና የተቀደሰ ተልዕኮ ደግሞ ስለሌለ ለዚሁ ዓላማ ተሰለፉ። ይህ ታቦት በእጃቸው ቢገባ የሚያገኙትን ክብርና ኃይል አበክረው ያውቁ ስለነበር ቢያገኙት ኖሮ ያለጥርጥር ወደ አገራቸው በወሰዱት ነበር። በጥናትና ምርምር ባይደገፍም አንድ ነገር ማግኘታቸውን የሚገልጽ ወሬ ግን በእጅጉ ተናፍሷል። ሰባት ዓመታት መቅደሱ ተራራ ላይ ባካሄዱት ቁፋሮ በርካታ ጥንታዊና ምሥጢራዊ ጽሑፎችን፣ በተለይ ፀአይሁዳ ውያንና ጥንታዊ ግኝቶች ላይ የተፃፉ መረጃዎችን (ምናልባትም እስከ ሙሴ ዘመን የሚዘልቁ) ማግኘታቸው ጥርጥር እንደሌለውና፣ ይህንም በነሱው በተመሠረተው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ውስጥ ለነበሩት የምሥጢራዊው ቡድን አባላት በቃል መተላለፉ ተጠቅሶ ተጽፏል። ይህ አባባል በሰፊው ቢናፈስም፣ እኔ ግን በቂ ማስረጃ ላገኝለት አልቻልኩም።

ከዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ በስተጀርባው ግን ተጨባጭ መረጃን ባላገኝም እንኳን ዘጠኙን ቴምፕላሮች ወደኢየሩሳሌም የላኳቸው የክሌርቮክሱ ቅዱስ በርናርድ መሆናቸውን ተገንዝቤያለሁ። እኚህ ሰው በ1112 የተመሠረተውን ማሕበረ መነኩሳት ከተደባለቁ በኋላ፣ በ1115 የገዳሙ አበምኔት ሆኑ። ከዚያም በ1119 በፈረንሳይ ከፍተኛ የሃይማኖት መሪነትን ቦታ ተቆናጠጡ፤ይህም ዘመን ቴምፕላሮች ወደ ኢየሩሳሌም የደረሱበት ወቅት ነበር። በመሆኑም በተልዕኳቸው ውስጥ የእሳቸው ምንም ዓይነት ሚና አልነበረውም ማለቱ ብልህነት እንዳልሆነ ተገነዘብሁ። ይህም ጥርጣሬዬ ጠረኞቹ በመጀመሪያዎቹ ሰባት ዓመት ያከናወኑትን ተግባር ስመረምር ተጠናከረ።

በ1126 የፓየንሱ ሁዩ የቅዱስ በርናርድ አጎት ከሆነው ከሞንትባርዱ አንድሬይ ጋር ድንገት ኢየሩሳሌምን ለቀው በ1127 ፈረንሳይ ገቡ። በጥር፣ 1128 ደግሞ በቴምፕላሮች ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ግምት በሚሰጠው አንድ ክንውን ተሳተፉ። በትሮይስ ከተማ የተካሄደው የዚህ ሲኖዶስ ዓላማም፡ ለቴምፕላሮቹ የቤተክርስ ቲያኒቱን ይፋዊ ድጋፍ ለማስገኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነበር።

ከዚህ ስብሰባ ጋር የተያያዙ ሦስት ጉዳዮች በተለይ ትኩረቱን ሳቡት። የመጀመሪያው የሲኖዶሱ ስብሰባ የተካሄደው የቅዱስ ጽዋውን ታሪክ ወደበኋላው ባመነጨው የፈረንሳዩ ገጣሚ መኖሪያ ከተማ ውስጥ መሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ስብሰባው በፀሐፊው በቅዱስ በርናርድ መመራቱ ነው። ሦስተኛው፣ በስብሰባው ወቅት ቴምፕላሮች በራሱ የሚተዳደሩበት ሕጋዊ የመተዳደሪያ ደንብ በቅዱስ በርናርድ መዘጋጀቱ ነበር።

እንደምገምተው ቴምፕላሮቹ በኢየሩሳሌሙ የሰባት ዓመታት ቆይታቸው ወቅት ባደረጉት ቁፋሮ ጠቃሚ የሆነ ቅርስ ምናልባት ሊያገኙ ቢችሉም፣ በ1126 አካባቢ ግን ይፈልጉት የነበረውን የቃል ኪዳኑን ታቦት እንደማያገኙት ተረድተዋል። ይህም ሁኔታ መጻኢ ተስፋቸውን እንዲመረምሩና ወደፊት ባሉበት የመቀጠል ወይም የመበትን ምርጫ የተደቀነባቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ አደረጋቸው። የዚህ ሲኖዶስ መካሄድና በውሳኔውም ለቴምፕላሮች እንዲሰጥ የተወሰነው ሁለንተናዊ ድጋፍ ለሕልውናቸው መረጋገጥና ለሌሎች ሥራዎችም መቀጠል ታላቅ ተስፋ ሆነ። ከዚህም የተነሳ አዳዲስ ምልምሎች ከመላ ፈረንሳይና የአውሮፓ አገሮች ወደቡድኑ መጉረፍ ጀመሩ። እጅግ በርካታ ገንዘብና መሬት እንዲሁም ሌሎች ዕ ርዳታዎችም ጉ ል ። የተወሳሰቡ የዓለም አቀፍ የባንክ ሥርዓቶችን ሳይቀርም ዘረ ፡ ታዲያ ይህ ሁሉ ከፍተኛ ድጋፍ ለቴምፕላሮቹ በቅዱስ በርናርድ ከሁል ሲሰጣቸው በምላሹ ምን ሰጥተው ይሆን?

የ1130ዎቹን ዓመታት ላስታወሳቸው በአውሮፓ ውስጥ በድንገት ታይቶ የማይታወቅ የሕንፃ ንድፍ (ጎቲክ) ሥራ እየተስፋፋ የነበረ ሲሆን፣ የዚህ ሥራ ዋነኛ ደጋፊም ቅዱስ በርናርድ ነበሩ። እንደተገለጸው ቴምፕላሮቹ በኢየሩሳሌም በቆዩባቸው ሰባት ዓመታት ውስጥ ባካሄዱት ቁፋሮ ከመቅደሱ ተራራ የጥንታዊ ዕውቀትን ምንጭ ማግኘታቸው ቀደም ሲል በስፋት ተናፍሷል። ለተደረገላቸው ውለታ ምላሽ ይሆን ዘንድ ይህን ምስጢር የሲኖዶሱ ፀሐፊ ለነበሩት ለቅዱስ በርናርድ ሰጥተው ይሆን? በርግጥ ነፍጠኞቹ የቃል ኪዳኑን ታቦት ከሰሎሞን ማግኘት አልቻሉም። ነገር ግን በቁፋሯቸው ወቅት ከሰሎሞን ጊዜ ጋር የተያያዙ ጥንታዊ የብራና ጽሑፎችን፣ የሒሳብ ቀመሮችን፣ ካርታዎችን፣ የግንባታ ምስጢሮችን አግኝተው ቢሆንስ? የሒሳብ መመሪያዎች። ግንቦቹ በተለይም ፒራሚድንና ጥንታዊ ግንቢዎች የተጠቀሙባቸውን የግንባታ ጂኦሜትሪ አካተው እንደሆንስ? ቴምፕላሮች ቅዱስ በርናርድ ላደረጉላቸው ውለታ እነዚህን ምስጢሮች አካፍለዋቸው ይሆን?

እነዚህ ግምቶች መሰረተ ቢስ አልነበሩም። እውነቱ በተቃራኒው ቴምፕላሮች ታላቅ የስነህንፃ አዋቂዎች መሆናቸው ነው። በ1139 የቅዱስ በርናርድ ከፍተኛ ድጋፍ የነበራቸው ጳጳስ ዳግማዊ ኢኖሰንት ለቴምፕላሮቹ የራሳቸውን ቤተክርስቲያን እንዲያንፁ የሚያስችላቸውን ልዩ መብት ሰጥተዋቸዋል። ቴምፕላሮቹም ዕድሉን ሙሉ በሙሉ ተጠቅመውበታል። ውብ የሆኑ የአምልኮ ሥፍራዎችን በየቦታው ገንብተዋል። ነፍጠኞቹ ፈፅሞ የማይበገሩ ወታደራዊ ህንፃዎችንና ግምቦችንም በመሥራት የታወቁ ነበሩ። ከነዚህም ታዋቂው ምሽግ አትሊት (ሻቶ ፒሌሪን ወይም የፒልግሪም ግምብ) የሚባለው ሲሆን፣ የተገነባውም በ1218 በ14ኛው የቴምፕላሮቹ ርዕስ አለቃ በሻርትሩ ዊልያም ነበር። ይህም ስም ከታላቁ ጐቲክ ካቴድራል ጋር የተቆራኘ ነው።

ቴምፕላሮቹ የግንባታ ሥራዎችን በአውሮፓ ብቻ ሳይሆን ጠቅላይ ዕሀፈት ቤታቸው በነበረበት በኢየሩሳሌምም በስፋት አካሂደዋል። ተመሳሳይ ግንባታ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ አካባቢ ባሉት ቦታዎች ይካሄድ እንደነበር እንደ በ1174 ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ተጉዞ የነበረ ቴዎዲሪሽ የተባለ የጀርመን መነኩሴ ዘግቧል። ይህንም በ1187 ኢየሩሳሌም በሙስሊሙ ጀኔራል ሳላዲን እስከተያዘ ድረስ ገፍተውበታል።

ቴምፕላሮቹ ታቦቱን ለማግኘት ያደረጉት ጥረት ባይሳካላቸውም፣ በተቻላቸው ግን የት ሊገኝ እንደሚችል በሐውልትም ሆነ በሥነ ጽሑፍ ገልጸዋል። ይህ የእነርሱ "ካርታ" ያመለከተውም ወደ ኢትዮጵያ ነበር።

ለዚህም መልስ ለማግኘት ቁልፏ ኢየሩሳሌም ስለሆነች የትኩረት አቅጣጫዬን ወደዚያ አደረግሁ። ምክንያቱም አንድ ኢትዮጵያዊ ልዑል በ1185 ወደአገሩ እስከተመለሰ ድረስ በስደት በኢየሩሳሌም ይኖር ነበርና። የዎልፍራም፣ የፓርዚቫልን የድርሰት ሥራና የሰሜናዊ ሻርትር ካቴድራል ታዛ ላይ የተጀመረውም የቅርጽ ሥራ ከዚሁ ሁኔታ ፀመነሣት አስር ዓመታት ቆየት ብሎ ነበር የተሠራው።

## ኢትዮጵያዊ ልዑል በኢየሩሳሌም

ኢትዮጵያዊው ንጉስ ላሊበላ አብዛኛውን የወጣትነት ዕድሜውን ያሳለፈው ኢየሩሳሌም ውስጥ ነበር። በ1165 አንድ ደብዳቤ በካህኑ ንጉስ ዮሐንስ ስም ወደአውሮፓ መላኩንና በ1177 ጳጳሱ እስክንድር ሣልሳዊ ለዚሁ ደብዳቤ ምላሽ መስጠታቸው ይታወቃል። እንደ ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ አባባል በዚያን ዘመን በኢየሩሳሌም ከተማ በቀራንዮ ቤተመቅደስ ማሠሪያ ቦታ ይሰጠኝ ብሎ ሊጠይቅ የሚችል

የሌላ ሳይሆን የኢትዮጵያ ንጉሥ ብቻ ነው፡፡ በ1177 ይግም ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረው ንጉስ ሐርቤ ነበር፡፡ ጳጳስ እስክንድር ግን መልስ የሠጡት ለሐርቤይ ሳይሆን ለላሊበላ እንደነበር በአደረግኩት ጥናት ለማወቅ ችያለሁ፡፡

ንጉስ ሐርቤይም ሆነ ንጉስ ላሊበላ ከቀዳማዊ ምኒልክ ከሚጀምረው ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግስት የተገኙ አይደሉም፡፡ ሁለቱም ከዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ሲሆኑ፣ ከ1030 እስከ 1270 ሥርወ መንግሥቱ ወደሰሎሞን ዘር እስኪተመለሰበት ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያን ገዝተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስለዛጉዌ ሥርወ መንግስት ያለው መረጃ በጣም ጥቂት ነው፡፡ ሆኖም ስሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት በ980 ገደማ ዮዲት (ጉዲት) በምትባል የአይሁድ እምነት ተከታይ ሴት መገልበጡን አረጋግጫለሁ፡፡ የአይሁድ እምነት ተከታይ የነበረችው የጉዲት ዓላማ የክርስትናን እምነት ማጥፋት ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ ዮዲት አክሱምን ደምስሳ ንጉሱንም ገደለች፡፡ ሌሎች ሁለት ልዑላንም ሲገደሉ፣ አንዱ ግን አምልጦ ሸዋ ገባ፡፡ እዚያም ወልዶ ከብዶ እንደነገሩ ንግሥናውን ለማቆየት ችሏል፡፡

ዮዲት ቀጥተኛ ወራሽ ይኑራት አይኑራት በትክክል ማወቅ ባይቻልም፣ እርሷ ከሞተች ሃምሳ ዓመታት በኋላ የሰሜን ኢትዮጵያ አብዛኛው ክፍል የአገው ተወላጅ በሆኑ የዛጉዌ ነገሥታት ይገዛ እንደነበረ የታሪክ ምሁራን ይስማማሉ፡፡

ይህ ሥርወ መንግሥት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት እንደዮዲት አይሁዳዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በርግጠኝነት መናገር ባይቻልም ንጉሥ ላሊበላ ከመወለዱ በፊት የዛጉዌ ሥርወ መንግስት የክርስትናን እምነት ተቀብሏል፡፡

የንጉሥ ሐርቤ የአንድ ወገን ወንድም የሆነው ላሊበላ ወደፊት ታላቅ ሰው እንደሚሆን እናቱ ያወቀችው ሕፃኑ አልጋው ላይ ተጋድሞ ሳለ በንብ ሠራዊት ተከቦ ባየች ጊዜ ነበር፡፡እንስሳት ወደፊት ስለሚመጡ ታላላቅ ሰዎች ያውቃሉ የሚባለውን የቆየ እምነት የምታውቀው እናቱ፥ "ይህንን የንብ ክበባ ባየች ጊዜ በመንፈስ ተቃኝታ፥ ላሊበላ በማለት በታላቅ ድምፅ ጮኸች"የሚል አፈታሪክም አለ፡፡ላሊበላ ማለት "ንቦች ኃይልህንና ሥልጣንህን አወቁ" እንደማለት ነው፡፡

ንጉስ ሐርቤም ትንቢቱን ሲሰማ፣ ዘውዱን እንዳይቀማ በመፍራት ላሊበላን በሕጻንነቱ ለማስገደል ጥረት አደረገ፡፡ የመጀመሪያ ሙከራው ባይሳካም፣ የተለያዩ የግድያ ሙከራዎች ለብዙ ዓመታት ቀጠሉ፡፡ በመጨረሻም ላሊበላ መርዝ እንዲጠጣ ተደርጎ ራሱን ሳተ፡፡ በአፈታሪኩ መሠረት ላሊበላ ለሦስት ቀናት ራሱን ስቶ ቆይቷል፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር የላሊበላ ነፍስ ወደመጀመሪያው፣ ሁለተኛውና ሰባተኛው ሰማያት በመላእክት የተወሰደችውና በእግዚአብሔር ፊት የቆመችው፡፡ ልዑል እግዚአብሔር፥ ላሊበላን ለሕይወቱ ከቶ እንዳይፈራና ለንግሥና የታቀባ መሆኑን ነግሮታል፡፡ ወደፊትም በርካታ ተግባራትን እንደሚያከናውን ተገልጾለታል፡፡ ይኸውም ከእንቅልፉ



እንደነቃ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሰደድና እዚያም ከአደጋ ተጠብቆ ቆይቶ ጊዜው ሲደርስ ንጉሥ ሆኖ ወደ ትውልድ አገሩ ሮሃ እንደሚመለስ ተነግሮታል፡፡ ከዚህ በፊት ታይተው የማይታወቁ አብያ ተክርስቲያናትንም ይገነባል፡፡ የግንባታውንም ጥበብ በተመለከተ ከእግዚአብሔር ዝርዝር መመሪያ ተቀብሏል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ አፈታሪክና ታሪክ በማስረጃ በተደገፈ ሁኔታ መጣጣማቸውን የታሪክ መዛግብት ያረጋግጣሉ፡፡ በርግጥም ላሊበላ ለረጅም ጊዜ በስደት ኢየሩሳሌም ቆይቷል፡፡ ላሊበላ የተሰደደው በ1160 ገደማ ሲሆን፣ በዚያን ጊዜም ዕድሜው ወደሃያ ዓመት ይጠጋ ነበር፡፡ በ1185 ላሊበላ ወደአገሩ ኢትዮጵያ ተመልሶ ንጉሥ ሐርቤን ከሥልጣን በማስወገድ በትረ መንግሥቱን ጨበጠ፡፡

ዜና መዋዕሉቹ እንደሚናገሩት ከዚህ ዘመን ጀምሮ እስከ 1211 ድረስ ሲነግስ፣ መዲናውንም የተወለደባትን የሮሐን ከተማ አደረገ፡፡ በኋላም የሮሐ ከተማ ለንጉሱ ክብር ሲባል ስሟ ተቀይሮ ላሊበላ ተባለች፡፡

ላሊበላም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመፈፀም የውቅር አብያ ተክርስቲያናቱን ግንባታ በመጀመር እጹብ ድንቅ የሆኑ ከአንድ ወጥ አለቶች ተጠርበው የወጡ አሥራ አንድ አብያተክርቲያናትን አሳነጿል፡፡

ላሊበላ ያሳነጻቸው አብያተክርስቲያናት ገጽታዎች ከቅድስቲቱ ምድር በስደት ቆይታው ይዟቸው የተመለሰ ይመስላሉ፡፡ ለምሳሌ፥ ከተማውን አቋርጦ የሚያልፈውን ወንዝ "ዮርዳኖስ" ብሉ ሰይሞታል፡፡ ከአሥራ አንዱ አብያተክርስቲያናት ውስጥ ቤተ ጉልጉታ የቱባለውና በተለየ መልኩ የታነፀው በኢየሩሳሌም ያለውን የቀራንዮ መካነ መቃብር እንዲወክል ተደርጐ ነው የተቀረጸው፡፡ በአጠገቡ ያለው ደብረዘይት የተባለ ቋራራም የተሰየመው ክርስቶስ በመጨረሻው ሰዓት በአይሁድ ጭፍሮች በተያዘበት ቦታ ስም ነው፡፡

ላሊበላ የራሱን መዲና "አዲሲቱ ኢየሩሳሌም" ለማድረግ ከመጣሩ በተጨማሪ በዘመነ መንግሥቱ ከኢየሩሳሌም ጋር የነበረው ግንኙነት አድጓል፡፡ በርግጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምራ ለሃይማኖታዊ ተልዕኮ ቀሳውስትን ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ትልክ ነበር፡፡ ከታሪኩ እንደምናስታውሰው ንጉሥ ሐርቤ፣ ለጳጳስ እስክንድር ሳልሳዊ በ1165 በጻፈው ደብዳቤ በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ የቤተመቅደስ ማሠሪያ ቦታ መጠየቁ ይህንኑ ግንኙነት ለማጠናከር ቢሆንም፣ በ1177 ከጳጳሱ ለሐርቤ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ አልነበረም፡፡ ከአሥር ዓመታት በኋላ ግን ሁለት ዐበይት ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ የመጀመሪያው በ1185 የላሊበላ መንገሥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በ1187 የሙስሊሙ ጀኔራል ሳላዲን ኢየሩሳሌምን በመያዝ ተዋጊ የመስቀል ጦረኞቹን ማባረርና የኢትዮጵያም ማህበረሰብ ከሌሎች የምሥራቅ ክርስቲያኖች ጋር ወደ ቆጵሮስ ደሴት እንዲሰደድ መገደዱ ነበር፡፡

የንጉሡ ዜና መዋዕል እንደሚያሳየው በዚህ ሁኔታ በእጅጉ የተረበሸው ንጉሥ ላሊበላ በ1189 መልዕክተኞቹን ወደኢየሩሳሌም በመላክ ሳላዲንን ለማግባባት ባደረገው ሙከራ ኢትዮጵያውያን እንዲመለሱ ከመፈቀዱም በላይ የተሰጣቸው ቦታ ከበፊቱ እጅግ ክቡር የሆነና በክርስቶስ መካነ መቃብርና የተሰቀለበት ቦታ ቀራንዮ አካባቢ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ ቦታ አሁን የኢትዮጵያውያን አይደለም፡፡ ከኢትዮጵያ ኢየሩሳሌም፣ ሔመጓለም የሚሄዱ ምዕመናን ጸሎታቸውን ለማድረስ የሚችሉት በቆረቆሩት ገዳም ውስጥ ባለች አነስተኛ ቤተክርሳቲያን ውስጥ ሲሆን፣ አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያውያን ሁለት ሌሎች ገዳማት በኢየሩሳሌም ውስጥ እንዳላቸው፣ እንዲሁም በአርጌዋ ከተማ ውስጥ ከቀራንዮ ቤተክርስቲያን አጠገብ የጳጳሳትና የምዕመናን ማረፊያ በእጃቸው እንዳለ ይታወቃል፡፡

በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ፖሊሲ እንዲሁም ከሥነሕንፃ ግንባታና ከደረሰበት መንፈሳዊ እድገት አንፃር ሲገመገም፣ የላሊበላ ዘመነ መንግስት የዛጉዌ ሥርወ መንግስት ቁንጮ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ከላሊበላ ሞት በኋላ ግን ውድቀት ተከተለ፡፡ በ1270 የላሊበላ የልጅ ልጅ ነአኩቶ ለአብ ሥልጣኑን የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ወራሽ ለሆነው ለይኩኖ አምላክ አስረከበ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በ1974ቱ አብዮት ከሥልጣን እስከተወገዱበት ጊዜ ድረስ ከአንድ ንጉሥ በስተቀር ሁሉም የዘር ግንዳቸውን ከሰሎሞናዊ ሥርወ መንግስት ጋር ሲያያይዙ ቆይተዋል፡፡

## የድርጊቶች መገጣጠም

የላሊበላን አንፀባራቂ ዘመነ መንግስት ከገመገምኩ በኋላ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ቀደም ሲል ከተዋልኳቸው ክንዋኔዎች፣ ማለትም ከመስቀል ጦርነቶች፣ ከቴምፕላሮችና ከአሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድርጊቶች ጋር መቀራኘቱ ነበር፡፡

- በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ (ወይም በ1099፣ የ11ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ) ኢየሩሳሌም በመስቀል ጦረኞች ተያዘች፡፡
- በ1119 የቴምፕላር መሥራቾች የሆኑ ዘጠኙ የፈረንሳይ መኳንንት ወደ ኢየሩሳሌም በመግባት ጸኖናው የሰሎሞን ቤተመቅደስ ግቢ ጠቅላይ ሠፈራቸውን መሠረቱ፣
- በ1128 የክሌየርቮክሱ ቅዱስ በርናርድ በትሮይስ በተካሄደው ሲኖዶስ ላይ ለቴምፕላሮች ሙሉ ዕውቅናን ሰጡ፡፡
- በታሪክ የመጀመሪያው የሆነው የጕቲክ ሥነሕንፃ አሠራር በሻርትር ካቴድራል ሥራ፣ በተለይም የሰሜናዊው ክፍል ሕንፃ ግንባታ በ1134 ተጀመረ፤



- በ1145 "ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" የሚለው ስም ለመጀመሪያ ጊዜ በአውሮፓ ተሰማ፣
- በ1160 ላሊበላ ወንድሙን በመፍራት የፖለቲካ ስደተኛ በመሆን ኢየሩሳሌም ገባ፡፡
- በ1165 "ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" የሠራዊቱን ብዛትና ኃያልነት እንዲሁም የሀብቱን ክምችት በመግለጽ ለአውሮፓ ነገሥታት ደብዳቤ አሰራጨ፡፡
- በ1177 ጳጳስ እስክንድር ሣልሳዊ "በካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" ተጻፈ ለተባለው ደብዳቤ መልስ ሲጽፉ እንደገለጹት፣ "የካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" መልዕክተኞች በኢየሩሳሌም ጉብኝታቸው ወቅት ፊሊፕ ከተባለ ከርሳቸው ሐኪምና መልዕክተኛ ጋር መገናኘታቸውንና ለእርሱም በኢየሩሳሌም ውስጥ የመቅደስ ማሠሪያ ቦታ ይሰጣቸው ዘንድ ደብዳቤ እንዲያደርስላቸው መጠየቃቸውን በመጥቀስ የተጻፈ ነበር፡፡ "ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" የተባለው ሰው ሊሆን የሚችለው የላሊበላ ወንድም የሆነው ሐርቤ ሲሆን፣ እርሱም በ1177 የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበር፡፡
- በ1185 ልዑል ላሊበላ ከኢየሩሳሌም ወደኢትዮጵያ በመመለስ ሐርቤን ከዙፋኑ አስወግዶ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ ወዲያውኑ ዕጹብ ድንቅ የሆኑትን የአብያተ ክርስቲያናት ሥራ በሮሐ ከተማ ጀመረ፡፡ የሮሐ ከተማ ስምም ለክብሩ ሲባል ተለውጦ "ላሊበላ" ተባለ፣
- በ1187 ኢየሩሳሌም በሱልጣን ሳላዲን በሚመራው የሙስሊም ኃይሎች ሥር እንደወደቀችና የመስቀል ጦረኞቹም ተባረው ሲወጡ፣ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት ከቅድስቲቱ ከተማ ተሰደው በቆጵሮስ ደሴት ውስጥ ጊዜያዊ ጥገኝነት አገኙ፡፡ ከኢየሩሳሌም ውድቀት በኋላ ከቴምፕላሮቹ መካከል ጥቂቶቹ ወደዚህች ደሴት በመሸሸና መሬት በመግዛት ጠቅላይ ሠፈራቸውን ለተወሰነ ጊዜ በዚያው አድርገዋል፡፡
- በ1189 ንጉሥ ላሊበላ ወደኢየሩሳሌም መልዕክተኞችን በመላክ ሱልጣን ሳላዲንን በማግባባት ኢትዮጵያውያን ወደዚህች ከተማ እንዲመለሱ ለማድረግ ከመቻሉም በላይ ከዚያ በፊት አግኝተውት የማያውቁትን ልዩ እንክብካቤና ጠቀሜታ ከሙስሊሙ ሱልጣን እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ (ሐርቤ በ1177 ጳጳሱን ጠይቆ ማግኘት ያልቻለውን አገኘ ማለት ነው፡፡)
- በ1195 እና በ1200 መካከል ዎልፍራም "ፓርዚቫልን" መድረስ ጀመረ፡፡ ይህም ሥራ ከፈረንሳዩ ባለቅኔ የትሮይሱ ክሬቲን የቀጠለ ሲሆን "ጽዋ" የተባለውንም "ድንጋይ" በማለት በርካታ ነጥቦችን ከኢትዮጵያ ታሪክ ያካተተበትና በተለይ "የካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" እና የቴምፕላሮችን ስም የጠቀሰበት ወቅት ነበር፡፡

ዎልፍራም ድርሰቱን በጀመረበት ጊዜ ነበር በሻርትር ካቴድራል የሰሜናዊው መግቢያ በር ግንባታ የተጀመረው፡፡ ይህም ማለት ኢትዮጵያዊቷ ንግሥተ ሳባ፣የመልከ ጼዴቅ ጽዋ እና የቃል ኪዳኑ ታቦት ሐውልቶች የተቀረጹበት ወቅት ነበር፡፡

የጉቲከ ሥነሕንፃ፣ ቅዱስ ጽዋው፣ ቴምፕላሮችና አውሮፓዊ ያልሆነ ኃያል ክርስቲያን ንጉሥ ("ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ") የ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውጤቶች ነበሩ፡፡ "ፓርዚቫል" ከመጻፉና የሻርትር ካቴድራል ሰሜናዊ መግቢያ ከመገንባቱ ጥቂት ቀደም ብሎ የወደፊቱ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ንጉሥ ላሊበላ ከ25 ዓመታት ስደት በኋላ በትረ ሥልጣኑን ለመጨበጥ ወደአገሩ የተመለሰው በዚሁ በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነበር፡፡

ከዚህ ሁሉ የተገነዘብኩት እነዚህ እጅግ የተወሳሰቡ፣ ነገር ግን በአንድ የጋራ ነጥብ ላይ የተዛመዱ ነገሮች ሆነ፣ ተብሎ እንዳይታወቅ መደረጉን ነው፡፡ ቴምፕላሮች የቃል ኪዳኑን ታቦት ለማግኘት መጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ትኩረት ማድረጋቸው ከተረጋገጠ፣ ከዚህ በፊት ያገኘኋቸውን የተያያዙ ድርጊቶች ውጤትና ምክንያት ምስጢር ለማወቅ ያስችል ይሆናል፡፡

ለጊዜውም ቢሆን ግን የተረዳሁት ኢየሩሳሌምን በተመለከተ የሚቻለኝን ያህል መጓዜን ሲሆን፣ ያልተፈታው እንቆቅልሽ በኢትዮጵያ በኩል ያለው ነበር፡፡ ቴምፕላሮቹ የቃል ኪዳኑን ታቦት ፍለጋ ወደኢትዮጵያ ሄደው ነበር? ሄደውስ ከነበረ ይህንኑ በተመለከተ ዎልፍራም በሥነ ጽሑፉ ውስጥ ያስፈረው ሚስጥር ይኖር ይሆን?

## "ከሃዲዎቹ ቴምፕላሮች . . ."

ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ በ1165 ለክርስቲያን ነገሥታት ጻፈ የተባለውን ወደእንግሊዝኛ የተተረጐመ ደብዳቤ ካገኘሁ በኋላ አንድ ርምጃ ወደፊት ለመራመድ ቻልኩ፡፡ ምሁራን ይህ ደብዳቤ ከካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ የተላከ ለመሆኑ ይጠራጠራሉ፡፡ የተጻፈበት ቀን ትክክለኛ ቢሆንም በዚያን ጊዜ ካህኑ ንጉስ ዮሐንስ የሚል ማዕረግ ካለው ንጉስ ሊጻፍ ስለማይችል የተጭበረበረ ሰነድ ነው ይላሉ፡፡

የደብዳቤው ፀሐፊ ስለአገሩ ሲገልፅ በርካታ ሊታመኑ የማይችሉ ነገሮችን አስፍሯል፡፡ ደብዳቤውን ካነበብኩ በኋላ ነበር ምሁራኑ ለምን ከዚህ ድምዳሜ ላይ ሊደርሱ እንደቻሉ የገባኝ፡፡ ፀሐፊው በደብዳቤው ላይ በጉችን የሚያካክሉ ጉንቸሎችንና በሬዎችን ከመሬት ወደ ሰማይ ማንሳት የሚችሉ አሞሮች በአገሩ እንዳሉ ገልጿል፡፡ እንዲሁም ከፊታቸው አንድ አይን ከኋላቸው ደግሞ ሦስት አይኖችና ቀንድ ያላቸው ሰዎች መኖራቸውንም አስፍሯል፡፡ በተጨማሪም የፈረስ ኮቴ ያላቸው ሰዎች፣ ከወገብ በላይ ሰው ሁነው ከወገብ በታች የፈረስ ቅርጽ ያላቸው ፍጡራን፣ ወጣት የሚያደርግ የምንጭ ውሃ፣ ማንኛውንም ውዳቂ ነገር ጎደ ዕንቁ የሚለውጥ የአሸዋ ባሕር፣ የሕይወት ዛፍ፣ ባለሰባት ራስ



ደራጎን ወዘተ በግዛቱ ውስጥ እንደሚገኙ በዝርዝር አስፍሯል፡፡ ይህ ሁሉ የተነገረለት አገር ግን የት እንደሚገኝ በደብዳቤው ውስጥ አልተጠቀሰም፡፡ ሆኖም ስለኢንዲዝ ግዛቶች በመጠኑም ቢሆን ተጠቅሷል፡፡ በዚያን ጊዜ ደግሞ አውሮፓውያን ኢንዲዝን ለኢትዮጵያ መጠሪያነት ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ምናባዊ ፍጡራን በተጨማሪ የሰውን ዓለም ፍጡራንም ተገልፀዋል፡፡ ለምሳሌም ያህል ዝሆኖችና ግመሎች፣ አንበሳን ሊገድሉ የሚችሉ ባለአንድ ቀንድ አውራሪስን የሚመስሉ እውሬዎችና ሌሎችም ተጠቅሰዋል፡፡ ይህን ሁሉ ሳነብ ደብዳቤው የተጭበረበረ ሰነድ ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ፡፡ ፀሐፊው ስለኢትዮጵያ የሚናገር ስለመሆኑ በአገሪቱ ስለሚገኙ ዝሆኖች፣ ግመሎች፣ አንበሶችና አውራሪሶች መጥቀሱ ሌላው ማስረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ ጥርጣሬዬን የበለጠ ያጠናከረልኝ ደግሞ ስለመቄዶንያው ትልቁ እስክንድር መጠቀሱ ነው፡፡ ትልቁ እስክንድር ከ"ጉግ ማንጉግ" ተዛምዶ ነው የቀረበው፡፡ በዚህ ላይ እንዳተኩር ያደረገኝ ደግሞ ትልቁ እስክንድር "ልፋፈ ጽድቅ" በተሰኘው የጥንት ኢትዮጵያ ሃይማኖት ጽሑፍ ውስጥ በተመሳሳይ አገላለጽ መስፈሩ ነው፡፡ ይህ ጽሑፍ ከአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት በፊት ከኢትዮጵያ ውጪ የሚታወቅ አይደለም፡፡

ሌላው ትኩረቴን የሳበው ጉዳይ "ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" በደብዳቤው ውስጥ በክርስቲያን ግዛቱ ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው አይሁዶች እንደሚኖሩና መጠነኛ የሆነ የራስ ገዝ አስተዳደር እንዳላቸው፣ በየጊዜውም ከነርሱ ጋር ጦርነትና ግጭት ማካሄዱን መግለፁ ነበር፡፡ ይህ በርግጥ እውነት ነበር፡፡ በ10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተካሄደውና በጉዲት ከተመራው የአይሁዶች አመጽ በኋላ ለብዙ መቶ ዓመታት በኢትዮጵያውያን አይሁዶችና ክርስቲያኖች መካከል ግጭት ተካሂዷል፡፡

ምንም እንኳን በደብዳቤው ውስጥ የተጠቀሱት እስፈሪ አውሬዎች የፈጠራ ቢምስሉም፣ ደብዳቤው ሙሉ በሙሉ የተጭበረበረ ነው ለማለት አልደፈርኩም፡፡ ለኔ የገባኝ ደብዳቤው በወቅቱ በአውሮፓ የነበሩ ኃያላንን ለማስፈራራት የተጻፈ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ ለምሣሌ "ካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" ስለሠራዊቱ እንደሚከተለው መጻፉ ነው ፡፡

> ከዓለም በውበታቸውና በታላቅነታቸው ተወዳዳሪ የሌላቸው ጽንዲሁም በበርካታ ወታደሮች የሚጠበቁ አርባ ሁለት ቤተመንግስቶች አስገንብተናል፡፡ አስር ሺህ ምርጥ ወታደሮች፣ ስድስት ሺህ ባለጠስፈንጥሮች፣አስራ አምስት ሺህ ቀስተኞች፣ አርባ ሺህ ፈረሰኞች አሉን፡፡ ወደ ጦርነት ስንጓዝ አርባ ሺህ ቀሳውስት ከፊታችን ሲንቀሳቀሱ፣ ያን ያህል ምርጥ ወታደሮች ደግሞ ያጅቡናል፡፡ ቀጥሎ ሁለት መቶ ሺህ ሰዎች በእግር ይከተሉናል፡፡ ይህም ስንቅ የሚያጓጉዙትን የዕቃ ጋሪዎች፣ መሣሪያና ትጥቅ የሚሸከሙትን ዝሆኖችና ግመሎች ሳይጨምር ነው፡፡

በርግጥ ይህ ጉራ ቢመስልም፣ በተለይ ቴምፕላሮቹ ላይ ያነጣጠረ ይመስላል፡፡ በተለይ "ለፈረንሳዩ ንጉሥ" በተፃፈ ደብዳቤ የሚከተለው ሰፍሯል፡፡

> የናንተው ወገን ባለሟልና አጃቢዎቻችሁ የሆኑ የተወሰኑ ግለሰቦች ከአረቦች (ሳራሲኖች) ጋር አብረዋል፡፡ እናንተ ግን የሚረዷችሁ መስሏችሁ የልባችሁን ትነግሯቸዋላችሁ፡፡ እነሱ ግን ከሃዲና ተሸፋቾች ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህን ከሃዲ ቴምፕላሮች በሞት መቅጣት እንድትችሉ ብርታቱን ይስጣችሁ፡፡

ይህን ማኅበረ ከሌላው የደብዳቤ መልዕክት ጋር አነፃፅሬ ስመረምረው፣ በ1165 የትኛው የኢትዮጵያ ንጉስ ነው ለአውሮፓ ነገሥታት ወታደራዊ የበላይነቱን በመግለጽ በትምክህት ሊናገር የሚችልና ነፍጠኞቹ ቴምፕላሮችን ከማንቋሸሽ አልፎ በሞት እንዲቀጡ የሚገፋፋ? የሚሉት ሁለት ጥያቄዎች በአእምሮዬ ውስጥ ተደቀኑ፡፡ ይህን ሊያደርግ የሚችል ከሐርቤ ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም፡፡ ከዚህ በፊት እንደደረስኩበት በ1177 ጳጳስ እስክንድር ሳልሳዊ ለፕሬስተር ጆን ወይም ለካህኑ ንጉስ ዮሐንስ ብለው ደብዳቤ የፃፉት ለርሱ ነው፡፡

ሐርቤ ላይ በተለይ ያተኮርኩበት አንደኛው ምክንያት ከቃላት ትርጉም ጋር በተያያዘ ፍንጭ ስላገኘሁ ነው፡፡ በምርምሬ እንደተረዳሁት በዘመኑ የነበሩ ሁሉም የዛጉዌ ነገሥታት የሚጠሩት ጃን የሚለውን ቃል በማስቀደም ነበር (ጃን እከሌ እንደሚባለው)፡፡ ይህም ጃኖ ከሚለው ቃል የመጣ ነው፡፡ ይህ ቀይ፣ ወይን ጠጅማ ሰፊ ጥለት ያለው የነገሥታት ዘሮች ብቻ የሚለብሱት ልብስ ነው፡፡ የቃሉ ትርጉም ጃንሆይ እንደማለት ሲሆን፣ ጆን (John) ከሚለው የእንግሊዝኛ ቃልም ጋር ሳይምታታ አልቀረም፡፡ ብዙዎቹ የዛጉዌ ነገሥታት ቁሶች ስለነበሩ "ፕሬስተር ጆን" ወይም "ካህኑ ዮሐንስ" የሚለውን መጠሪያም በዚህ የተነሳ ሳይፈጥሩት አልቀሩም፡፡

ከዚህም ሌላ የደብዳቤው ፀሐፊ ሐርቤ ለመሆኑ የሚያሳምኑ ጠንካራ ምክንያቶች አሉ፡፡ ሐርቤ በ1165 በበርካታ ፖለቲካዊ ችግሮች የተጠመደ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ከሱ ሸሽቶ የሄደው ላሊበላ፣ በስደት ኢየሩሳሌም ውስጥ መኖር ከጀመረ አምስት ዓመታትን አስቆጥሮ ስለነበር፣ በቆይታው ወቅት ከቴምፕምላሮች ጋር ሊተዋወቅና ወዳጅነትን ሊፈጥር እንደሚችል ይገመታል፡፡ ላሊበላ ምናልባትም ቴምፕላሮቹ ሐርቤን እንዲያስወግዱለት ሳይጠይቃቸው አልቀረም፡፡ የኋላ ኋላም ይህንኑ የተጠነሰሰበትን ሴራ ሐርቤ ሰምቶ ይሆናል፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው ግምታዊ አስተያየቶች መሠረተ ቢስ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ሐርቤ በኢየሩሳሌም የቤተመቅደስ ማረፊያ ቦታ እንዲሰጠው ጳጳስ እስክንድር ሣልሣዊን መጠየቁ፣ ይህም ጥያቄ እስራኤል ውስጥ ለጳጳሱ ተወካይ ለነበረው ሰው መቅረቡ የሚያመለክተው ሐርቤ መልዕክተኞችን በየጊዜው ወደኢየሩሳሌም እንደሚልክና እነዚህም መልዕክተኞች በምልልሳቸው ወቅት ልዑል ላሊበላና ቴምፕላሮች ያቀዱትን የመንግሥት ግልበጣ ሴራ በተመለከተ በ1165



ምሥጢራዊ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘታቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህን የሐርቤ መልዕክተኞች ችግሩ ስላሳሰባቸው እዚያው ኢየሩሳሌም እያሉ "በካህኑ ንጉሥ ዮሐንስ" ስም ከዚህ በፊት የተጠቀሰውን ዛቻ የተቀላቀለበት ደብዳቤ ጽፈዋል፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ፈረንሳውያን የነበሩትን የቴምፕላሮች ስም በማጉደፍና በክህደት ወንጀል በመክሰስ በልዑል ላሊበላና በቴምፕላሮች መካከል የተፈጠረውን ግንኙነት ለማስቀረት የነደፉት ስትራቴጂ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አደረብኝ፡፡

ያቀረብኩት ምክንያት ማራኪ ቢሆንም፣ አምኖ ለመቀበል ግን አስቸጋሪ ነው፡፡ በዚሁ መስመር ልግፋ ወይስ ልተወው? እያልኩ ሳለሁ፣ "ፓርዚቫል" በተሰኘው ጽሑፍ ውስጥ ላሊበላ ከቴፕምላሮች ጋር ስለመዶለቱ ማረጋገጫ ሊሆኑ የሚችሉ አንቀጾችን አገኘሁ፡፡

## "ወደአፍሪካ መዝለቅ. . ."

ላሊበላ ንጉሥ ሐርቤን ከዙፋኑ ካስወገደው ከጥቂት ዓመታት በኋላ የተጻፈው ፓርዚቫል፣ ቴምፕላሮችን በተለያዩ ቦታዎች በቀጥታ በስማቸው ጠቅሷቸዋል- "የቅዱስ ጽዋው ማህበር (ድርጅት)" አባላት በማለት፡፡

ዎልፍራም በተደጋጋሚ ያሰፈረውና ትኩረቴን የሳበው የነዚህ ቴምፕላሮች አልፎ አልፎ ለልዩ ምሥጢራዊ ተልዕኮ ባድብቅ ወደባሕር ማዶ አገሮች መጓዛቸው ሲሆን፣ ይህንንም የሚያደርጉት የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ መሆኑን ለምሣሌ እንደሚከተለው ገልጿል፡፡

> በቅዱስ ጽዋው ላይ ጽሑፍ ታየ፡፡ ጽሑፉም "ማንም ቴምፕላር መብታቸውን ሊያረጋግጥላቸውና ሊያጉናጽፋቸው በእግዚአብሔር ለሚላከባቸው ለሩቅ ሕዝቦች፣ ስሙንና የዘር ግንዱን አይግለጥ፡፡ የዚህ ዓይነት ጥያቄ ለእርሱ ከቀረበ እነዚያ ሰዎች እርሱን እዚያ እንዲኖር አያደርጉትም፡፡ ነገር ግን መብታቸውን ለማስከበር ከመርዳት ወደኋላ አይበል፡፡"
> ወይም በተመሳሳይ፤ አንድ አገር መሪዋን አጥታ ሕዝቦቿም የእግዚአብሔርን ርዳታ በመለመን ከቅዱሱ ጽዋው ማኅበር አዲስ መሪ በጠየቁ ጊዜ ጸሎታቸው ይፈጸምላቸዋል... እግዚአብሔርም በምሥጢር እነዚህን መልዕክተኞች ይልካል፡፡

ከላይ የተገለፁት አባባሎች ሁሉ ጠቃሚ ቢሆኑም በይበልጥ ትኩረቴን የሳበው ግን ከአንድ ገጽ በኋላ የተጻፈውና የቅዱስ ጽዋው ማህበር አባል የሆነ ሰው የተናገረው ቃል ነበር፡፡ ይኸውም "ሮሐን አልፎ ወደአፍሪካ መዝለቅ..." የሚለው ነው፡፡

"ፓርዚቫል"ን ያጠኑ ምሁራን "ሮሐ" የተባለው ቃል የሚያመለክተው በሳናጉ ስቲሪያ ውስጥ የምትገኘውን ሮሂትስሸርበርግ

የምትባለውን በታ ነው ይላሉ። ይህ አባባል ግን ከአፍሪካ ጋር ያልተገናዘበ በመሆኑ ትርጉም የለሽ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በዎልፍራም ጽሑፍ ላይ የሚመራመሩ የጀርመንና የእንግሊዝ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን ግን ሮሐ የተባለው ስም በመሐል ኢትዮጵያ ደጋማው ክፍል የሚገኘው የጥንታዊ ከተማ ስም መሆኑንና ከተማውም በኋላ ከኢየሩሳሌም በ1185 ተመልሶ በድል አድራጊነት ዘውድ በጫነው በንጉሥ ላሊበላ ስም መጠራቱን የሚያውቁ አይመስለኝም፤ እንዲያውቁም አይጠበቅባቸውም። ከዚህም በተጨማሪ እነዚሁ የጀርመን የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ይህ ንጉሥ በኢየሩሳሌም ለ25 ዓመታት በስደት መቆየቱንና ከቴምፕላሮች ጋር ግንኙነት እንደነበረውም አያውቁም። ቴምፕላሮቹም የጠፋውን የቃል ኪዳን ታቦት ፈልጉ የማግኘት ልዩ ተልዕኮ እንደነበራቸውም ፈጽሞ የተገነዘቡ አይመስለኝም።

ለኔ ዋነኛው ጥያቄ ግን፤ ላሊበላ ወደኢትዮጵያ ሲመለስ በቴምፕላር ሠራዊት (ድጋፍ) ንጉሥ ሐርቤን ከዙፋኑ አስወግዶ ይሆን? የሚለው ነበር። በአጋጣሚ በ1983 ወደላሊበላ ከተማ ለመንግሥት ሥራ ሄጄ በነበርኩበት ጊዜ ያሰፈርኳቸውን የጽሑፍ ማስታወሻዎቼን ማገላበጥ ስጀምር አንድ ትኩረትን የሚስብ ነገር ተመለከትኩ።

ይኸውም፤ ከላሊበላ አብያተክርስቲያናት ውስጥ በተለይ በቤተማርያም ቤተክርስቲያን ጣራ ላይ የደበዘዙ ቀይ ቀለም የተቀቡ የአውሮፓ የመስቀል ጦረኞችን አርማ ዓይነት የያዙ መስቀሉች በማየቴ በወቅቱ "እነዚህ መስቀሎች ከሌሎች የኢትዮጵያ መስቀሎች ጋር በፍጹም አይመሳሰሉም" በማለት በማስታወሻዬ ውስጥ ከማስፈሬም በላይ፥ ከመስቀሎቹም መካከል የአንዱን ምስል ጫር፤ ጫር አድርጌ ነበር። የመስቀሎቹ ግማዶች የሦስት ጐን ቅርጽ ሲኖራቸው፤ ከመሃል ወደዳር እየሰፉ የሚሄዱ ናቸው።

በ1983 ላሊበላን በጐበኘሁበት ወቅት ይህ ቀይ "ክርዋ ፓቲ" የተሰኘ መዳፍ መሰል መስቀል የቴምፕላሮች ዓርማ መሆኑን አላውቅም ነበር። ይህን ያወቅሁት ግን በ1989 ነው። ከዚህም በተጨማሪ ቴምፕላሮች መላ ታሪካቸው ብርቅና ድንቅ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናትን ከማነጽ ጋር የተያያዘ መሆኑን ለማወቅ ችያለሁ።

እነዚህ የላሊበላ አብያተክርስቲያናትም በሥነ ሕንፃ ጥበብ ረገድ እጅግ የረቀቁ ናቸው። ምንም እንኳን ሌሎች ጥንታዊ፥ ከቋጥኝ የተሠሩ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በኢትዮጵያ ውስጥ ቢኖሩም፥ ንጉሥ ላሊበላ ካሠራቸው ጋር ፈጽሞ አይወዳደሩም። ዩኔስኮ እነዚህ አብያተክርስቲያናት ከዓለም አስደናቂ ሥራዎች መካከል ሊመዘገቡ ይገባቸዋል ብሎ ያምናል። አብያተክርስቲያናቱ ከአንድ ወጥ ድንጋይ እንዴት ሊታነጹ እንደቻሉ ለማወቅ የቢያ እንድም ተመራማሪ እስከአሁን አልተገኘም። አንዳንዶች ስለነዚህ ሥራዎች ሲናገሩ፤ ንጉሥ ላሊበላ የሕንዶችንና የግብጽ ግንበኞችን ቀጥሮ አሠርቷል ይላሉ። በኢትዮጵያውያን አፈታሪክ ደግሞ ሥራዎቹ በመላእክት እገዛ የታነጹ ናቸው ተብሎ ይታመናል። የኔ ጥያቄ ደግሞ የዚህ ሥራ ባለቤት ቴምፕላሮች ይሆኑ? የሚል ነው።



በ1983 ላሊበላን በጐበኘሁበት ወቅት የጻፍኩት ማስታወሻ የሚከተለው ነበር።

> ረዘም ያሉ ሕንፃዎች ናቸው። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናትም ከስምንት መቶ ዓመታት በኋላ አምልኮተ እግዚአብሔር እየተፈፀመ ባቸው ነው። የሕንፃዎቹ አሠራር ዛሬ ከምናየው የግንባታ ሥራ ፍጹም የተለየ ነው። ከእሳተ ገሞራዊ ቋጥኞች ተፈልፍለው የታነጹ፥ በሰው እጅ የተሰሩ የማይመስሉ፥ በግዝፈታቸውና በአሠራራቸው የሚያንጸባርቁት የጥበብ ውጤቶች... እጅግ በርካታ፥ የዋሻ ውስጥ ለውስጥ መንገዶች፥ በሮች፥ ግምጃ ቤቶች.... በርግጥም እንቆቅልሾች ናቸው። አራቱ አብያ ተክርስ ቲያናት ሙሉ በሙሉ በራሳቸው የቆሙ ናቸው። ከአካባቢያቸው ካለው ቋጥኝ ጋር የሚያገናኛቸው የተገነቡበት መሠረት ብቻ ነው። ሁሉም ከአንድ ወጥ ቋጥኝ የተጠረቡ ሲሆኑ፤ በተለይ ከሁሉም ትንሽ ራቅ ብሎ የቆመው ቤተ ጊዮርጊስ የተባለው ልዩና ግርማ ሞገስ ያለው ነው። ከፍታውም ከአሥራ ሁለት ሜትር የሚበልጥ ሆኖ ከላይም ከውስጥም የመስቀል ቅርጽ እንዲኖረው ተደርጐ የተሠራ ነው። ባጭሩ በጉድጓድ ውስጥ የተቀመጠ ሕንፃ ነው።

በመጨረሻም "መላእክት ገነቡት የሚለውን አባባል ወደጐን ተወት እናድርግና "በርግጥ እነዚህ የላሊበላ እጹብ ድንቅ ሥራዎች እንዴት ተሠሩ?" የሚለውን ሐሳብ እናንሣ። እውነቱን ለመናገር ...ማን እንደሠራቸው እስካሁን የሚያውቅ ሰው የለም። ድንጋዮቹ በምን ዓይነት ጥበብ እንደተፈለፈሉና እንደተጠረቡ ሳይታወቅ 'ሁሉም ነገር በታሪክ ጭጋግ ውስጥ ተሸፍኖ ቀርቷል" የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሼ ነበር።

በርግጥ የላሊበላ አብያተክርስቲያናትን አሠራር ምሁራን ሊፈቱት ያልቻሉት እንቆቅልሽ ነው። ማስታወሻዬን በማገላብጥበት ጊዜ ስለቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የመዘገብኩትን እንደገና ማየት ጀመርኩ።

> ቅድስተ ቅዱሳኑ መግቢያ አጠገብ ከመሬት ወደጣሪያው የወጣ አንድ ወፍራም የድንጋይ ምሰሶ ይታያል። ይህን ያላዩኝ ቄስ ምሰሶው ንጉሥ ላሊበላ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት እንዴት አድርጐ እንዳሠራቸው የሚገልጽ ጽሑፍ የተጻፈበት እንደሆነ ገለጹልኝ። ሆኖም በምሰሶው ላይ የተጻፈውን ጽሑፍ ለማየት አልቻልኩም። ምክንያቱም ከላይ እስከታች ድረስ በጣም ወፍራም በሆነ ጨርቅ ተሸፋፍኗል። ለማየት ይቻል እንደሆን ላቀረብኩላቸው ጥያቄም ቄሱ በተደናገጠ ስሜት "ይህ የተቀደሰ ምሰሶ ነውና አይደፈርም" በማለት መልስ ሰጥተውኛል።

እንግዲህ በላሊበላ ካየሁት ቀይ ቀለም ከተቀባው የቴምፕላሮች መስቀል ምልክት በስተቀር የነርሱ እጅ በህንፃው ሥራ ለመኖሩ

ያገኘሁት ማስረጃ የለም። ሆኖም ጥረቴን አላቋረጥኩም። በዚህ መካከል ከ1520-1526 የፖርቱጋል የልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ ስለአጋጠሙት ጉዳዮች በቄስ ፍራንቼስኮ አልቫሬዝ የተጻፈ "The Prester John of Indies" ("የኢንዲዙ ካህን ንጉሥ ዮሐንስ") የሚል ወደ እንግሊዝኛ የተተረጐመ መጽሐፍ አገኘሁ። መጽሐፉ በ1540 በሊዝበን (ፖርቱጋል) የታተመ ሲሆን፣ ወደ 500 ገጾች አሉት። ይህን መጽሐፍ ምሁራን ስለኢትዮጵያ ታሪክ በጥልቅና በትኩረት የተጻፈ በማለት ያደንቁታል። ይህን ምስክርነት በማሰብ መጽሐፉን አገላበጥኩ። በቅጽ አንድ፣ ገጽ 205 ላይ አልቫሬዝ ስለላሊበላ ጉብኝቱ በሰፊው ይዘረዝራል።

አልቫሬዝ ላሊበላ የደረሰው አብያተ ክርስቲያናቱ ከታነጹ ከ350 ዓመታት በኋላ ነበር። ስለላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት በዚያን ጊዜ አልቫሬዝ የጻፈውንና እኔ በጉብኘኋቸው ወቅት ያየኋቸው ሕንፃዎች በዘመናት ምንም እንዳልተቀየሩ በመገንዘቤ እጅግ ተደነቅሁ።

አልቫሬዝ እንዲህ ይላል።

> ስለእነዚህ ሕንፃዎች መጻፍ ደከመኝ። ምክንያቱም የማየውን ማመን አቃተኝ። ከዚህ በተጨማሪ ብጽፍ ማንም አያምነኝም፤ ሐሰተኛ እባላለሁና። ስለዚህም በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ፤ የጻፍኩት ሁሉ እውነት ነው። ምንም ከራሴ የጨመርኩት የለም። እንዲያውም ያልጻፍኩትና የተውኩት ብዙ ነው። ውሸታም ተብዬ እንዳልወቀስ። ዓለም ይህን ድንቅ ሥራ እንዲያውቅልኝ እመኛለሁ።

በጉብኝቱ ወቅት አልቫሬዝ የአብያተ ክርስቲያናቱ አባቶችን በማነጋገር እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በማን እንደታነጹ መጠየቁን ይገልጽና በመቀጠልም፣ "እንደነገሩኝ አብያተ ክርስቲያናቱን ለመጨረስ ሃያ አራት ዓመታት ፈጅቷል። ይህም በጽሑፍ ሰፍር ይገኛል። የተሠራውም በነጮች ነው። እነሱም የሠሩት በንጉሥ ላሊበላ ታዘው ነው" ይላል።

ይህን ምስክርነት ወደጐን ለመተው አልፈለግኩም። መደርደሪያዬ ላይ ካሉት የታሪክ መጻሕፍት አንዳቸውም ከአልቫሬዝ በፊት "ነጮች ወደ ኢትዮጵያ ሄደዋል" የሚል ነገር አላሰፈሩም። ይህ ማለት ግን የሃይማኖታዊና ወታደራዊ ሥርዓት መሥራቾች፣ ምሥጢረኞችና በዓለም አቀፍ ተጓዦነታቸው የታወቁ በምዕራም ታሪክ ውስጥ "ማንነታቸው እንዲጠየቅ የማይፈቅዱ የተባሉ ወደሩት ሕዝቦች የሚላኩ... መብታቸውን እንዲያገኙ የሚረዱ፣ በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዋና መቀመጫቸውን በኢየሩሳሌም ከተማ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ መሠረት ያደረጉ ነጮች፣ ወደኢትዮጵያ ፈጽሞ አልሄዱም" ማለት አይደለም።

የሚገርመው ነገር ቴምፕላርሽ፣ ምዕራም ይህን ምሥጢር በታሪኩ ውስጥ እንዲያካትተው የፈለገበት ምክንያት ምን ይሆን? መልሱ ምናልባት እንደምገምተው ምሥጢር አዘል ታሪክ ተጽፎ



በመሬት ውስጥ ቢደበቅ ወይ ይጠፋል፤ አለያም በታው ይዘነጋል። ለሕዝቡ ዕይታ በሚቀርብ መልክ ተጽፎ ቢቀርብ ግን ከዘመን ወደ ዘመን ለትውልድ ሊተላለፍ ይችላል ከሚል አስተያየት ተነስተው ይሆናል።